Daniel Fikadu Tesfaye

Attorney at all Federal Courts

ዳንኤል ፍቃዱ ተስፋዬ

በማናቸውም ፍ/ቤት ጠበቃና የህግ አማካሪ

0913158507
0978554559

በዳንኤል ፍቃዱ (ጠበቃና የህግ አማካሪ)

ያልታተሙ የሰበር ውሳኔዎች በአንድ ተሰብስበው የተዘጋጁ

ቅፅ _ 4

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 205862

ህዳር 28 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች- አቶ አባይ ይርጋ

ተጠሪ- የአሶሳ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማት ማኔጅመንት መምሪያ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአሶሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ በአሶሳ ከተማ የሚገኘውንና እና የይዞታ መለያ ቁጥሩ 72/30/19 የሆነውን ሱቅ ወ/ሮ ትርንጎ በላይ እና አቶ በላይ አበበ ከተባሉ ግለሰቦች ላይ በውል ገዝቼ ውሉ ፀድቆ ስሙ-ሀብቱ ወደ እኔ ዞሮ ቁጥሩ 355/164 የሆነ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶኝ ለ10 ዓመታት ያክል ስሰራበት ቆይቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ወ/ሮ ማሪቱ መንጌ የተባለች ግለሰብ በ2008 ዓ.ም በአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይዞታ ይገባኛል ክርክር አቅርባ ጉዳዩን እንዲያጣራ የታዘዘው ተጠሪ ለፍርድ ቤቱ በላከው ማስረጃ አመልካች 15.18 ካ.ሜ ይዞታ እንዳለፍኩኝ ለአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመግለጽ በህጋዊ መንገድ ያገኘሁትን ይዞታ በፍርድ አሳጥቶኝ ለከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ የዳረገኝ በመሆኑ ለደረሰብኝ ጉዳት ብር 3,000,000.00 ካሳ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት የጠየቀዉን ዳኝነት መነሻ ያደረገ ነዉ ፡፡ ክሱ እንደሚከተለው ቀርቧል…………….

ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ አመልካች ከወ/ሮ ማሪቱ መንጌ ጋር በነበራቸው ክርክር ከደንብ ውጪ የግለሰቧን ይዞታ በማለፍ የያዙትን እንዲለቁ ከተወሰነባቸው በኋላ በካርታ ቁጥር 355/164/07 የተሰጣቸው የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሠረዘ በመሆኑ አመልካች ክስ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማቅረብ አይችሉም፤ ያቀረቡት የካሳ ጥያቄም የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ከክሱ በነፃ ሊያሰናብተን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ በአንድ ወቅት ለአመልካች የሰጠውን የባለሀብትነት ደብተር ህጋዊ ምክንያት ሳይኖረው የሰረዘባቸው በመሆኑና ይህም አመልካች ላይ ጉዳት ያደረሰባቸው በመሆኑ አመልካች ከተወሰደባቸው ይዞታ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ይዞታ በምትክ እንዲሰጣቸው እና የ10 ወራት የሱቅ ኪራይ ብር 60,000.00 በካሳ መልክ ተጠሪ ይክፈላቸው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት አመልካች ይግባኛቸውን እና የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች በቅደም ተከተል ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በቀን 30/07/2013 ዓ.ም በተፃፈ 03 ገጽ የሰበር አቤቱታ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ የተሳሳተ መግለጫ ምክንያት ተጠሪ በህጋዊ መንገድ ያገኘሁትንና የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያወጣሁበትን ከአንድ እስከ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር የሚገመት ሱቅ ያፈረሰብኝ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ግምቱ እንዲከፈለኝ ሳይወስን ማለፉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩም በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች ይዞታዬ በመወሰዱ ምክንያት ለደረሰብኝ ጉዳት ብር 3,000,000.00 ካሳ ይከፈለኝ በማለት ጠይቀው እያለ የስር ፍርድ ቤት የጉዳቱ መጠን በዝርዝር ተለይቶ አልቀረበም በሚል ምክንያት የአስር ወር የሱቅ ኪራይ ብቻ እንዲከፈላቸው የወሰነበት አግባብ መጣራ ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቧል፡፡ በዚሁም መሠረት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ በቀን 04/02/2014 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ ምንም እንኳን አመልካች አንዲለቁ በተወሰነባቸው ይዞታ ላይ ስልጣን ባለው አካል የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ቢሰጣቸውም ይዞታው የተገኘበት ሁኔታ በሌላ ሰው ይዞታ ላይ ተደርቦ በተጭበረበረ መንገድ ስለሆነ ካሳ የመጠየቅ መብት የላቸውም፤ የስር ፍርድ ቤትም የአመልካች ይዞታ በሌላ ሰው ይዞታ ላይ የተደረበ መሆኑን በማረጋገጥ እንዲለቁ በሌላ መዝገብ የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ለአመልካች ትክ ቦታ እና ካሳ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቶ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሠበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉን ውሳኔ ከግራ ቀኝ ክርክር እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም አመልካች በስር ፍርድ ቤት ባቀረበዉ ክስ ለጠየቀዉ ዳኝነት መሠረት ያደረገዉ በተጠሪ የተሰጠዉን ማስረጃ መሠረት በማድረግ በሌላ መዝገብ ላይ በተሰጠ ዉሳኔ 15.8 ካ/ሜትር ከይዞታዉ እንዲቀነስ በመደረጉ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት ካሳ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንዲከፈለዉ ነዉ፡፡ የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻዉ ጭብጥም አመልካች በዚህም መልኩ የጠየቀዉ ዳኝነት ከመነሻዉም ተገቢነት ያለዉ ነዉ ወይ? የሚል ነዉ፡፡

በመሠረቱ በፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ ይጎዳኛል ወይም መብቴን ይነካል የሚል ሰዉ እንደነገሩ ሁኔታ ዉሳኔዉን በሰጠዉ ፍርድ ቤት ወይም በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርቦ ዉሳኔዉን በማሳረም መብቱን ማስከበር የሚችልበትን ሥርዓት የፍትሐብሔር ሥነ ስርዓት ህጉ ይዘረጋል፡፡ በዚህም መሠረት ፍርድ ቤቱ ለሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ያደረገዉ በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበዉን ሰነድ ወይም ሐሰተኛ የምስክርነት ቃልን ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቀስ ተግባርን መሠረት በማድረግ ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 6 መሠረት፣ በክርክር ሂደት የተፈጸመ የሥነ ሥርዓት ግድፈት ከሆነ በአንቀጽ 207-211 መሠረት እንዲሁም ዉሳኔዉ መብቴን ነክቷል የሚል ሰዉ ተከራካሪ ያልነበረ ሦስተኛ ወገን ከሆነ በአንቀጽ 358 መሠረት ዉሳኔዉን ለሰጠዉ ፍርድ ቤት አቤቱታዉን በማቅረብ መብቱን ማስከበር የሚችል ሲሆን፤ ከዚህ ዉጭ ባሉት ሁኔታዎች አቤቱታዉን ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ መብቱን ማስከበር የሚችል ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 320 እና ተከታዮቹ ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ የፍርድ ቤት ዉሳኔ በህግ በተዘረጋዉ ሥርዓት መሠረት ካልታረመ እና በማንኛዉም ጊዜ በዘፈቀደ የሚለወጥ ወይም የማይፈጸም ከሆነ የፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ተገማችነት እንዳይኖረዉ እና በዚህም ዜጎች በፍርድ ቤቶች ላይ አመኔታ እንዳይኖራቸዉ ሊያደርግ ይችላል፤ የህግ የበላይነት እንዲሸረሸርም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ በተዘረጋዉ ሥርዓት መሠረት አቤቱታ ቀርቦበት እንዲታረም ያልተደረገ ዉሳኔ ከነስህተቱ ጸንቶ የሚቀጥል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 212 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ በዚሁ ምክንያት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ፍርድ ቤት ዉሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ በግራ ቀኝ የቀረቡትን ማስረጃዎች ህጋዊነት፣ ትክክለኛነት፣ ተቀባይነት እና አግባብነት በክርክር ሂደት የማጣራት እና የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለበት የሚታወቅ ነዉ፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤት ዉሳኔ የሰጠዉ በሐሰት የቀረበን ማስረጃ መሠረት በማድረግ ወይም በአግባቡ ሳይመረምር እና ሳይመዝን ነዉ የሚል ተከራካሪ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ ከላይ በተመለከተዉ አግባብ አቤቱታዉን አቅርቦ የማስረጃ አቀባበል እና የምዘና መርህን መሠረት ያላደረገ ዉሳኔ እንዲታረም መጠየቅ የሚችል ሲሆን፣ በዚህ መልኩ ካልጠየቀ እና ካላሳረመ ፍርድ ቤቱ ለሰጠዉ ዉሳኔ መሠረት ያደረገዉ ማስረጃ ትክክለኛ እና አቀባበሉ እንዲሁም የምዘና ሥርዓቱ ተቀባይነት ያለዉን የማስረጃ አቀባበል እና የምዘና መርህን መሠረት ያደረገ ነዉ ተብሎ ይገመታል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ ቀደም ሲል መሬቱን አስመልክቶ በአሶሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ዉሳኔ ተጠሪ ያቀረበዉን የሐሰት ማስረጃ መሠረት በማድረግ ነዉ የሚል ከሆነ አመልካች እንደነገሩ ሁኔታ አቤቱታዉን በሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 6 መሠረት በዚያዉ መዝገብ ላይ በማቅረብ ማሳረም አሊያም ጉዳዩ በአንቀጽ 6 መሠረት ሊታይ የሚችል አይደለም የሚል ከሆነም አቤቱታዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ማሳረም ነበረበት፡፡ አመልካች ይህንን አላደረገም፡፡ ይህ በመሆኑም አመልካች ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነዉን 15.8 ካ/ሜትር ይዞታ ለሌላ ሰዉ እንዲለቅ በሚል የተሰጠ ዉሳኔ እንደጸና ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ቀደም ሲል ፍርድ ቤቱ የሰጠዉ ዉሳኔ ትክክለኛ ማስረጃን መሠረት በማድረግ እንደተሰጠ ዉሳኔ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ከፍ ሲል በተመለከተዉ ምክንያት በተጠሪ የተሰጠ ማስረጃ ሐሰተኛ መሆን ያለመሆኑ ጉዳይ የሚመረመረዉ በዚያዉ መዝገብ ላይ አቤቱታ በማቅረብ እንጂ በአዲስ የክስ መዝገብ ሊሆን አይገባም፡፡ በመሆኑም በተጠሪ የተሰጠዉን ሐሰተኛ ማስረጃ መሠረት በማድረግ በተሰጠ ዉሳኔ ምክንያት ጉዳት ደርሶብኛል በማለት አመልካች በሌላ የክስ መዝገብ ላይ ያቀረበዉ ዳኝነት ከመነሻዉም ተገቢነት ያለዉ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የስር የከተማዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በዚህ መልኩ ያቀረበዉን ዳኝነት ዉድቅ ማድረግ ሲገባዉ ተቀብሎ በሌላ መዝገብ ላይ ህጋዊነቱ ወይም ትክክለኛ መሆኑ ተረጋግጦ ለዉሳኔዉ መሠረት እንደሆነ የሚገመተዉን ማስረጃ ህጋዊነት እና ትክክለኛነት መርምሮ ተጠሪን ኃላፊ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ ሊታረም የሚገባዉ መሠረታዊ ስህተት የህግ ስህተት ነዉ፡፡ ይሁንና ኃላፊነትን አስመልክቶ ተጠሪ አቤቱታ ባለማቅረቡ ዉሳኔዉን ለመሻር ያልተቻለ ሲሆን፣ በሌላ በኩል አመልካች ያቀረበዉን ክስ ያላግባብ ተቀብሎ ብር 60,000.00 ካሳ እንዲከፈለዉ ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ አመልካችን ያላግባብ የጠቀመዉ ነዉ የሚባል ካልሆነ በስተቀር አልጎዳዉም፡፡ በዚህም ምክንያት የካሳዉ መጠን የተወሰነበትን አግባብነት አስመልክቶ በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘዉን ጭብጥ መመርመር ሳያስፈልግ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ዉሳኔ**</u>

1. በአሶሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00283 በቀን 20/02/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 11155 በቀን 06/07/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 11219 በቀን 24/07/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ትዕዛዝ ምክንያቱ ተለዉጦ ከዉጤት አንፃር በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንተዋል፡፡

2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ ዪራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 205786
ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የቤጊ ከተማ አስተዳደር አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ደጉማ ባያ ተወካይ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ቁጥር 335735 መጋቢት 21ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ እንዲታረም አመልካች በመጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ በተጀመረበት የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ወለጋ ዞን ቤጊ ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሣሽ የቤጊ ከተማ መሬት ልማት ማኔጅምንት ፅ/ቤት ተከሣሽ እንዲሁም አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 40(2) መሰረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ጣልቃገብ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ግንቦት 6ቀን 2010ዓ/ም በተፃፈ ክሣቸው በቤጊ ከተማ ቀበሌ 02 በተለምዶ ቅዳሜ ገበያ ተብሎ በሚታወቀዉ ስፍራ አዋሳኙ በክሱ የተገለፀውንና ከ1975 ዓ/ም ጀምሮ ከአባቱ በዉርስ የተላለፈለትን ይዞታ የከተማው መሬት ልማት ማኔጅመንት ፅ/ቤት ምንም መብት ሣይኖረው በ2005ዓ/ም ወስዶ 16 ቤቶችን በሁለት ረድፍ እንዲሰራበት ያደረገ በመሆኑ የተሰራውን ቤት አፍርሶ ይዞታውን እንዲመልስለት ጠይቋል፡፡

ተከሳሽ የነበረው የቤጊ ከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት ፅ/ቤት ተጠሪ ክስ ያቀረበበት የከተማ መሬት በመሆኑ ስፋቱን በካሬ ሜትር ሣይገልፅ አዋሳኙን ብቻ መግለፁ ተገቢ አለመሆኑን፣ የቤጊ ከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት ፅ/ቤት በ2008ዓ/ም የተቋቋመ በመሆኑ በ2005ዓ/ም ተፈፅሟል ለተባለ ድርጊት ሀላፊነት የሌለበት መሆኑን፣ ይዞታው የተጠሪ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሣያቀርብ ክስ ማቅረቡ ተገቢነት የለውም ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ክሱን ሰምቶ የመጀመሪያ መቃወሚያ ክርክሩን በብይን ውድቅ አድርጎ የከተማው አስተዳደር (አመልካች) በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 40(2) መሰረት በተከሣሽነት ወደ ክርክሩ እንዲገባ አድርጓል፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ ክስ ባቀረበበት መሬት ባለይዞታ መሆኑን የሚያረጋግጥ ካርታ ሣይኖረው ክስ ማቅረብ የማይችል መሆኑን፣ የመሬቱን ስፋትም በካሬ ሜትር አለመግለፁን፣ በይዞታው ላይ የተሰሩት ቤቶች እያንዳንዳቸው ከ300ሽህ ብር በላይ ስለሚያወጡ የስር ፍርድ ቤት ስልጣን የሌለው መሆኑን፣ አከራካሪው ይዞታም ከ1992ዓ/ም ጀምሮ ለሕዝብ ጥቅም ማለትም የገበያ ቦታ መሆኑን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ እንዲደረግለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚውን ውድቅ አድርጎ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የአመልካች ነው ወይስ አይደለም? የመሬት ልማት ማኔጅሜንት ፅ/ቤትስ ሃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም? አመልካች ይዞታውን የያዘው በምን ምክንያት ነው? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ የአመልካችንና የተጠሪን ምስክሮችን ሰምቶ አከራካሪው ይዞታ የከተማ ይዞታ በመሆኑ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ከተወሰደ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 እና በደንብ ቁጥር 155/2005 እና 182/2008 መሰረት የተፈፀመ መሆኑ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት አመልካች በይዞታው ላይ የተሰሩትን ቤቶች አፍርሶ ይዞታውን ለተጠሪ እንዲያስረክበው ወስኗል፡፡

አመልካች ውሣኔውን በመቃወም የይግባኝ አቤቱታውን ለምዕራብ ወለጋ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ አፅንቷል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክርክር ያስነሣው መሬት ለተጠሪ እንዲመለስለት የተወሰነው መሬቱ የተጠሪ ስለመሆኑ በአግባቡ ተረጋግጦ መሆን አለመሆኑ በጭብጥነት ይዞ ከመረመረ በኋላ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሣኔ ሽሮ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 33(2) መሰረት በይዞታው ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የለውም ሲል ወስኗል፡፡ ይህ ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በሚል የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ክርክር ያስነሣውን መሬት በውርስ ያገኘው ስለመሆኑ በተረጋገጠበት ክስ የማቅረብ መብት የለውም ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ሲል ውሣኔውን ሽሮ የወረዳና የከፍተኛ ፍርድ ቤቶችን ውሣኔ ስላፀና አመልካች ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች ሚያዚያ 5ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው ተጠሪው ክሱን ያቀረበው በውክልና ሆኖ ክርክሩ እልባት ሣያገኝ የሞተ በመሆኑ የውክልና ስልጣኑ ወዲያውኑ ቀሪ ስለሚሆን ወራሽ ነኝ የሚለው ሰው ወራሽ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሣያቀርብ ክርክሩ እንዲቀጥል መደረጉ፣ ያቀረበው የይርጋ ዘመን መቃወሚ መታለፉ፣ ክርክር ያስነሣው መሬት ከ1992ዓ/ም ጀምሮ በአመልካች እጅ ሆኖ ቤቶች የተሰሩበት

ስለመሆኑ በተረጋገጠበትና የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1179፣ 1180፣ 1149 እና 1845 የሚደነግጉት ድንጋጌ ታልፎ 16 ቤቶች ፈርሰው ይዞታው ለተጠሪ እንዲለቀቅ መወሰኑ መሰረታዊ ነው ተብሎ እንዲታረምለት ተከራክሯል።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ይዞታ የተጠሪ ስለመሆኑ የተረጋገጠበትና አመልካች በይዞታው ላይ ያለው ንብረት በማንሣት ለተጠሪ እንዲለቅ የተወሰነበት አግባብነት ላይ ግራቀኙ ተከራክረውበት እንዲወሰን ታዟል።

የተጠሪ ተወካይ ነኝ ያሉት አቶ አብዱልቃድር ድጉማ በቁጥር 1904/2010 ግንቦት 21ቀን 2010ዓ/ም ቤጊ ወረዳ

ፍትህ ፅ/ቤ የፀደቀላቸውን ውክልና በማያያዝ አመልካች ባቀረበው የሰበር ክርክር ላይ በዝርዝር መልስ በመስጠት በጥቅሉ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ እንዲፃና ተከራክሯል፣ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቦ ክርክሩ ተጠናቋል።

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥና በዚህ ችሎት የቀረበውን ክርክር ነበር። ችሎቱም የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት መደምደሚያ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን ያለመሆኑ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ፍርድ ቤቶች ተገቢውን የሙግት አመራር ሂደት ተከትለው ውሣኔ የመስጠታቸውን ጉዳይ ሊመረመር የሚገባው ነጥብ መሆኑ ስላመነበት ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አንፃር መርምሯል።

እንደመረመረው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ተጠሪ የእኔ ነው በሚለው ይዞታው ላይ የተሰሩት 16 ቤቶች ፈርሰው ይዞታው እንዲለቀቅለት ያቀረበው ክስ ነው። ተጠሪ ባቀረበው ክስ አመልካች በተከሳሽነት ያልተጠቀሰ ቢሆንም አመልካች በክርክሩ መሣተፉ የግድ ነው በሚል ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 40(2) ድንጋጌ መሰረት በተከሣሽነት የገባ ነው። በጥቅሉ ከክርክሩ አመጣጥ ለክርክሩ መንስዔ በሆነው ይዞታ ላይ 16 ቤቶች መሰራታቸውን፣ እነዚህ ቤቶች የተለያዩ ወይም ራሣቸውን የቻሉ ቤቶች መሆናቸውን፣ ቤቶቹ የተሰሩበት ይዞታ የማን ነው የሚለው አከራካሪ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ ይዞታው በአሁኑ ጊዜ የገበያ አገልገሎት እየሰጠ መሆኑን መገንዘብ የተቻለ ሲሆን በእነዚህ ቤቶች የተለያዩ ሰዎች እየተገለገሉባቸው መሆኑ ይታመናል።

በሌላ በኩል አንድ ሰው በሌሎች ሰዎች ተይዞብኛል የሚለውን የማይንቀሳቀስ ንብረቱን ለማስለቀቅና ለመረከብ ክስ ባቀረበ ጊዜ በማናቸውም ምክንያትና ሁኔታ በንብረቱ ላይ ሰፍረው የሚገኙትን ሰዎች ሁሉ አጣምሮ መክሰስ የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 36(4) ይደረግጋል። የሕጉ ሀይለ-ቃል "በማናቸውም ምክንያትና ሁኔታ በንብረቱ ላይ ሰፍረው የሚገኙት ሰዎች" በሚል ሲደነገግ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የማይንቀሳቀስ ንብረት በባለሃብትነት ወይም ኪራይን ጨምሮ በማናቸውም መንገድ

በንብረቱ ላይ መብት አለን የሚሉ ሰዎችን የሚያካተት ሆኖ ነገር ግን በሚሰጠው ውሣኔ መብታቸው ወይም ጥቅማቸው ሊነካ የሚችሉ ሰዎችን ማለቱ እንደሆነ መገንዘብ ይገባል፡፡ የዚህ ድንጋጌ ዋና ዓላማም በያዙት ይዞታና ቤት ላይ በቀረበው ክርክር ተካፋይ ሣይሆኑ የሚሰጠው ውሣኔ መብታቸውንና ጥቅማቸው ወይም ግዴታቸው የሚጎዳ ሊሆን ይችላል ተብሎ በሕግ አውጪው በመታመኑ መሆኑ መገንዘብ ይገባል፡፡

ይህ ድንጋጌ የማይንቀሣቀስ ንበረትን አስለቅቆ ለመረከብ በቀረበ ክስ የሚፀና ውሣኔ ለመስጠት በማናቸውም ሁኔታ በንብረቱ ላይ የሰፈሩት ወይም መብትና ጥቅም አለን የሚሉት ሰዎች ሁሉ በክርክሩ ተሣታፊ መሆናቸው የግድ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በክርክሩ ውስጥ የግድ ተሳጣፊ መሆን የሚገባቸው ሰዎች በክሱ ውስጥ ባልተጨምሩ ጊዜ የከሣሽን ክስ ውድቅ ከማድረግ ይልቅ ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያዩት ወይም በተከራካሪ ወገኖች ጠያቂነት ያልተካተቱትን አስፈላጊ ሰዎች ወደ ክርክሩ በተከሣሽነት ወይም በከሳሽነት እንዲገቡ ትዕዛዝ መስጠት ክርክሩን ማስቀጠል የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 39(1) እና 40(2) ጣምራ ንባብ ያስገነዝባል፡፡ ይሁን እንጅ ተጠሪ የኔነው በሚለው ይዞታው ላይ የተሰሩት 16 ቤቶች ፈርሰው ይዞታው እንዲለቀቅለት ክስ ሲያቀርብ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሰረት በቤቶችና በይዞታው ላይ የሚገለገሉትን ወይም የሰፈሩትን ሰዎች ሁሉ በተከሣሽነት በማጣመር ክሱን አለማቅረቡን የክርክሩ አመጣጥ ያስገነዝባል፡፡ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 36(4) ድንጋጌ መሰረት ክሱን አዘጋጅቶ ባላቀረበ ጊዜ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 36(4)፣ 39(1) እና 40(2) መሰረት የስር ፍርድ ቤት አመልካችን ብቻ ሣይሆን ሌሎች በይዞታው ላይ ወይም/እና በይዞታው ላይ በተሰሩት ቤቶች መብት ወይም ጥቅም አለን የሚሉትን ሁሉንም ሰዎች በተከሣሽነት እንዲገቡ ትዕዛዝ መስጠት ይገባው ነበር፡፡

በዚህ መሰረት ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ የኔነው በሚለው ይዞታ ላይ የተሰሩት 16 ቤቶች ፈርሰው ይዞታው እንዲለቀቅለት እስከሆነ ድረስ ከላይ እንደተጠቀሰው በማናቸውም ምክንያትና ሁኔታ በንብረቱ ላይ ሰፍረው የሚገኙት ሰዎች በተከሣሽነት በማጣመር ክስ ያላቀረበ ቢሆንም እነዚህ ሰዎች በክርክሩ የግድ ተሣታፊ መሆን ስለሚገባቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 40(2) መሰረት ፍርድ ቤቱ ራሱ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ ሰጥቶ ጉዳዩን መመርመር ሲገባው አመልካች ብቻ በተከሣሽነት እንዲገባ አድርጎ ክርክሩን ማስቀጠሉ ተገቢውን የሙግት አመራር ሂደትን ያለተከተለ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ውሣኔ

1) የቤገ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15823 የካቲት 9ቀን 2012ዓ/ም፣ የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 43848 ታሕሣስ 6ቀን 2013ዓ/ም፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 224612 የካቲት 16ቀን 2013ዓ/ምና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 335735 መጋቢት 21ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጧቸውን ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ሽረናል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2) የቤጊ ወረዳ ፍርድ ቤት በውሣኔ የዘጋውን መዝገብ ቁጥር 15823 እንደገና በማንቀሣቀስ ተጠሪ ላቀረበው ክስ ምክንያት በሆነው ይዞታ ላይ በማናቸውም መንግድ ሰፍረው የሚገኙትን ሰዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 36(4) እና 40(2) ድንጋጌ መሰረት በተከሣሽነት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ትዕዛዝ በመስጠት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የመሰለውን እንዲወስን ክርክሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341 መሰረት ተመልሶለታል፡፡

3) ይህ ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የዬራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ እልባት ያገኘ በመሆኑ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-205675

ቀን፡-30/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ጀማል ሹራቤ- ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጀማል አቤ- አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ አመልካች DLA መከስከሻ ማሽን ባለ 32 ምጣድ የሆነ ለተጠሪ ሊሸጥለት ከተስማማ በኋላ እና ብሩን ከተቀበለ በኋላ ተጠሪን በሀሰተኛ ክስ በመክሰስ ማሽኑን መልሶ በመውሰድ ቢያንስ የ90 ቀናት ጥቅም በቀን በብር 4,000.00 ሒሳብ የክስክሶ ስራ እና ዘርን አፈር ማልበስ ሰርቶ የሚያስገኘውንና በአጠቃላይ ብር 360,000.00 ያሰጣኝ ስለሆነ ወጪ እና ኪሳራን ጨምሮ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበውን ክስ መነሻ ያደረገ ሲሆን አመልካች በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበረ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበር፡፡

ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ አመልካች በቀን 17/09/2008 ዓም በተፃፈ ስምምነት DLA መከስከሻ ማሽን ባለ 32 ምጣድ የሆነ ባሌ ዞን ደሎ ሳቡር ጎበርባጀ የሚባል ቦታ በከድር ሁሴን ካምፕ ውስጥ የሚገኘውን በብር 200,000.00 በተወካዬ በአቶ ሁሴን አቤ አማካኝነት

ሊሸጡልኝ በሽያጭ ዋጋው ላይ በስልክ ተስማምተን፣ከዚህ ውስጥ ብር 100,000.00 በዚሁ በአቶ ሁሴን አቤ በኩል በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሳጉሬ ቅርንጫፍ በሒሳብ ቁጥሩ የገባለት ሲሆን ከቀሪው ገንዘብ ውስጥ ብር 50,000.00 ከኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ በአቶ ከድር ገለቶ ስም በወጣው ቼክ ታዞለት አመልካች ቼኩን አራዳ ቅርንጫፍ መንዝሮ ይህን ገንዘብ ወስዷል፡፡ ከዚህ በኋላ በማሽኑ የግዥ እና የሽያጭ ውል ላይ እንዲፈርም ሲጠየቅ ምክንያትና ሀሰተኛ ምስክር በማቀናጀት "ተጠሪ ይህን ማሽን የሰሌዳ ቁጥሩ 3-29812 ኦሮ በሆነ አይሱዙ መኪና ባሌ ዞን ደሎ ሰብሮ ወረዳ እንዲያደርስልኝ ከአዳማ ወረዳ አዱላለ ሐጤ ሃሮሬቲ ቀበሌ ቻይና ሲሚንቶ ፋብሪካ ከሚባል ቦታ በአደራ ሲሰጠው እምነት በማጉደል ወደ አርሲ ዞን ሳጉሬ ወረዳ አስመልጧል" በማለት በአዳማ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት አዋሽ መልካሳ ጣቢያ በቀን 01/11/2008 ዓም አመልክቶ እኔ ገዝቼ እጄ ያስገባሁትን ማሽን አስይዞ በማስመጣት በኢግዚቢትነት እንዲያዝ አደርጎ በወንጀል ድርጊት ንብረቱ ከእጁ መውጣቱን በመግለጽ ጥቅምት ወር 2009 ዓ.ም ጉዳዩን በፖሊስ ከተጣራ በኋላ ማሽኑን ወስዶታል፡፡ስለሆነም መከስከሻውን በአይነት እንዲመልስልኝ፣ አመልካች ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የመከስከሻ ማሽን አስይዞ በእጁ በማስገባት የእርሻ ስራ ሰርቶ የሚያስገኘውን ገቢ ከሐምሌ 1/2008 ላይ ጀምሮ እስከ መስከረም 15 ቀን 2009 ዓም ድረስ ባሌ ዞን ውስጥ፣ ከመጋቢት 1 ቀን 2009 ላይ ጀምሮ እስከ ሚያዝያ 10 ቀን 2009 ዓም ቦረና ዞን ውስጥ እና ይህ ክስ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ቢያንስ የ90 ቀናት ጊዜ በቀን ብር 4,000.00 ሒሳብ የክስክሶ ስራ እና ዘርን አፈር ማልበስ ሰርቶ የሚያስገኘውን በአጠቃላይ ብር 360,000.00 ያሰጣኝ ስለሆነ ወጪ እና ኪሳራን ጨምሮ እንዲከፍለኝ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካችም በሰጠው መልስ ገንዘብ በባንክ በኩል በአቶ ሁሴን አቤ ስም ብር 100,000.00 እና በአቶ ከድር ገለቶ ስም ብር 50,000.00 ገቢ ሆኖለት ወስዷል የተባለው የቀረበው ክስ ይህ ገንዘብ ለዚህ ማሽን ግዥ እና ሽያጭ ይሁን አይሁን የሚገልጽ ነገር የሌለ ስለሆነ በዚህ ላይ ተመስርቶ በአመልካች የቀረበብኝ ክስ በሕግ ፊት ተቀባይነት የለውም፡፡ተጠሪ የሚለው እውነት ቢሆን ኖሮ ይህንን ገንዘብ ተጠሪ በሌላ ሰው በኩል ሳይሆን በራሱ ስም ለምን ይከፍለኝ የነበረ ሲሆን ይህ አለመሆኑ የሚያሳየው ተጠሪ በአቋራጭ መንገድ ለመበልፀግ የሚፈልግ መሆኑን ስለሆነ ይህንን ክስ ሊያቀርብ ችሎታ የለውም ተብሎ ክሱ ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ባቀረቡት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስም ተጠሪ አከራካሪውን መከስከሻ በሰሌዳ ቁጥር 3-29812 ኦሮ መኪና ባሌ ለማጓጓዝ በ17/09/2008 ዓም ተረክቦ በመሰወር በፖሊስ ክትትል በ14/02/2009 ኣም ከ152 ቀናት በኋላ የተያዘ መሆኑን በመጥቀስ በቀን ተከራይቶ የሚያስገኘውን ብር 2,500.00 ሂሳብ የ152 ቀናት ብር 380,000.00፣ለጭነት የወሰደውን ብር 6,000.00 እና መከስከሻውን መልሶ አዳማ ለማውጣት የተከፈለውን ብር 3,300,00 በድምሩ 389,300.00 ከ9% ወለድ ጋር እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪ በሰጡት መልስም አከራካሪውን መከስከሻ ከአመልካች ገዝተው ከመረከብ ውጪ እንደ አመልካች ክርክር ለማጓጓዝ ያልተረከቡ መሆኑን፤መከስከሻውም በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሰረት ንብረታቸው መሆኑ ተረጋግጦ የተወሰነ መሆኑን ገልፀው ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ይህንን ተከትሎ በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ አመልካች ይህንን ዕቃ ከሸጠልኝ በኋላ በመያዙ እና በማስያዙ ምክንያት ቀርቶብኛል ብሎ ያቀረበውን ጥያቄ አስመልክቶ አመልካች ይህንን ዕቃ ለተጠሪ እንዳልሸጠ እና እምነት አጉድሎ ያስቀረበት መሆኑን በማንሳት ከመከራከር ውጪ በዚህ አግባብ አለማስረዳቱን ፤ከዚህ ይልቅ ተጠሪ አከራካሪውን መከስከሻ በግዢ ውል አግባብ የተረከበ መሆኑን በምስክሮቹና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ የተረጋገጠ መሆኑን በመጥቀስ የአመልካችን የክፍያ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ አመልካች ክርክር የተነሳበትን DLA የመከስከሻ ዕቃ ምጣድ ለተጠሪ በዓይነት ይመልስለት፤ይህ ዕቃ በዓይነት ሊመለስ የማይችል ሆኖ ከተገኘ አመልካች ለዚህ ዕቃ ዋጋ ውስጥ የተከፈለውን ብር 150,000.00/አንድ መቶ ሃምሳ ሺ/ ለተጠሪ መልሶ ይክፈል፤ ከዚህ ሌላም አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን ዕቃ እምነት በማጉደል አሸሽቶብኛል በሚል ምክንያት እንዳይጠቀምበት በማድረጉ ተጠሪ የቀረበትን ገቢ ብር 360,000/ሶስት መቶ ስልሳ ሺ/ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔም በግራ ቀኙ መሃል የሽያጭ ውል መኖሩ አልተረጋገጠም በማለት ምክንያቱ ባይታወቅም ተጠሪ ለአመልካች በድምሩ ብር 150,000.00 ያስተላለፉ መሆኑ ስለተረጋገጠ እንዲሁም ተጠሪ ማሽኑን በመውሰድ 152 ቀናት ስላቆዩ የተቋረጠ ገቢ ብር 182,400.00 ስለሚመጣ ተጠሪ በልዩነት የመጣውን ብር 32,400.00 ለአመልካች ይክፈሉ በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር የወሰነ ሲሆን ይህ ውሳኔም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰሚ ችሎት ፀንቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔም አከራካሪው መከስከሻ ወደ ተጠሪ በሽያጭ መተላለፉ በስር ፍርድ ቤት በቀረቡት ማስረጃዎች ተረጋግጦ እያለ በግራ ቀኙ መሃል የሽያጭ ውል መኖሩ አልተረጋገጠም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሽሮ አከራካሪው ማሽን የተጠሪ መሆኑ ስለተረጋገጠ አመልካች በአይነት እንዲመልሱ ፤በአይነት መመለስ ካልቻሉ የተከፈለውን ገንዘብ ብር 150,000.00 አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ የወሰነ ሲሆን የአመልካችን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውድቅ አድርጎ የተጠሪን የተቋረጠ ጥቅም ዳኝነት ጥያቄ በተመለከተ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተመርምሮ እልባት ያልተሰጠው መሆኑን መነሻ በማድረግ ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩን መልሶታል፡፡

ጉዳዩ በዚህ አግባብ የተመለሰለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ማስረጃ ሰምቶና አጣርቶ በሰጠው ውሳኔም የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ተጠሪ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የባለንብረትነት መብት አለው ተብሎ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መወሰኑን ፤ባደረገው ማጣራትም መከስከሻው ብቻ በወር ብር 65,000.00 ሊከራይ እንደሚችል የተገለፀለት መሆኑን ጠቅሶ አመልካች መከስከሻው በፖሊስ አማካኝነት እጁ ከገባበት ቀን ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ያለውን የ90 ቀን ገቢ በወር ብር 55,000.00/ሃምሳ አምስት ሺ/ ታስቦ የ3 ወር/የ90/ ቀን አመልካች ለተጠሪ ብር 165,000.00/አንድ መቶ ስልሳ አምስት ሺ/ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምስራቅ ቋሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የለውም በማለት የሰበር አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ማሽን ከየካቲት 27/06/2009 ዓም በፊት በፖሊስ እጅ ነበር፤ማሽኑ በእኔ እጅ እንዳልቆየ እየታወቀ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ዐ/ሕግ በእግዚቢትነት ይዞ ፖሊስ ዘንድ የቆየበትን ወቅት ጨምሮ አመልካች እንዲከፍል ብሎ መወሰኑ የሕግ አግባብነት የለውም፡፡በተጨማሪም አንድን በወንጀል የተያዘ ክስ ጉዳዩ ውድቅ ቢደረግ እንኳን ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩትን ወጪና ኪሳራን በተመለከተ የሀገራችን ሕግ ተጠያቂ አያደርግም፡፡ይህ ሁሉ ሆኖ ሳለ ለክሱ መነሻ የሆነው መከስከሻ ማሽን በኤግዚቢትነት ተይዞ በፖሊስ ዘንድ የቆየበትን ጊዜ አመልካች ጥቅም እንዳገኘሁ ታስቦ እንዲከፍል መወሰኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተመሳሳይ የሕግ ትርጉም በቅጽ.19 በሰ/መ/ቁ.100651 ላይ የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት ያላደረገ በመሆኑ የሰጡት ውሳኔዎች እንዲሻርልኝ እና ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ማሽንም ለብቻው ሰርቶ ገቢ የማያስገኝና ተጠሪ ሰርቼበት አገኝ የነበረው ገቢ ቀርቶብኛል ያለበትም መንገድ በቂ ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ ጉዳዩ የሚመለከታቸው መስሪያ ቤትም በሰነድ አስደግፌው ያቀረቡትን ሪፖርት መሰረት በማድረግ ተጣርቶ ፍትሃዊ የሆነ ውሳኔ እንዲሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የክርክር መነሻ የሆነው የመከስከሻ ማሽን ለብቻው ሊከራይ የሚችል መሆን አለመሆኑ፤መጋቢትና ሚያዝያ 2008 ዓ.ም የተቋረጠው ገቢ በተመለከተ ከጠቅላይ ፍርድ ቤት በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት አመልካች ባልተገኘበት ተጣርቶ የቀረበበትን አግባብ ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር አድርገዋል፡፡

የአሁን አመልካች ኤግዚቢት የሆነውን የአፈር መከስከሻ ፖሊስ ጣቢያው ማስቀመጫ ቦታ ማጣቱን አይቶ በተፈለገ ጊዜ ለማቅረብ አመልክቶ ከፖሊስ የምርመራ መዝገብ ላይ ዋስትና ፈርሞ በቀን 01/11/2008 ዓም ከፖሊስ እጅ ከወሰደ በኋላ የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በወንጀል መ/ቁ 97878 በቀን 27/06/2009 ዓም በሰጠው ውሳኔ ክሱ ከመቅረቡ በፊት ለአሁን አመልካች ተሰጥቶ በፖሊስ እጅ ላልነበረ መከስከሻ ኤግዚቢት ለአመልካች ይመለስ ብሎ ትዕዛዝ ቢሰጥም ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 25915 በቀን 01/7/2009 ዓም በ4 ቀን ልዩነት የስር

ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሮ መከስከሻ ለተጠሪ እንዲመለስ ታዞ ትዕዛዙ በአዳማ ወረዳ ፖሊስ በኩል እንዲፈፀም ሲታዘዝ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በፊት ቀድሞ መወሰዱንና ለመመለስ ፈቃደኛ አለመሆኑን በደብዳቤ ቁጥር PAA/787/09 ተገልጿል፡፡

ስለዚህ መከስከሻውን እየሰራሁበት ሰኔ 30/2008 ዓም በአመልካች የሀሰት ክስ ምክንያት ከእጄ አስወስዶ በ2ኛው ቀን ተረክቦ ሲገለገልበት ስለነበር በከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል መዝገብ ላይ እንዲመለስ ሲታዘዝ እምቢተኛ ሆኖ እና በዚህ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔም መሰረት በዓይነት ለመመለስ ሳይፈልግ ቀርቶ በአማራጭ ውሳኔው መሰረት ለሽያጩ ከእጄ የወሰደውን ብር 150,000፡00/አንድ መቶ ሃምሳ ሺ/ ብቻ መልሶ ያለ አግባብ ስለበለፀገበት መከስከሻውን በፖሊስ ጽ/ቤት ሳይሆን በአመልካች እጅ ስለነበረ ለታጠው ጥቅም ኃላፊ ነው መባሉ የስር ፍርድ ቤት የሕግ ስሕተት የለውም ተብሎ ሊፀና በማለት ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡በመሰረቱ የስር ፍርድ ቤቱ አከረካሪው መከስከሻ ማሽን ከጥቅምት ወር 2009 ዓም ጀምሮ ከፖሊስ እጅ ወጥቶ አመልካች እጅ የገባ መሆኑንና ተጠሪ ክስ እስኪያቀርቡ ድረስ በእጃቸው የነበረ ለመሆኑ የቀረበውን ክርክር አመልካች በግልፅ ክደው ያልተከራከሩ መሆኑን በመጥቀስ በግልፅ ክደው አለመከራከራቸው እንዳመኑ የሚያስቆጥር መሆኑን በመጥቀስ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚያሳይ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ይህንን ነጥብ መነሻ በማድረግ ከተቋረጠ ገቢ አንፃርም የድጋሉ እና ጥጆ ወረዳ እርሻ እና የተፈጥሮ ሀብት ፅ/ቤት መከስከሻው ያላቸውን ገበሬዎች እና ባለሙያዎችን በማነጋገር ማሽኑ ለብቻው ሊከራይ እንደሚችል የወር ገቢውም ብር 55,000.00 መሆኑን በመግለፅ የሰጠውን ምላሽ በመጥቀስ የተቋረጠ ገቢ አመልካች የዘጠና ቀናት ብር 165,000.00 ለተጠሪ እንዲከፍሉ በማለት ማስረጃን የመስማት የመመርመርና የመመዘን ስልጣኑን መሰረት በማድረግ የደረሰበት መደምደሚያ መሰረታዊውን የማስረጃ ምዘና መርህ ያደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 280899 በቀን 07/07/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተቋረጠ ገቢ አንፃር የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል አመልካች ለተጠሪ ብር 165,000.00/አንድ መቶ ስልሳ አምስት ሺህ ብር/ እንዲከፍሉ የሰጠው ውሳኔና ይህንን ውሳኔ በማፅናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.374478 መጋቢት 27 ቀን 2013 ዓም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንተዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2. በዚህ መዝገብ ተለዋጭ ትዕዛዝ እስኪደርሰው ድረስ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 36637 የተጀመረው አፈፃፀም ለጊዜው እንዲታገድ በቀን 06/08/2013 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>**ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**</u>

ሂ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-205633

ቀን፡- 26/02/2014ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ካሳው ጋረደው- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- እናኒ አያልነሀ- አልቀረቡም

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች በሚያዝያ 04 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 0329882 በመጋቢት 28 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የመሬት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ወሎ ዞን ሳይንት ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ በዚህ የሰበር ክርክር ያልተጠሩ ስማቸው በስር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ያልተጠቀሰ ግለሰብ 1ኛ እና 2ኛ፣4ኛ እና 5ኛ ተከሣሾች ፣የአሁን ተጠሪ ደግሞ 3ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የአሁን አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች በማረሚያ ቤት እያለሁ ተከሳሾች በከተማ ክልል ውስጥ የሚገኘውን አዋሳኙ በክሱ ላይ የተገለጸውን የሚች አባቴ የሆነውን መሬት የያዙበት መሆኑን ገልጸ ተከሳሾች ለቅቀው እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በሚል ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የስር 1ኛ ተከሳሽ በሰጠው መልስ፡- አመልካች በክሱ ላይ የጠቀሰው ይዞታ ከአመልካች አባት በ1988 ዓ.ም በህግ ፊት ቀርቦ በሚጸና የሽያጭ ውል በብር 600 /ስድስት መቶ/ ገዝቻለው፤ ይዞታውን ለ24 ዓመታት ይዤዋለሁ የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር መልስ፡- አመልካች ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፤ የተጠሪ ባለቤት ባዶ ቦታ ከእነ አትክልቱ ያለውን በ07/01/1983 ዓ.ም ከአመልካች አባት ከአቶ ጋረደው ተፈራ ገዝቶ በ1980 ዓ.ም ቤት ሰርተን ሲኖሩ ቆይተው በ1991 ዓ.ም ጋብቻቸው ሲፈርስ ቤት እና ቦታውን እኩል ተካፍለን ተጠሪ ድርሻዬን ይዤ እየተጠቀምኩ እገኛለሁ በማለት ተከራክራለች፡፡

4ኛ ተከሳሽ በሰጠው መልስ፡- ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የሳር አፊጅ ቤት በ1998 ዓ.ም በህግ ፊት በሚጸና ውል ከወ/ሮ እናኒ እሸቱ ገዝቼ አፍርሼ ባለ 55 ቆርቆሮ ቤት ሰርቻለሁ በማለት ተከራክሯል፡፡

5ኛ ተከሳሽ በሰጠው የተሻሻለ መልስ፡- ክሱ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000 መሰረት በ3 ዓመት ይርጋ ይታገዳል፤ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት እና ቦታ ልጄ ሽመልስ ግርማ ከአመልካች እንጀራ እናት ከተጠሪ በብር 60,000.00 ገዝቶ በላዩ ላይ የቆርቆሮ ቤት ሰርቶ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ይዞ መቆየቱን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ እና የሚመለከተው አካል እስከ ቦታው ድረስ በመሄድ አጣርቶ መግለጫ እንዲልክ ካደረገ በኋላ ክርክር ከተነሳበት ይዞታ በምስራቅ መኪና፣ በምዕራብ ቃኘው፣ በሰሜን መንገድ አዋሳኝ ውስጥ ቁመት 30 ሜትር ወርዱ 18 ሜትር የሆነ ቦታ የዘለቀ መርጊያ እና የግርማ ልጅ የሰሩት እንጂ የከሳሽ አባት የጋረደው ተፈራ ቦታ አለመሆኑ ተረጋግጧል፤በክሱ ውስጥ ከተጠቀሰው በአዋሳኝ ከነበረው ቦታ ወርዱ 16 ቁመቱ 16 ሜትር የሆነው የጋረደው ተፈራ እና የተጠሪ የጋራ ሀብት መሆኑ ተረጋግጧል፤ አቶ ጋረደው ተፈራ በ1983 ዓ.ም ለተጠሪ በስተምስራቅ በኩል ወርዱ 16 ሜትር ቁመቱ 8 ሜትር መሸጡ ተረጋግጧል፤ ተጠሪም ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ለ28 ዓመታት ቤት ሰርታበት መኖሯ ተረጋግጧል፤1ኛ ተከሳሽ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ በግዥ ውል መያዙ የተረጋገጠ በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት በዚህ ረገድ የቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም፡፡

ተጠሪ ከባለቤቷ ከጋረደው ተፈራ ጋር የተካፈለችውን ወርዱ 16 ሜትር ቁመሩ 9.5 ሜትር የሆነውን ለ4ኛ የስር ተከሳሽ መሸጧ ተረጋግጧል፤ አመልካች የሌላ ሰው ይዞታን ጭምር በማካተት ክስ ማቅረቡ፤ የተጠሪ ባለቤት አቶ ይበልጣል ከአመልካች አባት በውል መግዛቱን እና በኋላም ተጠሪ እና ባለቤቷ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቦታ በፍርድ ቤት መካፈላቸው ተረጋግጧል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች የጠየቀው የተጠሪን ድርሻ ሳይሆን በጠቅላላ መሬቱን ስለመሆኑ ተረጋግጧል፤ ተጠሪ በህይወት ያለች እና በስጦታ ለአመልካች ያላስተላለፈች በመሆኑ 4ኛ ተከሳሽም የአመልካችን አባት ድርሻ መያዙ ባልተረጋገጠበት ሊጠየቅ አይገባም፤ 5ኛ ተከሳሽ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ በግዥ ስለመያዙ ያልተረጋገጠ በመሆኑ የሚያስረክበው መሬት የለም፤ በመሆኑም 1ኛ የስር ተከሳሽ እና ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቦታ ለአመልካች ለቀው ያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤትም የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማጽናት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡ ተጠሪ በመቀጠል ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርባለች፡፡ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም ሟች አቶ ጋረደው ተፈራ በ1995 ዓ.ም መሞታቸው አላከራከረም፤ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት ከባለቤቷ ጋር በመግዛት ቤት ሰርተው ሲጠቀሙበት መቆየታቸውን ተረጋግጧል፤ ሟች አቶ ጋረደው ተፈራ ሀብቱን በሽያጭ ወደ ተጠሪ አስተላልፏል፤ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ በግዥ ባገኘችበት ወቅት የገጠር መሬት የነበረ በመሆኑ በሽያጭ እንዳታስተላልፍ በጊዜው በነበረው ህግ ግልጽ የሆነ ክልከላ ያልተደረገ እና ቤት የተሰራበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የሽያጭ ውሉ ህገወጥ ነው በማለት ተጠሪ እንድትለቅ መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በሚል ሽሮ ተጠሪ ቤት የሰራችበትን ቦታ ልትለቅ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቦታ እና ቤት የአመልካች ስለመሆኑ ተረጋግጧል፤ ተጠሪ ያቀረበችው የሽያጭ ውል ህገወጥ ስለመሆኑ ተረግጧል በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ ቦታውን በግዥ ግንኙነት ወቅት የገጠር መሬት በነበረው ህግ ግልጽ ክልከላ ያልተደረገበት በመሆኑ ተጠሪ መሬቱን ለአመልካች ልትለቅ አይገባም በማለት የወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ለክርክሩ መነሻ በሆነው ይዞታ ላይ ግብር ስለመክፈሉ አላስረዳም፤ አመልካች አባቱ ከመሞቱ በፊትም ሆነ ከሞተ በኋላ አልተቃወመም፤ የአመልካች የውርስ ጥያቄ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1000(1) እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 6 መ.ቁ. 20295 ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን ነው፤ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ይዞታ በአካባቢው ባህል እና ልማድ መሰረት መግዛቴ አመልካች አልካደም፤ ይህ ከሆነ ደግሞ የሽያጭ ውል መኖሩ ከታመነ በፍታብሔር ህግ 1723 መሰረት አለመፈጸሙ ፈራሽ እንደማያደርገው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 13 መ.ቁ. 36887 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠበት በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎ የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርከሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው አመልካች በስር ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረው ክስ ማረሚያ ቤት እያለሁ የአባቴ የሆነውን ይዞታ ይዘውብኛልና ለቅቀው ያስረክቡኝ በሚል ሲሆን የአሁን ተጠሪ በሰጠችው መልስ ከአመልካች አባት ገዝቸ ለ28 ዓመት የያዝኩት እንጂ ሌላ መሬት አልያዝኩም በማለት ተከራክራለች፡፡

ከአጠቃላይ ክርክሩ እና አጣሪ ችሎቱ ሊጣራ ይገባዋል ብሎ ከያዘው ጭብጥ አንፃር የሚያከራክረው መሬት በ1983 ዓ.ም. የተሸጠ ከመሆኑ አኳያ በጊዜው መሬት መሸጥ መለወጥ ካለመከልከሉ አኳያ ተመርምሮ የመወሰኑን አግባብነት በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው ነው፡፡

አዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 3/1 ስር በግልጽ የሚደነግገው የከተማ ቦታና ቤት የመንግሥት መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ያለ እና ያልተሻረ ሲሆን ከዛ ወዲህ የወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40/3 መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የሚያከራክረውን ይዞታ ከአመልካች አባት ገዝቻለሁ የሚሉት በ1983 ዓ.ም. በመሆኑ በዚህ ጊዜ በአጠቃላይ በአገሪቱ ባሉ ከተሞች የሚገኙ የከተማ ቤትና መሬት የመንግሥት ስለመሆኑ የታወጀ በመሆኑ ይህ አዋጅ ፀንቶ ባለበት መሬት መሸጥ መለወጥ አልተከለከለም ነበር በሚል የሚቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ከዛ ወዲህ የወጣው የኢ.ፌ.ድ.ሪ.ሕገ መንግሥት ከላይ እንደተገለፀው መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የመንግሥት እና የህዝብ ሀብት መሆኑን መደንገጉ ሲታይ አስቀድሞ የወጣው አዋጅ ቁጥር 47/67 የሚያጠናክር በመሆኑ መሬት በ1983 ዓ.ም. ሽያጭ አልተከለከለም በማለት የሚቀርበው ክርክር ተገቢ አይደለም፡፡

ሆኖም ግን ተጠሪ በ1983 ዓ.ም. የሚያከራክረውን መሬት ከሟች ሲገዙ አመልካች በዛን ጊዜ ማረሚያ ቤት መሆኑ ያልተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ማረሚያ ቤት ነበር ቢባል እንኳን የአመልካች አባት ከዚህ አለም በሞት የተለዩት በ1995 ዓ.ም. በመሆኑ፣ የሽያጭ ውሉ መኖሩን አባቱ ህይወታቸው እስኪያልፍ ድረስ ያልካዱ ከመሆኑም በላይ በይዞታው ላይ ተጠሪ አትክልት ሲተክሉና ቤት ሲገነቡ የተቃወማቸው ስለመኖሩ በስር ፍ/ቤት ያልተረጋገጠ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ቤቱና ቦታውን ተጠሪ ሊለቁ አይገባም ሲል የደረሰበት መደምደሚያ ህግን መሠረት ያደረገ እንጂ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሊባል የማይገባው በመሆኑ ውሣኔው ሊፀና ይገባል ብለን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 0329882 መጋቢት 28 ቀን 2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡

<u>መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

ሰ/መ/ቁ፡-205362

ቀን፡- 30/02/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ ዓለሜ ቦጋለ - ጠበቃ አቶ አለማየሁ ሻረው

ተጠሪዎች፡ 1ኛ. አቶ ታዬ(ብስራት) ቦጋለ

2ኛ. አቶ ሰለሞን ቦጋለ

3ኛ. ወ/ሮ ብርሃኔ ቦጋለ

4ኛ. ወ/ሮ ወሰኔ(ማህደር) ቦጋለ

5ኛ. ካሳሁን ቦጋለ

6ኛ. ወ/ሪት እታገኘ ቦጋለ

7ኛ. ህፃን ማክቤል መሰረት

(1ኛ–7ኛ ተጠሪዎች) የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ በሁከት ይወገድልኝ ክስ መነሻነት የተጀመረ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/08853 ላይ ታህሳስ 16/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በአሁን ከ1ኛ እስከ 4ኛ በተጠቀሱት ተጠሪዎች ላይ በቤንች ሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ጭብጥ ከወላጅ አባቴ በተደረገልኝ እና በዞኑ ፍትህ መምሪያ በተመዘገበ የስጦታ ውል በተላለፈልኝ ንብረት ላይ ሁከት የፈጠሩብኝ በመሆኑ ሁከቱ ተወግዶ ንብረቱን ለቀው ሊያስረክቡኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት ከ1ኛ እስከ 4ኛ ያሉ ተጠሪዎችም መልስ እና ከመልሳቸው ጋርም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ የመልሳቸው ይዘት ሁከት ተፈጠረበት የተባለው ንብረት የግራ ቀኛችን ወላጅ አባት የውርስ ሀብት እንጂ የአመልካችዋ ባለመሆኑ በንብረቱ ላይ የፈጠርነው ሁከት የለም፤ አመልካች ተደረገልኝ የምትለውንም የስጦታ ውል አናውቅም፤ የስጦታ ውሉ ተደረገ በተባለበት ጊዜም ወላጅ አባታችን በተስተካከለ የአእምሮ ሁኔታ ላይ ያልነበሩ በመሆኑ ውሉ ፈራሽ ነው የሚል ነው፡፡

የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ይዘት ደግሞ በዞኑ ፍትህ መምሪያ ፀድቋል የተባለው የስጦታ ውል ከአመልካች ውጭ ያሉትን ስድስት የሟች ወደታች የሚቆጠሩ ወራሾችን ከውርስ የሚነቅል በመሆኑ እና የስጦታ ውሉም በተደረገበት ጊዜ ስጦታ አድራጊው በትክክለኛ የአእምሮ ሁኔታ ላይ ያልነበሩ በመሆኑ ውሉ ፈራሽ ነው ሊባል ይገባል የሚል እና የሟች ሌላ የውርስ ሀብት ጠቅሶ በፍርድ ቤት ውሳኔ ለመካፈል የሚጠይቅ ነው፡፡ ከዚሁ ክስ ጋርም የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱን አስመልክቶ ከ5ኛ እስከ 7ኛ ያሉት ተጠሪዎች በክርክሩ እንዲጨመሩላቸው ጠይቀዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ከ5ኛ እስከ 7ኛ ያሉት ተጠሪዎች በጣልቃ ገብነት የክርክሩ አካል ተደርገው ከ1ኛ እስከ 4ኛ ከተጠቀሱት ተጠሪዎች ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያለው መከራከሪያ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ግራ ቀኙን ጨምሮ የሟች ወራሾች ስምንት ልጆች መሆናቸውን፤ ሁከት ተፈጠረበት ተብሎ የተጠቀሰው ንብረትም ለአሁን አመልካች በስጦታ የተላለፈ መሆኑን፤ ለአመልካች የተደረገው ስጦታ አጠቃላይ ካለው የውርስ ሀብት ጋር ሲነፃፀር ቀሪ ወደታች የሚቆጠሩ የሟች ወራሾችን ከውርስ የሚነቅል መሆኑን፤ ሟች ከአመልካች ውጭ ያሉትን ቀሪ ወራሾችን ከውርስ ለመንቀል የጠቀሱት ምክንያት “አልጠየቁኝም፤ አላሳከሙኝም፤ ከባለቤቴ ጋር አለያይተዉኛል” የሚል መሆኑን፤ በተናዛዡ የተጠቀሰው ምክንያት የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾችን ከውርስ ለመንቀል በቂ ምክንያት እንዳልሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/57836 እና 55648 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠ መሆኑን ጠቅሶ የስጦታ ውሉ ፈራሽ ነው፤ ውሉ ፈራሽ ከሆነ ደግሞ ሁከት ተፈጠረበት የተባለው ንብረት የግራ ቀኙ ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት በመሆኑ ሁከት ተፈጥሮበታል ሊባል አይቻልም፤ ግራ ቀኙ ሊከፋፈሉት የሚገባ ሌላ የውርስ ሀብት ስለመኖሩ አልተረጋገጠም በማለት የሁከት ክሱን ውድቅ አድርጎ ግራ ቀኙ ንብረቱን እኩል እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህንኑ ውሳኔን በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች መጋቢት 28/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ያቀረቡት የሁከት ይወገድልኝ አቤቱታ ውድቅ የተደረገበት፣ በስጦታ የተሰጣቸው ንብረቶችም ከውርስ የነቀለ ነው በሚል የስጦታ ውል እንዲፈርስ የተወሰነበት አግባብነትና የሰ/መ/ቁ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

57836 እና 55648 ለጉዳዩ ያለው ተፈፃሚነት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገበዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንደተመረመረውም አመልካች ክስ ያቀረቡት በስጦታ በተላለፈልኝ የግል ንብረቴ ላይ ሁከት ተፈጥሯ በሚል ነው፡፡ በዚሁ ጉዳይ ተከሳሽ የነበሩት አካላት ደግሞ ንብረቱ ላይ የተደረገ ስጦታ አለመኖሩ እና ንብረቱም የወራሾች የጋራ ሀብት መሆኑን ገልፀው የተፈጠረ ሁከት የለም ብለዋል፡፡ ከዚሁ ጋርም በንብረቱ ላይ ተደርጓል የተባለው የስጦታ ውል ህጋዊ አይደለም የሚሉበትን ምክንያት ጠቅሰው እንዲሻርላቸው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡

በዚሁ ክርክር መነሻነት ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣኑ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ክስ በቀረበበት ንብረት ላይ የተፈጠረ ሁከት አለ ወይስ የለም? ሁከት ተፈጠረበት የተባለው ንብረትስ የአመልካች ነው ወይስ የግራ ቀኙ የውርስ ሃብት ነው? በንብረቱ ላይ ተደረገ የተባለው የስጦታ ውል ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? ግራ ቀኙ ሊካፈሉት የሚገባ ሌላ የውርስ ሀብት አለ ወይስ የለም? የሚሉትን ጭብጦች መስርቶ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን መርምሯል፡፡ በውጤቱም ለክሱ ምክንያት በሆነው ንብረት ላይ ተደርጓል የተባለው የስጦታ ውል ከተቀረው የሟች የውርስ ሀብት ጋር ሲነፃፀር ሌሎች ወራሾችን ከውርስ የሚነቅል መሆኑን፣ በዚህ መልኩ ወደታች የሚቆጠሩ ወራሾችን ከውርስ ለመንቀል በስጦታ አድራጊ የተጠቀሰው ምክንያትም ከህግ አንፃር ሲመረመር በቂ የሚባል አይደለም ተብሎ ውድቅ ተደርጎ ንብረቱ የግራ ቀኙ የጋራ የውርስ ሀብት ነው ተብሏል፡፡ በዚሁ መነሻነትም ሁከት ተፈጠረ የተባለው የጋራ በሆነ የውርስ ሀብት ላይ ነው በሚል የአመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ ውድቅ ተደርጎ ግራ ቀኙ ንብረቱን በጋራ እንዲካፈሉ ተወስኗል፡፡

እንግዲህ ከስር ፍርድ ቤት የፍርድ ትችት በግልፅ መረዳት እንደሚቻለው የአመልካች የሁከት ይወገድልኝ ክስ ውድቅ የተደረገው ክስ የቀረበበት ንብረት የግል ይዞታቸው ሳይሆን የግራ ቀኙ የውርስ ሀብት ነው በሚል መነሻነት ነው፡፡ ይህ ሊባል የተቻለው ደግሞ በንብረቱ ላይ ተደርጓል የተባለው የስጦታ ውል ውድቅ ተደርጎ ነው፡፡ የስጦታ ውሉ ውድቅ የተደረገውም ከኑዛዜ አድራጊው ቀሪ ሀብት ጋር ሲነፃር በስጦታ የተላለፈው ንብረት ሌሎች ተወላጆችን ከውርስ የሚነቅል መሆኑ ተረጋግጧል በሚል ነው፡፡

በእርግጥ አንድ አውራሽ/ተናዛዥ/ በውርስ ሀብት ላይ ባደረገው የኑዛዜ ስጦታ ሌላኛው ወራሽ በውርስ ሊደርሰው ከሚገባው ድርሻ ከሩብ በላይ ጉዳት እንዲደርስበት ካደረገ በውጤት ደረጃ ስጦታ ያለተደረገለትን ሌላኛውን ወራሽ ከውርስ መንቀል መሆኑን፣ ወደታች የሚቆጠር ተወላጅን ከውርስ ለመንቀል ተናዛዡ የሰጠው ምክንያት በቂ መሆን ያለመሆኑ በዳኞች ሊመረመር የሚችል መሆኑን፣ በዚሁ መሰረት "ታምሜ አልራዳኝም፣ አላስታመመኝም ወይም አልጠየቀኝም" በሚል በተናዛዡ የሚጠቀስ ምክንያት ተወላጅን በኑዛዜ ከውርስ ለመንቀል የሚያስችል በቂ ምክንያት እንዳልሆነ ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 912፣ 915፣ 938፣ 939፣ 1047 እና 1123 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንኑ ጉዳይ አስመልክቶም በማስቀረቢያ ነጥቡ ውስጥ በተጠቀሱ የመዝገብ ቁጥሮች እና በሌሎች በርካታ መዝገቡት ላይ ይኸው ችሎ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ለክሱ ምክንያት በሆነው ንብረት ላይ በግራ ቀኙ አውራሽ ለአሁን አመልካች ተደርጓል የተባለው የኑዛዜ ስጦታ ከተቀረው የውርስ ሀብት ጋር ሲነፃፀር ሌሎች ወደታች የሚቆጠሩ

ተወላጆችን ከውርስ የሚነቅል ስለመሆኑ ማስረጃን ፍሬ ነገርን የመመርመር እና የመመዘን የዳኝነት ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከተረጋገጠ ለክሱ መነሻ በሆነው ንብረት ላይ የተደረገው ስጦታ ውድቅ የሚደረግ በመሆኑ ንብረቱ የግራ ቀኙ የጋራ የውርስ ሀብት ይሆናል፡፡ ንብረቱ የግራ ቀኙ የጋራ የውርስ ሃብት ከሆነ ደግሞ የጋራ ባለሀብቶች አንዱ በሌላኛው ላይ ንብረቱን በተመለከተ ሁከት ፈጥሯል የሚባል አይደለም፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ ህግን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት መሰረታ የህግ ስህተት ባለመኖሩ የአመልካች መከራከሪያ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/08853 ላይ ታህሳስ 16/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት የሰጠውን የመጨረሻ ውሰኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሂ/መ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ፡-205297

ቀን፡-30/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ፡- ዓ/ህግ ቴዎድሮስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- እያሱ ያየህ ባየህ - አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 197256 ጥር 19 ቀን 2013 ዓ.ም የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ያስተላለፈውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመሻር ተጠሪን በነጻ በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪ ላይ በስር ፍርድ ቤት አቅርቦት የነበረው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 543/2 ድንጋጌን በመተላለፍ በቀን 24/09/2010 ዓ.ም ከጠዋቱ 1፡45 ሰዓት የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-01771 ኢት የሆነ ተሽከርካሪ ይዞ ከሳህሊተ ምህረት ቤተክርስቲያን ወደ ጃክሮስ አቅጣጫ በሚያሽከረክርበት ወቅት ሳህሊተ ምህረት ቤተክርስቲን አካባቢ ሲደርስ የመንገዱን እና የእግረኞቹን ሁኔታ በማየት ጥንቃቄ አድርጎ ማሽከርከረ ሲገባው ይህን ባለማድረግ መንገዱን ከግራ ወደ ቀኝ ሲያቋርጥ የነበረውን ሟች ማቴዎስ ሀናቆ የተባለውን ግለሰብ በተሸከርካሪው የፊት ለፊት የግራ አካል በመግጨት ጥሎት ሟችም በግጭቱ ምክንያት

በጭንቅላቱ ላይ በደረሰ ጉዳት ሕይወቱ ያለፈ በመሆኑ በፈጸመው በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

ክሱ ለተጠሪ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በኂላ ድርጊቱን መፈጸሙን ሆኖም ጥፋተኛ አለመሆኑን በመግለጽ ቃሉን ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም የዓቃቤሕግን ማስረጃ ከሰማ በኂላ ዓቃቤሕግ ባቀረበው ማስረጃ ተጠሪ የተከሰሰበትን ወንጀል ስለመፈጸሙ በበቂ እና አሳማኝ በሆነ ሁኔታ አስረድቷል በማለት ተጠሪ ክሱን እንዲከላከል ብይን ሰጥቷል፡፡ ተጠሪም መከላከያ ምስክሮቹን አስቀርቦ አሰምቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ ባቀረበው መከላከያ ማስረጃ የቀረበበትን ክስ አልተከላከለም በማለት ጥፋተኛ ብሎ በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ቀላል እስራት እና በብር 1,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ የወሰነ ሲሆን ቅጣት እንዲገደብ የቀረበውን ጥያቄ በሚመለከት ደግሞ የትራፊክ አደጋ እንደሐገር እያደረሰ ካለው ጉዳት አንጻር ተቀባይነት አላገኘም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኂላ ሟች በተጠሪ መኪና ከመገጨቱ በፊት ተጠሪ ሟችን አይቶት ከሁለት ጊዜ በላይ ክላክስ ያደረገለት መሆኑ፤ መኪናውም ፍጥነት ያልነበረው ይልቁንም በመቆም እና በእንቅስቃሴ መካከል የነበረ ስለመሆኑ እንዲሁም ሟች ፊቱን ከመኪናው ወደ ተቃራኒ ኣጣጫ በማዞር ወደ ኂላ ወደ መኪናው መጥቶ መጋጨቱ መመስከሩ ሲታይ ተጠሪ በሚያሽከረክረው መኪና ሟችን ሊገጨው እንደሚችል እያወቀ ይህ ክስተት አይደርስም በሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን በሟች ላይ ጉዳት ደርሷል ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፤ በተመሳሳይ ሟች እንደሚገጨው ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ሟች ላይ ጉዳት ደርሷል ለማለት የሚያስችልም አይደለም፤ ይልቁንም መኪናው ፍጥነት አለመኖሩ እና ክላክስም ማድረጉ የደረሰውን አደጋ ለማስቀረት ሙያው በሚፈቅደው መሠረት ጥረት ማድረጉን የሚስገነዝብ ነው፤ በመሆኑም በማስረጃ የተረጋገጠው ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23/2፤ 24፤ 59/1፤ 543/2 የተመለከቱትን በሚያሟላ መልኩ የተፈጸመ የቸልተኝነት የወንጀል ድርጊት ነው ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም በማለት በስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጠውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመሻር ተጠሪን በነጻ በማሰናበት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም መጋቢት 24 ቀን 2013 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም ፤ ሟች ሳያይ ወደ መኪናው መግባቱ ለአደጋው አስተዋጽኦ አለው ሊባል ከሚችል በቀር ሌሎች ማስረጃዎችን በተለይም የተጠሪን ቸልተኝነት መኪናውን ፍሬን ይዞ አለማቆሙ መሆኑን የሚያሳየውን የባለሙያ ምስክርነት ወደ ጎን በመተው የዓቃቤሕግ ምስክሮች ሟች መጥቶ ተጋጨ ብለዋል በሚል ለብቻው መዝኖ ክላክስ በማድረጉ ብቻ ሟችን ለማዳን ጥረት ስላደረገ ቸልተኝነት የለም መባሉ አግባብ አይደለም፤ ዓቃቤሕግ ተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ እንደክስ አመሰራረቱ ያስረዳ እና ተጠሪም ይህንን በማስረጃዎቹ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ያላስተባበለ በመሆኑ ተጠሪን በነጻ በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪን ከቀረበበት ክስ በነጻ የማሰናበቱን አግባብነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 89676 ከሰጠው የማስረጃ ምዘና መሠረታዊ መርህ አንጻር ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጡት መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የዓቃቤሕግ ሁለት ምስክሮች ተጠሪ መኪናውን ከቆመበት አስነስቶ በዝቅተኛ ፍጥነት እየነዳ ሳለ ሟች በመኪናው በስተግራ ወደ ኋላው ዙሮ እያወራ ዘሎ ሲገባበት ተጠሪ የመኪና ክላክስ እያደረገ መኪናውን ለማቆም በመታገል ላይ እያለ ሟች ከመኪናው ጋር በመጋጨት እንደወደቀ መስክረዋል፤ 3ኛው የዓቃቤሕግ ምስክር አደጋው ሲፈጠር በቦታው ላይ ያልነበረ እና የሙያ ምስክር እንደሆነ በመግለጽ ተጠሪ ሟችን በሆነ መንገድ ሊያተርፈው ይችል ነበር ከማለት በቀር በዚህ ርቀት ተጠሪ ሟችን ሊያተርፍ የሚችልበትን መንገድ አላሳየም፤ የተጠሪ መከላከያ ምስክሮች ክላክስ እያሰማሁ መኪናውን በማቆም ላይ እያለሁ ሟች ከመኪናው ፊት ለፊት በግራ በኩል ተጋጭቶ መውደቁን መስክረዋል፤ ተጠሪ ማንበብ ስለማልችል በአደጋ ፕላኑ ላይ መፈረሜ ድርጊቱን መፈጸሜን የማያሳይ በመሆኑ በስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪን በነጻ በማሰናበት የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተጠሪን በነጻ በማሰናበት የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም ይገባል በማለት የሚከራከረው ተጠሪ ክላክስ ማድረጉ ብቻ ሟችን ለማዳን ጥረት አድርጓል አያስብልም፤ ተጠሪ ሌላ እርምጃ በመውሰድ ሟችን ከሞት ለመታደግ ሲችል ተገቢውን ጥረት ያላደረገ በመሆኑ በወቅቱ ቸልተኝነት የነበረው መሆኑን የሚያሳይ ነው በማለት ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በዝቅተኛ ፍጥነት እየነዳሁ ሳለ ሟች በመኪናው በስተግራ ወደ ኋላው ዙሮ እያወራ ዘሎ የገባብኝ እና ክላክስ በማድረግ መኪናውን ለማቆም በመታገል ላይ የነበርኩ በመሆኑ ጥፋተኛ ልባል አይገባም በማለት የሚከራከር ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ሊወስደው ይገባው የነበረውን እርምጃ ሳይወስድ በመቅረቱ ምክንያት የሟችን ሕይወት እንዲያልፍ አድርጓል? ወይስ አላደረገም? የሚለው በዚህ ችሎት ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ነው፡፡

የወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል አንቀጽ 57 ለድርጊቱ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት አንድ ወንጀል ካላደረገ በቀር በወንጀል ጥፋተኛ አይሆንም በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 59

ማንም ሰው በቸልተኝነት የወንጀል ተግባር አድርጓል የሚባለው ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም የሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን ወይም ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈጸመ እንደሆነ ነው በማለት ተመልክቷል፡፡ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው በአንድ ድርጊት ምክንያት አንድን ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ነው ለማለት ከሳሽ የሆነው ዓቃቤ ሕግ ድርጊቱ የተፈፀመው ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት መሆኑን ነው፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ የተከሰሰበት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 ድንጋጌ በቸልተኝነት ሰውን ስለመግደል የሚመለከት ሲሆን የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (2) የሌላ ሰውን ሕይወት፣ ጤንነት ወይም ደህንነት የመጠበቅ የሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት እንደ ሕክምና ባለሙያ ወይም አሽከርካሪ ያለ ሰው በቸልተኛነት ሰውን የገደለ እንደሆነ በድንጋጌው የተመለከተውን ቅጣት እንደሚቀጣ ይደነግጋል፡፡

ስለሆነም በእርግጥም አመልካች እንደሚለው ተጠሪ ቸልተኝነት የነበረው መሆን አለመሆኑን ለመለየት ተጠሪ በቸልተኝነት ወንጀል ፈጽሟል በማለት በተከሰሰበት በሕጉ ልዩ ክፍል ላይ የተቀመጡትን ሁኔታዎች ከአድራጊው የግል ሁኔታ፣ በተለይም ዕድሜው፣ ያለው የኑሮ ልምድ፣ የትምሕርት ደረጃው፣ ሥራውን እና የማሕበራዊ ኑሮ ደረጃው ጋር ሲመዘን በጉዳዩ ሁኔታዎች ሊደረጉ ይገባል ተብሎ በአግባቡ የሚጠበቁበትን ጥንቃቄዎች ያላደረገ እንደሆነ ነው በሚል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 59/1(ለ) ላይ ከተቀመጡት መስፈርቶች ጋር በጥንቃቄ ታይቶ እና ተገናዝቦ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ አሽከርካሪነት ሙያው በመሆኑ የሌላውን ሰው ሕይወት እና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፣ ይህንኑ ግዴታውን ለመወጣትም ሙያው የሚፈቅደውን አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የሥር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት መኪናው ፍጥነት አልነበረውም፣ ተጠሪ ክላክስ ማድረጉ የደረሰውን አደጋ ለማስቀረት ጥረት ማድረጉን ያስገነዝባል በማለት ተጠሪን ከተከሰሰበት ክስ በነጻ ያሰናበተ ቢሆንም ተጠሪ በወቅቱ የመኪናውን ፍሬን በመያዝ ወይም መሪ በማዞር የሟችን ሕይወት ለመታደግ ጥረት ያደረገ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር የለም፡፡ ይህም ተጠሪ ሙያው የሚፈቅድለትን አስፈላጊ የሆነውን ጥረት በማድረግ ሟችን ማትረፍ ሲችል አድራጎቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እያወቀ አይደርስም የሚል ግምት ወይም ባለማመዛዘን ወይም ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ እያለበት ወይም እየቻለ ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈጸመ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይኸው የተጠሪ አድርጎትም የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል በሰጠው የሕክምና ማስረጃ ላይ እንደተገለጸው በሟች ሁለቱም የራስ ቅል ውስጥ ደም መፍሰስ እና የራስ ቅሉ የቀኝ ጎን መካከለኛ እና ኋለኛው አጥንት መሰንጠቅ እና መሰበር እንዲሁም አንጎሉ ውስጥ ደም መፍሰስ አስከትሎ የሟች ሕይወት እንዲያልፍ አድርጓል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ በቸልተኝነት ለፈጸመው ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/2 መሠረት ጥፋተኛ መባል ሲገባው ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪን ከተከሰሰቡት ክስ በነጻ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በፈጸመው በቸልተኝነት ሰውን መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ሊባል ይገባል ካልን ዘንዳ የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበውን የቅጣት ይገደብልኝ ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ቀጥለን እንመልከት፡፡

በመሠረቱ ቅጣት ሊገደብ የሚችለው ጥፋተኛ የተባለን ሰው ለጥፋቱ መነሻ የሆኑትን ምክንያቶችን በጠቅላላው በመመልከት በጥፋተኛው ላይ የተወሰነውን ቅጣት ለጊዜው በገደብ እንዲታገድ በማድረግ የወንጀለኛውን ጠባይ ለማረምና ለማሻሻል እንዲሁም ወደ መደበኛ ማህበራዊ ኑሮው ለመመለስ ጠቃሚ መሆኑ በታመነ ጊዜ ስለመሆኑ የቅጣት ገደብን አስመልክቶ ከተደነገጉት የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህንንም ተፈጻሚ ለማድረግ ፍ/ቤቶች ቅጣትን ለመገደብ የሚያስችሉ የተለያዩ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስባት እንዳለባቸው፤ እነዚህም ሁኔታዎች ወንጀለኛው ቀድሞ ያልተቀጣ ሆኖ ጠባዩም አደገኛነት እንደሌለው የሚታመንበት እንደሆነ፤ጥፋቱ በመቀጮ፤ በግዴታ ስራ ወይም ከሶስት አመት የማይበልጥ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኝነቱን ካረጋገጠ በኂላ ለወደፊት ጠባዩን ለማረም እንደሚችል እምነት ሊጣልበት የሚችል መሆኑና በዚህ ውሳኔ ብቻ እስከ መጨረሻው ሊሻሻል የሚችል መሆኑን ‘ያመነበት’ እንደሆነ፤ እንዲሁም ጥፋተኛው አስቀድሞ የተፈረደበት ቢሆንም ባይሆንም የተፈረደበትን ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት ለተወሰነ ጊዜ ቅጣቱ ታግዶለት አመሉ ቢፈተን ሁለተኛ ጥፋት ከማድረግም የሚታገድ መሆኑና ስለጠባዩም መሻሻል አንድ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ብቻ የሚበቃ መሆኑ ፍርድ ቤቱ ያመነበት እንደሆነ ቅጣቱ ከአፈፃፀም ታግዶ እንዲቆይ ሊያዝ የሚችል ስለመሆኑ ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 192 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በጥፋተኛው ላይ የተወሰነው ቅጣት እንዳይገደብ ሊያደርጉ የሚችሉ በሕጉ የተቀመጡ ሁኔታዊች ያሉ ሲሆን እነኚህም ሁኔታዎች ጥፋተኛው ከዚህ በፊት የጽኑ እሥራት ቅጣት ወይም ከሦስት ዓመት የሚበልጥ ቀላል እሥራት ቅጣት ተፈርዶበት እንደሆነ እና እንደገናም በተከሰሰበት ወንጀል ከእነዚህ ቅጣቶች አንዱ የሚወሰንበት እንደሆነ ወይም ጥፋተኛው ከዚህ ቀደም ያልተቀጣ ሆኖ በተከሰሰበት ወንጀል ከአምስት አመት የበለጠ የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚፈረድበት እንደሆነ ነው በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 194 ድንጋጌ ላይ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በሕጉ ከተመለከቱት ከእነኚህ ሁኔታዎች ውጪ ቅጣት እንዳይገደብ ለማድረግ የሚያስችሉ ሌሎች ሁኔታዎች ስለመኖራቸው በሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 196/2 የወንጀሉ ከባድነት / the gravity of the crime /፤ በወንጀል ድርጊት መደጋገም ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት እና በጥፋተኛው ላይ ሊጣልበት የሚችለው እምነት ከግምት ውስጥ መግባት አለበት በማለት የተቀመጠውም ቢሆን ፍ/ቤቱ ቅጣቱ እንዲገደብ አቋም ከያዘ በኂላ ቅጣቱ ተገድቦ የሚቆይበትን የፈተና ጊዜ ለመወሰን / ….. to fix the probation period ….. / እንጂ ቅጣቱን ለመገደብ ሊሟላ ይገባል ተብሎ የተቀመጠ ቅድመ-ሁኔታ አይደለም፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በሌላ በኩል በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 የተመለከቱት ቅድመ-ሁኔታዎች ፈተና የሚሰጥባቸውን ሁኔታዎች እንደሆኑ ከድንጋጌው ርዕስ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን እነኚህ ሁኔታዎች መሟላት አለመሟላታቸው ሊረጋገጥ የሚችለው ፍ/ቤቱ ከተከሳሹ የቀድሞ ታሪክ፤ የጠባዩ እና የዓመሉ አካሄድ በመነሳት ቅጣቱን መገደብ እንዳለበት ሲያምን እና ጥፋተኛው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 ላይ የተመለከቱትን ቅድመ-ሁኔታዎች እንደሚያሟላ ማረጋገጫ እንዲሰጥ በማድረግ እንደሆነ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 192፤196/1 እና 197 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ፍ/ቤቱ በጥፋተኛው ላይ የሚጣለውን ቅጣት ለጊዜው ማገድ ለወደፊቱ ጥፋቱን ለማረም እንደሚችል ሊያምን ወይም ላያምን የሚችለው የጥፋተኛውን የቀድሞ ታሪኩ፤ የጠባዩ እና የዓመሉ አካሄድ አስመልክቶ በችሎቱ የተረጋገጡትን እውነታዎች መነሻ በማድረግ ሲሆን ፍ/ቤቶች በሕግ እና በተገቢ ምክንያት የተደገፈ ውሳኔ መስጠት ያለባቸው በመሆኑ አመልካች ቅጣቱን ለማስገደብ ያቀረባቸው ምክንያቶች ፍ/ቤቱን የሚያሳምኑ ናቸው ወይም አይደለም ለማለት ሕግን መሠረት በማድረግ እና አግባብነት ያለውን ምክንያት በመስጠት ሊሆን ይገባል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ በፈጸመው ድርጊት ምክንያት ተጸጽቶ ለፍትሕ አካል እጁን የሰጠ መሆኑን፤ ሟችን በተጎዳ ሰዓት ያሳከመ እና ከሟች ቤተሰብ ጋርም የታረቀ መሆኑን፤ የቤተሰብ አስተዳዳሪ እና የቀድሞ ታሪኩም መልካም መሆኑን፤ በልማት እና በበጎ አድራጎት ስራ የሚሳተፍ እና የጤና ችግርም ያለበት መሆኑ በስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የልዩነት ሐሳብ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህም ተጠሪ በወንጀል ሕጉ በተገለጸው አግባብ ቅጣትን ለማስገደብ የሚያስችሉ ቅድመ-ሁኔታዎችን ያሟላ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ያስተላለፈውን ቅጣት መገደብ ሲገባው የትራፊክ አደጋ እንደ ሐገር እያደረሰ ካለው ጉዳት አንጻር ቅጣቱ ሊገደብ አይገባም ሲል የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የቅጣት ገደብን አስመልክቶ በሕጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ተጠሪ ያልፈጸመው ቀሪ የእስራት ቅጣት በሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ ሊገደብለት ይገባል በማለት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 197256 ጥር 19 ቀን 2013 ዓ.ም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 221450 ሐምሌ 14 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ጥቅምት 18 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው የቅጣት ውሳኔ ጸንቷል፡፡
3. ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው ምክንያት ተጠሪ በስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሠረት ያልፈጸመው ቀሪ ቅጣት በሁለት ዓመት የጊዜ ገደብ ሊገደብለት ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ትዕዛዝ

- ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 197 መሠረት የብር 3000 / ሶስት ሺህ ብር / መተማመኛ ዋስትና እንዲያስይዝ ታዟል፡፡
- የሚመለከተው ማረሚያ ቤት ተጠሪን እንዲረከብ እና ተጠሪ ለመተማመኛ ዋስትና ማስያዙ እና በስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት የተላለፈበትን የብር 1000 / አንድ ሺህ / የገንዘብ መቀጮ መክፈሉ በተረጋገጠ ጊዜ ተጠሪን እንዲለቅ ታዟል፡፡
- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁጥር 205048

ህዳር 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡ ዮናስ ሰለሞን- ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡ ሸገር ብዙሀን ትራንስፖርት ድርጅት- ነ/ፈ አየለ ወርቁ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ በዲሲሊን ክስ ቀርቦ ሰራተኛው ከስራ እንዲሰናበት ከተወሰነ አሰሪው ሰረተኛው ከስራ የሚያሰናብተውን ጥፋት መፈጸሙን አውቋል ሊባል የሚችለው መቼ ነው? የሚለውን የአሰሪ እና ሰራተኛ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ሐምሌ 3 ቀን 2012 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ክስ ስራ ሳይጠናቀቅ ባስ አቁመህ ሄደሀል በማለት ተጠሪ በሚያዝያ 19 ቀን 2012 ዓ.ም. ከስራ አግዶኛል፡፡ እንደዚሁም የስምሪት ኦፊሰር ላይ ድብደባ ፈጽመሀል በማለት ከ30 ቀን በላይ ታግጄ ከቆየሁ በኋላ ተጠሪ ከስራ አሰናብቶኛል፡፡ በመሆኑም ስንብቱ ህገወጥ ስለሆነ የተለያዩ ክፍያዎች ይከፈሉኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪም በሐምሌ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች ከስራ በመቅረታቸው ምክንያት በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ቢሆንም ባለመታረማቸው በሚያዝያ 19 ቀን 2012 ዓ.ም. ከስራ ታግደዋል፡፡ ሚያዝያ 15 ቀን 2012 ዓ.ም. በሰራተኛ ላይ ድብደባ በመፈጸማቸው የዲሲፕሊን ኮሚቴ አጣርቶ አመልካች ከስራ እንዲሰናበቱ የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ በ30 ቀን ይርጋ አይታገድም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክር ሰምቶ በአዋጅ ቁጥር 1156/11 አንቀጽ 27/3 አሰሪው ውል የሚያቋርጥበት ምክንያት መኖሩን ካወቀ ከ30 ቀናት በኋላ የማሰናበት መብቱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን ይገልጻል፡፡ አመልካች ጥፋት ፈጸሙ ከተባለበት ከሚያዝያ 19 ቀን 2012 ዓ.ም. ጀምሮ የመስሪያ ቤቱ ኃላፊ እስከፈረመበት ሰኔ 20 ቀን 2012 ዓ.ም. ድረስ ያለው ቀን ሲቆጠር 61 ቀን በመሆኑ እና የመስሪያ ቤቱ ሃላፊ የፈረመውም የዲሲፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ ከሰጠ የ30 ቀን ካለፈ በኋላ በመሆኑ ስንብቱ ህገወጥ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለአመልካች ውዝፍ ደመወዝ ከፍሎ ወደስራ ይመልሳቸው በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ላይ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የሰራተኛው ጥፋት በዲሲፕሊን ኮሚቴ የሚጣራ ከሆነ አሰሪው ጥፋት መፈጸሙን አውቋል ሊባል የሚችለው በዲሲፕሊን ኮሚቴው ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ ጊዜ ጀምሮ መሆን እንዳለበት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 53358 የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ በድርጅቱ የህብረት ስምምነት መሰረት ጥፋተኝነት የሚረጋገጠው በዲሲፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ ብቻ ሳይሆን የመስሪያ ቤቱ የበላይ ሃላፊ ሊያጸድቅ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ የመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ የዲሲፕሊን ኮሚቴው ውሳኔ ከጸደቀ ጀምሮ ሲቆጠር የ30 ቀን አልፏል ማለት ስለማይቻል ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡

አመልካች በመጋቢት 22 ቀን 2013 ዓ.ም. የተጻፈ የሰበር ቅሬታ ያቀረቡት ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡ የቅሬታው ይዘት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ቁጥር 53358 የህግ ትርጉም የተሰጠው የማጣራት ሂደት የሚያስፈልገው ጥፋት ሲፈጸም ነው፡፡ አመልካች ፈጽመሀል የተባልኩት ጥፋት በእለቱ በአሰሪ የሚታወቅ በመሆኑ ማጣራት የሚያስፈልገው አይደለም፡፡ ስለዚህ የይርጋ ጊዜ ሊቆጠር የሚገባው ጥፋቱ ተፈጸመ ከተባለ ጊዜ ጀምሮ ሊሆን ይገባል፡፡ ይርጋው መቆጠር ያለበት የዲሲፕሊን ኮሚቴ ከወሰነ በኋላ ነው ቢባል እንኳን የበላይ ሀላፊው ውሳኔውን እስኪያጸድቀው ሊጠበቅ አይገባም፡፡ በመሆኑም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎትም የአመልካችን የሰበር ቅሬታ መርምሮ ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው ኮሚቴው ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው ወይስ የኮሚቴ ውሳኔ በኃላፊው ከጸናበት ጊዜ ጀምሮ ነው? የሚለውን ነጥብ ለማጣራት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪ በሰኔ 22 ቀን 2013 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ በድርጅቱ የህብረት ስምምነት መሰረት አመልካች ጥፋተኛ መሆኑ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ተረጋግጦ በበላይ ሃላፊ ውሳኔው ከጸደቀበት ጀምሮ የ30 ቀን የይርጋ ጊዜ ሊቆጠር ይገባል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 53358 የህግ ትርጉም ተሰጥቶበታል በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካች በሐምሌ 7 ቀን 2013 ዓ.ም. የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በስር ፍርድ ቤት ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር እና ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ፈጽመዋል የተባለውን የሰራተኛ ድብደባ አለመፈጸማቸውን ክደው የሚያቀርቡት መከራከሪያ የለም፡፡ የስራ ውል ከመቋረጡ በፊት በድርጅቱ ህብረት ስምምነት መሰረት መጀመሪያ ጥፋቱ በዲሲፕሊን ኮሚቴ ተጣርቶ ውሳኔ መሰጠት እንዳለበት እና የዲሲፕሊን ኮሚቴው ውሳኔ በሀላፊ ሊጸድቅ እንደሚገባ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ድርጊቱ በተፈጸመ እለት ከስራ እንደሚያሰናብት የሚታወቅ ግልጽ ጥፋት በመሆኑ ከስራ ለማሰናበት በዲሲፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ እስኪሰጥ እና የዲሲፕሊን ኮሚቴው ውሳኔ በኃላፊ እስኪጸድቅ ሊጠበቅ አይገባም፡፡ በመሆኑም የስንብት ደብዳቤ የተሰጠኝ በህጉ የተመለከተው የ30 ቀን ካለፈ በኂላ በመሆኑ ስንብቱ ህገወጥ ነው በሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የተሰናበቱት ለስንብት ምክንያት የሆነውን ድርጊት ከፈጸሙ ከ30 ቀን በኂላ መሆኑን ሳይክድ የስንብት ኮሚቴ ውሳኔ እስኪሰጥ እና የኮሚቴው ውሳኔ በተጠሪ ኃላፊ እስኪጸድቅ መጠበቁ ተገቢ መሆኑን ገልጾ ተከራክሯል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/3 አንድ አሰሪ ሰራተኛው በአዋጁ አንቀጽ 27/1 ላይ የተዘረዘሩትን ከስራ የሚያሰናብተው ድርጊት መፈጸሙን ካወቀ ከ30 ተከታታይ የስራ ቀናት በኂላ ከስራ የማሰናበት መብቱን እንደተወ እንደሚቆጠር ያመለክታል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው የ30 ቀኑ የጊዜ ገደብ የበአላት እና የእረፍት ቀናትን ሳይጨምር የስራ ቀን ብቻ እንደሚቆጠር እና ይህ 30 የስራ ቀን መቆጠር የሚጀምረው አሰሪው ድርጊቱ መፈጸሙን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ አመልካች ድብደባውን በፈጸመ እለት አላውቅም ነበር በሚል ያቀረበው ክርክር ካለመኖሩም በላይ በአመልካች ላይ የዲሲፕሊን ክስ ያቀረበው ተጠሪ በመሆኑ ድርጊቱ በተፈጸመ ቀን አመልካች መፈጸሙን ያቅ እንደነበር አመላካች ነው፡፡ ይሁን እንጂ በድርጅቱ የህብረት ስምምነት ጥፋተኝነት በዲሲፕሊን ኮሚቴ ተወስኖ በበላይ ሃላፊ መጽደቅ እንዳለበት ከተመለከተ አሰሪው ይህንን ሂደት ሳይከተል ድርጊቱ መፈጸሙን እንዳወቀ ሰራተኛውን ቢያሰናብት ስንብቱን ህገወጥ ያደርገዋል፡፡ አሰሪው ያለው አማራጭ ድርጊቱ መፈጸሙን ድርጊቱ በተፈጸመ እለት ቢያቅ እንኳን በጉዳዩ ላይ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ እስኪሰጥ መጠበቅ ነው፡፡ አሰሪው ሰራተኛው በህብረት ስምምነት ያለውን መብት ለማክበር ጉዳዩ በዲሲፕሊን ታይቶ እስኪወሰን በመጠበቁ ሰራተኛውን ከስራ ሳያሰናብት የ30 ቀን የጊዜ ገደብ ቢያልፍ አሰሪው የማሰናበት መብቱን እንደተወው

መቁጠር የአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/3 ድንጋጌ አላማ ነው ተብሎም አይገመትም፡፡ በእርግጥ የዲሲፕሊን ኮሚቴ አጣርቶ ከወሰነ በኂላ የመስሪያ ቤቱ ኃላፊ የዲሲፕሊን ኮሚቴ በወሰነ በ30 ቀን ውስጥ የዲሲፕሊን ኮሚቴውን ውሳኔ በማጽናት ወይም በመሻር ወይም በማሻሻል ሊወስን ይገባል፡፡ ምክንያቱም የዲሲፕሊን ኮሚቴ አጣርቶ ከወሰነ በኂላ እንደገና የሀላፊውም ውሳኔ ሌላ ተጨማሪ ጊዜ እንዲወስድ ከተፈቀደ በአዋጁ አንቀጽ 27/3 የተቀመጠውን የጊዜ ገደብ አላማ የሚቃረን ይሆናል፡፡በመሆኑም ጥፋቱ በዲሲፕሊን ኮሚቴ መጣራት እንዳለበት በህብረት ስምምነት ወይም በሌላ ሁኔታ ከተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/3 የተመለከተው የ30 ቀን የጊዜ ገደብ መቆጠር መጀመር ያለበት የዲሲፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ በሀላፊ ከጸደቀበት ሳይሆን የዲሲፕሊን ኮሚቴ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ሊሆን ይገባል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 53358 የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የአመልካች ጥፋተኝነት በዲሲፕሊን ኮሚቴ ተጣርቶ ተፈርሞ የተጠናቀቀው በግንቦት 15 ቀን 2012 ዓ.ም. ነው፡፡ በተጠሪ የበላይ ኃላፊ የተፈረመው ደግሞ በሰኔ 20 ቀን 2012 ዓ.ም. ነው፡፡ ከግንቦት 15 ቀን 2012 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ሰኔ 20 ቀን 2012 ዓ.ም. ድረስ በተከታታይ ሲቆጠር 35 ቀን የሚሆን ቢሆንም በመካከል ቢያንስ 8 ቅዳሜ እና እሁድ የእረፍት ቀን የሚኖር በመሆኑ የስራ ቀን ብቻ ሲቆጠር ሃላፊው የዲሲፕሊን ኮሚቴውን ውሳኔ በማጽናት የወሰነው የ30 ቀን የጊዜ ገደብ ካለፈ በኂላ ነው ማለት አይቻልም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 27/1/ረ መሰረት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብታቸው የሚችል ድርጊት መፈጸማቸውን ተጠሪ ድርጊቱ በተፈጸመ እለት ቢያውቅ እንኳን በድርጅቱ የህብረት ስምምነት ጥፋተኝነት የሚወሰነው በዲሲፕሊን ኮሚቴ ከተጣራና ከተወሰነ በኂላ መሆኑን እስከተመለከተ ድረስ በአዋጁ አንቀጽ 27/3 የተመለከተው የ30 ቀን የጊዜ ገደብ መቆጠር መጀመር ያለበት የዲሲፕሊን ኮሚቴ ከወሰነ ቀን ጀምሮ ሊሆን ሲገባ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የ30 ቀኑ መቆጠር መጀመር ያለበት የዲሲፕሊን ኮሚቴው ውሳኔ በኃላፊ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ነው ማለቱ ተገቢ ባይሆንም የተጠሪ ኃላፊ ውሳኔውን ያጸናው የ30 ቀን የጊዜ ገደብ ሳያልፍ በመሆኑ ከውጤት አንጻር የሚያመጣው ለውጥ ስለሌለ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1ኛ. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 257967 በመጋቢት 06 ቀን 2013 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

2ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይ

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ፡-205033

ቀን፡-27/01/2014ዓ/ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1ኛ ወ/ሪት የአብስራ ጥላሁን } ጠበቃ ፋሲል ቀረቡ

2ኛ ህፃን ሚኪያስ ጥላሁን

ተጠሪ፡- አቶ ክፍለዩሀንስ ደረጀ - ከጠበቃ ደሳለኝ ደመቀ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር ክርክር ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች በቀን 20/07/2013 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 193736 በቀን 28/05/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልጸው በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻነት ሲሆን አመልካቾች በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሳሾች የነበሩ ሲሆን ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ የሟች አባታችን አቶ ጥላሁን በለጠ ልጆች እና ሕጋዊ ወራሾች ስንሆን አባታችን በህይወት በነበሩ ጊዜ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኝ መኖርያ ቤት የነበራቸው ሲሆን ለዚህ ቤት ተጠሪ ካርታ አወጣለሁ በሚል ከሟች አባታችን ውክልና የተሰጠው ሲሆን አባታችን ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ተጠሪ ይህንን ውክልና በመጠቀም በዚህ ቤት ላይ በአባታችን ስም በካርታ ቁጥር.20/41/17075/00 በቀን 30/12/99 ዓ.ም የይዞታ ማረጋጋጫ ካርታ ያወጣበት ሲሆን ሟች አባታችን ሕጋዊ ወራሽ እንደሌለው በማስመሰል እና አባታችንን እንዲጠፋ በማድረግ በማናውቀው ሁኔታ ቤቱን በእጁ በማድረግ እየተጠቀመ የሚገኝ በመሆኑ ተጠሪ በኃይል የያዘውን ቤት ከነይዞታ ማረጋገጫ እንዲያስረክበን ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስም ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት ከሟች አቶ ጥላሁን በለጠ መጋቢት 29 ቀን 1994 ዓም ባደረግነው የመንደር ሽያጭ ውል በብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ ገዝቼው ሚያዚያ 1 ቀን 1994 ዓ.ም ቤቱን ተረክቤ እስካሁን ድረስ እየኖርኩበት እገኛለሁ በይዞታው ላይ የነበረውን ቤት አፍርሼ ሌላ ቤት ሰርቼለሁ ለ16 ዓመታት ለቤቱ ግብር ገብሬያለሁ ስለሆነም ቤቱን በኃይል ሳይሆን በሽያጭ ውል የያዝኩት እና ሟችም ከመሞቱ በፊት መብቱን ሕግ በሚፈቅደው መሰረት በውል ያስተላለፈልኝ በመሆኑ ለአመልካቾች ቤቱን የማስረክብበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፤ ነገር ግን ቤቱን ማስረከብ አለብህ ከተባልኩ ለቤቱ ያወጣሁትን ልዩ ልዩ ወጪዎችን ከአመልካቾች የመጠየቅ መብቴ ይጠበቅልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሉ ሲደረግ ነበሩ የተባሉ ምስክርን አስቀርቦ በመስማትና የሰነድ ማስረጃዎችን በመመርምር በሰጠው ውሳኔም ተጠሪ አከራካሪውን ቤት 1994 ዓም በተደረገ የሽያጭ ውል ከአመልካቾች አባትና እናት በመግዛት ከገዙበት ጊዜ ጀምሮ በእጃቸው በማድረግ እየተጠቀሙበት መሆኑን የሚገኙ መሆኑን ያስረዱ ስለሆነ ተጠሪ አከራካሪውን ቤትና ሰነዶቹን ለአመልካቾች ሊያስረክቡ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ በተጠሪ እና በአመልካቾች አውራሽ መካካል የተደረገው ውል በፅሁፍ የተደረገ ሆኖ ሊመዘገብ ሲገባው ያልተመዘገበ በመሆኑ የህጉን ፎርማሊቲ አሟልቷል ሊባል ስለማይችል ውሉ እንደ ረቂቅ የሚቆጠር እንጂ ህጋዊ ውጤት እንዳለው የቤት ሽያጭ ውል ሊቆጠር ስለማይችል ተጠሪ በዚህ ውል አማካኝነት የቤቱ ባለቤት ተደርገው ሊወሰዱ አይችሉም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ በይዞታው ላይ ያፈሩት ንብረት ካለ ከስሶ የመጠየቅ መብትን በመጠበቅ ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሰኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ የሽያጭ ውሉን ክደን እንደተከራከርን ባረጋገጠበት ደረጀና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2003 ድንጋጌ በተቃረነ መልኩ አንድ ምስክር በመስማት በተካደ ውልና አግባብ ባለው ውል አዋዋይ ፊት ያልተረጋገጠን ረቂቅ ውል መሰረት አድርጎ ለአሁን ተጠሪ የባለቤትነት መብት ማጎናፀፉ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.1723፣ 2878 እና ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ.21448 እና በርካታ ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ የሕግ ትርጎሞች አንፃር መሰረታ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሊሽርበት የሚገባውን በቂ ምክንያት ሳያስቀምጥ የውሉን መኖር ክደን ተከራክረን እያለ በደፈናው ያቀረብነውን ክርክር ወደጎን በማለት የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ማፅናቱ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ነው፡፡ስለሆነም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ጉዳዩ እንደገና እንዲታይልን ወይም አሁን ያቀረብነው ቅሬታ በሰ/መ/ቁ.195021 ላይ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ቤቱንና ሰነዶችን እንዲያስረክበን ፍርድ ሳይሰጥ በማለፉ ቅሬታ አቅርበን ጉዳዩ ያስቀርባል ተብሎ ለምርመራ የተቀጠረ በመሆኑ ቅሬታው አንድ ላይ ተጣምሮ ፍትሃዊ ውሳኔ እንዲሰጥልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት ቋሚ /የማይንቀሳቀስ/ ንብረት ከመሆኑ አንፃር አለ የተባለው የሽያጭ ውል በሚመለከተው አካል ቀርቦ ባልተመዘገበበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ከአመልካቾች አባት ጋር የሽያጭ ውል ፈፅሟል በማለት ተጠሪ ቤቱን ሊለቅ አይገባም በማለት የወሰነበትን አግባብ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 21448 ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ.1723፣ 2878 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው መልስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ በዚህ መልሳቸውም በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ተጠሪ ውሉን ሲያቀርብ አመልካቾችን በጉዳዩ ላይ ጥቅም አለን ካሉ በአባታችንና ተጠሪ መካካል ውል አልተደረገም፣ወይም የአባታችን ፊርማ አይደለም፣ አባታችን የሽያጭ ገንዘብ አልተቀበለም፣ ውሉ ሀሰት ነው፣ እናታችን በሕይወት ያለች ስለሆነ መሸጥ አለመሸጧን ችሎት ቀርባ ታረጋግጥ ወዘተ ማለት ሲገባቸው ውሉ ረቂቅ ነው ይባልልን በማለት በክስ ላይ ያልጠቀሱትን ሀሳብ በይግባኝ ክርክር ወቅት አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች ውል መኖሩን በሚገባ ያውቃሉ፡፡አመልካቾችና እናታቸው ቤቱ መሸጡን ባያውቁ ኖሮ ቢያንስ አባታቸው በሞተበት 1997 ዓ.ም እና ክስ ባቀረቡት 2010 ዓ.ም መካካል ባሉት አስራ ሶስት ዓመታት ውስጥ በግለሰብ ኪራይ ቤት እየኖሩ ቤታቸውን ሌላ ሰው እንዲኖርበት ሊፈቅዱ አይችሉም፡፡ስለዚህ አመልካቾች ውል መኖሩን በሚገባ እያወቁና ውሉ እንዲፈርስ ግልጽ ዳኝነት ባልጠየቁበትና ክርክር ባልተደረገበት ሁኔታ የክርክር አቅጣጫ በሂደት እንዲቀየር በማድረግ በአቋራጭ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪ ለዓመታት የለፋሁበትንና ከፍተኛ ወጭ ያወጣሁበትን ቤት ለመረከብ ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ተብሎ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግልኝ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት የለውም ተብሎ እንዲፀናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡በመሰረቱ አንድ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አወሳሰን የጠራ ፍሬ ነገር የሌለ መሆኑን ከተገነዘበ ይኸው ፍሬ ነገር እንዲጣራ ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት ሁሉ ማድረግ እንደሚችል ከፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.136፣137፣272 እና 345 ድንጋጌዎች ለመረዳት የሚቻል ሲሆን ለጉዳዩ አወሳሰን መሰረት የሚሆንን ፍሬ ነገር በማስረጃ ሳያጣሩ መወሰን አግባብ ባለመሆኑ በክርክሩ የቀረቡት ማስረጃዎች በቂ ባልሆኑበት ጊዜ እና እነዚህን ማስረጃዎች ብቻ መሰረት አድርጎ መወሰን ፍትህን የሚያዛባ ከሆነ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት ተጨማሪ ማስረጃ ወይም ምስክር እንዲቀርብ መታዘዝ አለበት፡፡(በሰበር መዝገብ ቁጥር 72980 ፣ 22603፣180331 እና በተመሳሳይ ጉዳይ የተሰጡ አስገዳጅ ውሳኔዎችን ይመለከቷል፡፡)

አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ውሉ አለመደረጉን በመካድ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት አልተከራከሩም በዚህ አግባብ የቀረበው ክርክር አዲስ ክርክር ነው በማለት የተከራከሩ ቢሆንም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ «…አመልካቾች ውሉ ሀሰተኛ ነው፣ሚስትም አልፈረመችበትም፣የሽያጭ ውልም አልተደረገም…»በማለት መከራከራቸውን ማመልከቱ አመልካቾች ከውሉ አለመኖር ጋር በተያያዘ ያቀረቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር አለመሆኑን ያሳያል፡፡የውሉን መደረግ አለመደረግ ለማጣራት አንድ ምስክር በማስቅረብ የሰማ መሆኑ በውሳኔው ላይ የተመለከተ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት አመልካቾች ካቀረቡት ክርክር አንፃር የውሉ ተዋዋይ መሆናቸው ተገልፆ በተጠሪ ክርክር የቀረበባቸው ወ/ሮ አየሉ ሹሙ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ በማድረግ ግለሰቧ በውሉ ላይ የፈረሙ መሆን አለመሆኑን በማጣራት ከፈረሙም አመልካቾች የሽያጭ ውል አልተደረገም በማለት የተከራከሩ በመሆኑ በህጉ አግባብ የተደረገ ውል መኖር አለመኖሩን በማጣራት የሰጠው ውሳኔ ስለመኖሩ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አያሚይም፡፡

ይህንን ውሳኔ በይግባኝ ተመልክቶ ያፀናው ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም አመልካቾች አከራካሪውን ቤት አስመልክቶ በአውራሻቸውና እናታቸው ወ/ሮ አየሉ ሹሙ የተደረገ ውል የለም በማለት በግልፅ ክርክር ማቅረባቸውን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እያሳየ አመልካቾች«…አባታቸው የተባለውን ውል ከይግባኝ ባይ ጋር እንዳልፈፀመ ወይም አባታችን ውሉን አላደረገም በማለት በግልፅ ክደው እንዳልተካራከሩ ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ ውስጥ መረዳት ይቻላል፡፡» በማለት ከውሉ የህጉን መስፈርት ማሟላት አለማሟላት ጋር በተያያዘ የቀረበውን ክርክር ሳይመረምር የስር ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ማፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለው ተወስኗል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ውሳኔ

1.የፌደራል መጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 65262 በቀን 14/02/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ በማፅናት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይ/መ/ቁ 193736 ጥር 28 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2.የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጉዳዩን መዝገብ በማንቀሳቀስ ወ/ሮ አየሉ ሹሙን ወደ ክርክሩ በማስገባት ውሉ በአመልካቾች አውራሽና ወ/ሮ አየሉ ሹሙ የተፈረመ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ፊርማውን እንዲመረመር በማድረግ ውጤቱን በችሎቱ ቀርበው ከተሰሙት ምስክር ቃል ጋር በመመርመር ውሉ በነዚህ ተዋዋይ ወገኖች (አቶ ጥላሁን በለጠን ጨምሮ) የተፈረመ ከሆነም ውሉ የህጉን ፎርማሊቲ በማሟላት የተደረገ መሆን አለመሆኑን በመመርመር በህጉ አግባብ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡

3.ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>

ሄ/መ   የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የ/ሰ/መ/ቁ. 204919

ቀን፡-27/01/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዓቃቤሕግ-ዓ/ህግ ሄኖክ ተስፋየ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. አስረስ አዕሮ
2. ታምራት አዕሮ
3. አብይ አበራ
} አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ብይን

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 17 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 12027 በቀን 04/05/2013 ዓ.ም አመልካች ያቀረበውን ክስ ፍርድ ቤቱ በቀጥታ ተቀብሎ የማየት ስልጣን የለውም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ፤ ይህንኑ ትዕዛዝ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 08913 በቀን 27/05/2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የአሁን አመልካች ተጠሪዎች የንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 3 ድንጋጌን በመተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ያቀረበን ክስ የተመለከተው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበው ክስ በቀጥታ በፍርድ ቤቱ የሚታይ ሳይሆን በይግባኝ የሚታይ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በቀጥታ ተቀብሎ ለማየት የሚያስችል ሥልጣን የለውም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው በትዕዛዝ ውድቅ ተደርጓል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 በመተላለፍ የሚቀርቡ ክሶች ለፌዴራል ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ሆነው ሳለ ክሱ የቀረበለት የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት የቀረበውን ክስ በቀጥታ ለማየት የሚያስችል ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን ክስ በቀጥታ ለማየት የሚያስችል ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ትዕዛዝስ አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ጉዳዩ የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን የሚመለከት በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ጉዳዩን አከራክሮ መወሰን ያለበትን ፍርድ ቤት በመለየት ተገቢውን ፍርድ ቢሰጥ አንቃወምም የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ የሰበር አቤቱታው አቀራረብ አግባብ መሆን አለመሆኑን በቅድሚያ መርምሪናል፡፡

ለክርክሩ ሒደት መነንዘብ የተቻለው አመልካች ተጠሪዎች የንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀጽ 3 ድንጋጌን በመተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት በቀጥታ የዳኝነት ስልጣኑ እንዲመለከተው *በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱን ያቀረበ ቢሆንም ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ እንጂ በቀጥታ ለማየት የሚያስችል ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን የዘጋው መሆኑን ነው፡፡*

በመሠረቱ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎቶች መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈፀመባቸውን የክልል ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔዎችን በሰበር አይተው የማረም ሥልጣን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3(ለ) የተሰጣቸው ሲሆን በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ሥልጣናቸውን መሠረት አድርገው መስራት አለመስራታቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎቶች በሥራቸው ያሉ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የክልል ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸውን ጉዳይ አይተው ውሳኔ የሰጡት በሕግ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት መሆን አለመሆኑን አይቶ የማረም ሥልጣን ያላቸው ለመሆኑ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 78640፤ 82288፤ 106383 እና በሌሎችም መዛግብት አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ አንፃር የአሁን አመልካች አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በቀጥታ ለማየት የሚያስችል ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ አግባብ መሆን አለመሆኑን ውሳኔ ማሰጠት ሲገባው የሰበር ሥነ ሥርዓቱንና በመተላለፍ በቀጥታ ጉዳዩን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ማቅረቡ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ ያላገኘ በመሆኑ ተገቢውን ደረጃ ጠብቆ የቀረበ አይደለም በማለት ውድቅ አድርገናል፡፡
2. ይህ ውሳኔ መብቱን የሚጠይቅ ወገን በህጉ መሰረት አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከማቅረብ የሚያግደው አይደለም ብለናል፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

ሄ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-204866

ቀን፡-30/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የካ ክ/ከተማ ዐቃቤ ህግ ፅ/ቤት- ዮሴፍ ዲኖ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1.አቶ ብሩክ ወንድሙ } 2ኛ ተጠሪ ቀረቡ

2.ወ/ሮ ሚስጥረ ወንድሙ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 20 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.358 የቀረበን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከውጤት አንፃር ማፅናቱ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይኸው እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ሲሆን አመልካች በስር ፍርድ ቤት የመ/አመልካች የነበረ ሲሆን ተጠሪዎች የመ/ተጠሪዎች ነበሩ፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.358 መሰረት ባቀረበው አቤቱታም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 64/2011 መሰረት የአስተዳደሩን እና የነዋሪዎችን መብት እና ጥቅም በማስከበር በማናቸውም የዳኝነት አካል ዘንድ የመቃወም አቤቱታ የማቅረብ መብት እንዳለው በመግለፅ በመቃወም ተጠሪዎች እና በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 7 አስተዳደር ፅ/ቤት መካከል በተደረገው ክርክር ላይ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ መብቴን የሚነካ በመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል በማለት አመልክቷል፡፡

ፍርድ ቤቱም ተጠሪዎች በጉዳዩ ላይ መጥሪያ ደርሷቸው መልስ ከመስጠታቸው በፊት መዝገቡን መርምሮ በሰጠው ውሳኔም ተጠሪዎች የካ ክ/ከተማ ወረዳ 07 አስተዳደር ፅ/ቤትን ከሰው ክርክር ላይ በነበሩበት ወቅት አመልካች ተከሳሹን ወክለው መልስ በመስጠት ከተከራከሩ በኋላ ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፤በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.358 የመቃወም አቤቱታ ለማቅረብ የሚችለው በክርክሩ ተካፋይ ባልነበረ ወገን ሊሆን እንደሚገባ በግልፅ የሚያመለክት መሆኑን በመጥቀስ አመልካች ራሱ ተወካይ ሆኖ ተከራክሮ የተሰጠውን ውሳኔ ቅሬታ ካለው ይግባኝ በማቅረብ እንዲስተካከል ከማድረግ ባለፈ በድጋሚ ተቃዋሚ ሆኖ የሚቀርብበት አግባብ የለም በማለት የአመልካችን የመቃወም አቤቱታ ውድቅ ያደረገው ሲሆን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም ብይኑን ከውጤት አንፃር አፅንቶታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ባቀረበው የሰበር አቤቱታም በመጀመሪያው ክስ እና በመቃወም አቤቱታው ላይ ዐቃቤ ህግ ፅ/ቤት የወከላቸው የተለያዩ ተቋማት ሆነው እያለ ፍርድ ቤቱ ይህንን ሳይገነዘብ፤በአዋጅ ቁጥር 64/2011 ለአመልካች የተሰጠውን የመቃወም አቤቱታ የማቅረብ ስልጣንና ተግባር ሳይመረምር ፍርድ ቤቱ የደረሰበት መደምደሚያ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ፤የአስተዳር አካሉ ጣልቃ ለመግባት አቤቱታ አቅርብልኝ ብሎ ጉዳዩን ሲልክልኝ ብቻ ጉዳዩን በመመርምር በጉዳዩ ላይ የጣልቃ ገብ አቤቱታ ሊቀርብበት እንደሚገባ ሲያምን አቤቱታ ከማቅረብ ውጪ ዐቃቤ ህግ በራሱ ተነስቶ ጣልቃ ገብቶ ሊከራከር የሚችልበት አግባብ በሌለበት ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የደረሰበት መደምደሚያ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ አመልካች የአስተዳደሩንና የነዋሪውን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ በመቃወም አመልካችነት አቤቱታውን ተብሎ እንዲያከራክረን ይወሰንልን በማለት አመልክቷል፡፡

አመልካች በስር ፍርድ ቤት በቀድሞ ክስ የወከለው የካ ክ/ከተማ ወረዳ 07 አስተዳር ፅ/ቤትን ሆኖ እያለ አሁን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.358 መሰረት መብቴ ተነካ በማለት መቃወሚያ ያቀረበው የመሬት ባንክና ልማት ማኔጅመንት ፅ/ቤትን በመሆኑ አመልካች የወከለው ሁለት የተለያዩ ተቋማትን ከመሆኑ አንፃር ጉዳዩን ያውቃል በሚል አቤቱታው ውድቅ የተደረገበትን አግባብ ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ለተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸው መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዎች በሰጡት መልስም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀፅ 6 በዝርዝር ከተሰጠው ስልጣን አንጻር በተቋማት የምታዘዝ ስማ በለው ነኝ ማለቱ ተገቢነት የሌለው ሙግት ነው፤አመልካች የቀደመው ክርክር መኖሩን እያወቀ ውጤቱን ጠብቆ መቅረቡ አግባብ አለመሆኑን በመጥቀስ የተሰጠው

ውሳኔ በሰበር መዝገብ ቁጥር 56795 የተሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት ያደረገ በመሆኑ፣አመልካች መብቱ ተነክቷል የሚለው የክፍለ ከተማው የይዞታ አስተዳር ፅ/ቤት በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ ትዕዛዝ የቤት ቁጥር 389 እና 390 መዝገብ ውስጥ ያሉትን ሰነዶች በመፈተሽ በሰጠው ምላሽ ይዞታው በተጠሪዎች እጅ ያለ መሆኑን አረጋግጦ በሰጠው ምላሽ መሰረት በአፈፃፀም በተሰጠ ትዕዛዝ በሁከት ተግባር የፈረሰውን ቤትና አጥር ባለበት ሁኔታ ተጠሪዎች የተረከቡን በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ተቀባይነት የለውም ተብሎ ውሳኔ ይሰጥልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡በመሰረቱ የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የአመልካችን የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.358 የመቃወም አቤቱታ ውድቅ ያደረገው በመነሻነት አመልካች በቀደመው ክርክር የየካ ክ/ከ/ወረዳ 07 አስተዳደር ፅ/ቤትን ወክሎ መከራከሩን በመጥቀስ በዚህም የክርክሩ አካል ሳይሆን ወኪል መሆኑን በመጥቀስ ቢሆንም በመጨረሻ መደምደሚያው ላይ በውሳኔው ቅር ከተሰኘ ስልጣን ላለው አካል ቅሬታውን በማቅረብ ማስተካከል እንደሚችል በውሳኔው ላይ ማመልከቱ አመልካችን የክርክሩ አካል አድርጎ የወሰደ መሆኑን ያሳያል፡፡ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት የአመልካችን የመቃወም አቤቱታ ውድቅ ያደረገው ደግሞ ስለቀደመው ዋናው ክርክር አመልካች የሚያውቅ ሆኖ እያለ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.358 የመቃወም አቤቱታ ማቅረቡ የክርክሩን ውጤት ጠብቆ መቃወሚያ ማቅረቡን የሚያሳይ መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ ለመቃወም አቤቱታው መነሻ የሆነው ክርክር ይዞታን የሚመለከት የሁከት ይወገድልኝ ክርክር መሆኑ ግራ ቀኙ ያልተካካዱበት ነጥብ ሲሆን ተጠሪዎች ይዞታን በሚመለከት ክሱን ያቀረቡት በየካ ክ/ከተማ ወረዳ 7 አስተዳደር ፅ/ቤት ላይ ሲሆን በዚሁ ፅ/ቤት ላይ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በክሱ ሊካተቱ የሚገባቸው ከመሬት አስተዳደር ጋር በተያያዘ ስልጣን ያላቸውና አስገዳጅ ውሳኔ ቢሰጥም ለማስፈፀም አግባብነት ያላቸው አካላት ወደ ክርክሩ ገብተው መከራከራቸውን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ አያሳይም፡፡

አመልካች የመቃወም አቤቱታ ያቀረበው ከመሬት አስተዳደር ጋር በተያያዘ ስልጣን ያለውንና አስገዳጅ ውሳኔ ቢሰጥም ለማስፈፀም አግባብነት ያለውን የየካ ክ/ከተማ የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ፅ/ቤትን በመወከል መሆኑን በመጥቀስ በአዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 18(8)(9) በተሰጠው ስልጣን እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ.መ.ቁ 37502 በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት የመንግስትን እና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲል የሚያቀርበው የመቃወም አቤቱታ ሆኖ እያለ ስለቀደመው ክርክር ማወቅ አለማወቁ ሊጣራና ሊመረመር የሚገባው ከመሬት አስተዳደር ጋር በተያያዘ ስልጣን ያለውና አስገዳጅ ውሳኔ ቢሰጥም ለማስፈፀም አግባብነት ያለው የየካ ክ/ከተማ የመሬት

ባንክና ማስተላለፍ ፅ/ቤት እንጂ ይህንን ፅ/ቤት ወክሎ የሚከራካረው አመልካች ባልሆነበት የክፍለ ከተማው የመሬት ባንክና ማስተላለፍ ፅ/ቤት ስለቀደመው ክርክር እውቀቱ እያለው የክርክሩን ውጤት ጠብቆ መቅረቡ ባልተረጋገጠበት የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የመቃወም አቤቱታ ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.214399 ታህሳስ 26 ቀን 2013 ዓም የሰጠው ብይን እና ይህንን ብይን በማፅናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.261514 ሰኔ 09 ቀን 2013 ዓም የሰጠው ፍርድ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጉዳዩን መዝገብ በማንቀሳቀስ የአመልካችን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.358 የቀረበ አቤቱታ ተቀብሎ ግራ ቀኙን አከራክሮ አስፈላጊ ከሆነም ማስረጃዎችን ሰምቶ እና ተገቢውን ማጣራት አድርጎ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.360(2) መሰረት የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡
3. ሀምሌ 12 ቀን 2013 ዓም በዋለው ችሎት በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.261839 በተያዘው አፈፃፀም ላይ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ እልባት ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሂ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ 4/4
ለፍርድ አፈጻጸምዓላማአያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 204833

ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡ ኢሊሌ ኢንተርናሽናል ሆቴል፡- ነ/ፊጅ አመኑ ለሜሳ

ተጠሪ ፡ አቶ ፀጋዬ መለሰ፡- ከጠበቃ ፈለቀ ዋኘ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የስራ ክርክር ሲሆን በተጀመረበት የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በ08/11/2011 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ክስ በአመልካች ሆቴል ውስጥ በዋና ምግብ አዘጋጅነት የስራ መደብ በወር ብር 85,554 እየተከፈለኝ ስሰራ ቆይቼ ግንቦት 15 ቀን 2011 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ በግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም. በነበረው የሙስሊሞች ጾም አፍጥር ዝግጅት ላይ ጉድለት አሳይተሀል በሚል ከግንቦት 15 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የስራ ውሌን አቋርጧል፡፡ ነገር ግን የፈጸምኩት ጉድለት የለም፡፡ ጉድለት አለ ቢባል እንኳን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት ባለመሆኑ ስንብቱ ህገወጥ ነው ተብሎ አመልካች የማስጠንቀቂያ ጊዜ፤ የካሳ እና የስንብት ክፍያ እንዲሁም የአንድ ወር ደመወዝ በድምሩ ብር 705,820 እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች በ03/12/2011 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ ተጠሪ ዋና የምግብ አዘጋጅ እና የስራ መሪ ስለሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም፡፡ ተጠሪ በቂ ምግብ ባለማዘጋጀታቸው እንግዶች ተሻምተው እንዲበሉ ምክንያት ሆነዋል፡፡ ተጠሪ በስራቸው የሚገኙ ሼፎችን አስተባብረው ባለመስራታቸው የተፈጠረ ችግር ነው፡፡ በዚህም የሆቴሉ መልካም ስም ጎድፏል፡፡ ተጠሪ በተደጋጋሚ ጥፋት በመፈጸማቸው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ሊታረሙ አልቻሉም፡፡ በመሆኑም ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ በሚሊኒየም አዳራሽ ለ750 ሰዎች ለተዘጋጀው የአፍጥር ስነስረአት ተጠሪ 15 በመቶ ተጨማሪ ምግብ ማዘጋጀታቸው በተጠሪ ምስክር ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በቂ ምግብ ስለማዘጋጀት አለማዘጋጀታቸው የእራት ሰአት ከመድረሱ በፊት በአመልካች ቆጠራ አልተደረገም፡፡ ችግሩ ሊፈጠር የቻለው ተጠሪ በቂ ምግብ ባለማዘጋጀታቸው ሳይሆን አመልካች እንግዶቹን እየተቆጣጣረ የሚያስገባበት ሁኔታ ስላልነበር መሆኑን የተጠሪ ምስክሮች በተሻለ ሁኔታ ስላስረዱ በተጠሪ የተፈጸመ ጥፋት የለም፡፡ በመሆኑም ስንብቱ ህገወጥ ስለሆነ የስንብት፣ የካሳ፣ የማስጠንቀቂያ ክፍያ በድምሩ ብር 655,914 እና የጠበቃ አበል ብር 25,000 አመልካች እንዲከፈል ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 337 መሰረት በመሰረዙ የሚከተለውን የሰበር ቅሬታ አቅርቧል፡፡

አመልካች በ15/07/2013 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው የሰበር ቅሬታ ተጠሪ በተደጋጋሚ ለፈጸሙት ጥፋት በ02/08/2011 ዓ.ም. እና በ19/08/2011 ዓ.ም. የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ሰጥተን ሊታረም ባለመቻሉ ከስራ እንዲሰናበቱ መደረጉ ተገቢ ነው፡፡ የሰው እና የሰነድ ማስረጃ አቅርቤ፤ ተጠሪም ለሁለት ጊዜ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው መሆኑን ሳይክዱ ተጠሪ ጥፋተኛ አይደሉም መባላቸው ተገቢ አይደለም፡፡ ተጠሪ የስራ መሪ ናቸው ብለን ያቀረብነው ክርክርም ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎትም የአመልካችን የሰበር ቅሬታ መርምሮ የተጠሪ ስንብት ህገወጥ ነው የመባሉን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1(ሀ-ተ) አላማ እና አተገባበር አንጻር ለማጣራት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በ26/08/2013 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት መልስ አመልካች ቅሬታ ያቀረበው በፍሬ ነገር ክርክር ላይ ነው፡፡ የፍሬ ነገር ክርክሩ በማስረጃ ተጣርቶ የተወሰነ በመሆኑ የተፈጸመ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም በ13/09/2013 ዓ.ም. የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታውን አጠናክሯል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ ተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ለቅሬታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ከተገቢው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ለተጠሪ ስንብት ምክንያት የሆነው ድርጊቱ ተፈጽሟል በተባለ እለት በእንግዶች ቁጥር ልክ ምግብ ሳያዘጋጁ በመቅረታቸው እንግዶች ተገቢውን መስተንግዶ ሳያገኙ በመቅረታቸው የአመልካች መልካም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ስም ጎድፏል በሚል ነው፡፡ ይህ ጥፋት በተጠሪ ተፈጽሞ ከሆነ የአመልካችን መልካም ስም በማጥፋት ደንበኛ እንዲቀንስ በማድረግ በአመልካች ገቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ መሰረት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት የሚያበቃ ጥፋት ነው፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለ እለት ለእንግዶች የተዘጋጀው ምግብ ማነሱን ሳይክዱ ጥፋቱ የእኔ አይደለም በማለት የሚከራከሩ በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው አይደለም የሚለውን እልባት ለመስጠት በእለቱ ተጠሪ እንዲያዘጋጁ በአመልካች በታዘዙት መጠን ልክ ባለማዘጋጀት ጥፋቱን መፈጸም አለመፈጸማቸው በማስረጃ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዚህ ነጥብ ላይ የግራ ቀኙን ምስክር የሰማ ሲሆን የተጠሪ ምስክሮች ተጠሪ ከእንግዶች ቁጥር በላይ 15 በመቶ ትርፍ ምግብ አዘጋጅተው የነበረ መሆኑን፤ እንግዶቹ በሚስተናገዱበት ሚሊኒያም አዳራሽ ሌላ ዝግጅት የነበረ በመሆኑ እና አመልካች ኩፖን አዘጋጅቶ እንግዶችን እየተቆጣጠረ የሚያስገባ ሰራተኛ ባለመመደቡ ለሌላ ዝግጅት የተጠሩ ሰዎች ገብተው በመመገባቸው የተዘጋጀው ምግብ ሊያልቅ መቻሉን አስረድተዋል፡፡ በአንጻሩ በአመልካች በኩል ሁለት ምስክሮች የቀረቡ ቢሆንም አንደኛው ምስክር አመልካች እንግዶችን እየተቆጣጠረ የሚያስገባ ሰራተኛ መመደቡን ሌላኛው የአመልካች ምስክር ደግሞ አመልካች ተቆጣጣሪ አለመመደቡን የመሰከሩ እና የአመልካች ምስክሮች ቃል የተለያየ በመሆኑ ይልቁንም የአመልካች 2ኛ ምስክር ቃል የተጠሪን ምስክሮች ቃል የሚያጠናክር መሆኑን የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ በማስፈር ለእንግዶች የምግብ እጥረት ሊፈጠር የቻለው ተጠሪ በቂ ምግብ ባለማዘጋጀታቸው ሳይሆን አመልካች እንግዶቹን እየተቆጣጠረ ባለማስገባቱ ነው በሚል ስንብቱ ህገወጥ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ድ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 10 ላይ የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን የመጨረሻ ውሳኔዎች ማረም ነው፡፡ በማስረጃ ተጣርቶ ድምዳሜ ላይ የተደረሰባቸውን የፍሬ ነገር ክርክሮች ይህ ችሎት እንደገና የመመዘን ስልጣን አልተሰጠውም፡፡ አመልካች ለተጠሪ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን በመግለጽ የሚያነሳው ክርክር በተመለከተ ተጠሪ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው መሆኑን ባይክዱም እንኳን ለስንብት ምክንያት የሆነውን ጥፋት አለመፈጸማቸው እስከተረጋገጠ ድረስ አስቀድሞ በሌላ ጥፋት ማስጠንቀቂያ መሰጠቱ ስንብቱን ህጋዊ ሊያደርገው አይችልም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ፈጽመዋል የተባለውን ድርጊት አለመፈጸማቸውን ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች እስከተረጋገጠ ድረስ ስንብቱ ህገወጥ ነው መባሉን ይህ ችሎት እንዳለ የሚቀበለው በመሆኑ እና በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሌለ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1ኛ. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 70737 በ23/03/2013 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 250280 በ02/07/2013 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 348/1 መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

<u>ትእዛዝ</u>

በዚህ መዝገብ በ30/07/2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በአፈጻጸም መዝገብ ቁጥር 80332 ላይ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ:- 204829

ቀን:-01/02/2014ዓ/ም

ዳኞች- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች :- ፍቅር አብራክ የእናቶችና የሕፃናት ስፔሻላይዝድ የሕክምና ማዕከል -ወኪል ንጉስ አወቀ ቀረቡ

ተጠሪ :- ዶ/ር ልንገርህ ተፈራ- አልቀረቡም

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ።

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው። የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው ተጠሪ የስር ከሳሽ፤ አመልካች ተከሳሽ ሆኖ ተከራክረዋል። ተጠሪ ያቀረቡት ክስ አመልካች ከሕግ ውጭ የሥራ ውሌን ስላቋረጠ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈል እንዲወሰንልኝ የሚል ነው። አመልካች ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተጠሪ የሥራ መሪ በመሆናቸው ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ በሥራ ክርክር ችሎት ሊታይ አይገባም በማለት ተከራክሯል። የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 92429 አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በፍሬ ነገሩን ክሱን ለመስማት ቀጠሮ ሰጥቷል። አመልካች ባቀረበው ይግባኝ መሠረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ ውሳኔውን አጽንቷል።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ተጠሪ የሥራ መሪ ሆነው እያለ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎትም በዚሁ ነጥብ ላይ ለሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪን ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ ተጠሪ የሥራ መሪ አይደለሁም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ሲደረግ ዋናው ክርክር ሳይጠናቀቅ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ጉዳይ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ባቀረቡት የሥራ ክርክር ላይ አመልካች የሥራ መሪ ናቸው፣ ጉዳዩ በሥራ ክርክር ችሎትና በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ሊታይ አይገባም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ቢሆንም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት መቃወሚያውን ባለመቀበል በፍሬ ነገሩ ጉዳዩን ለመስማት ትእዛዝ ሰጥቷል፤ ሥረ-ነገሩ ላይ ውሳኔ አልሰጠበትም፡፡ አመልካች ይግባኝ ያቀረበው መቃወሚያው ውደቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም በሚል ነው፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡

በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320(3) መሰረት ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ከሥረ ነገሩ ፍርድ በፊት የሚሰጥ ትዕዛዝ እና የጉዳዩ የመጨረሻ ውጤቱ ሲታወቅ አብሮ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ጉዳይ ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደማይቻል ተመልክቷል፡፡ ድንጋጌው በክርክር ሂደት በሚሰጥ ትዕዛዝ ሁሉ ይግባኝ ከቀረበ የተከራካሪዎችን ወጪና ጊዜ የሚያባክን፣ የፍርድ ቤትን ጊዜ የሚወስድ ከመሆኑም በላይ በአንድ ጉዳይ ብዙ ፋይል እንዲኖር የሚያደርግና የሥራ ጫና የሚፈጥር እንዲሁም በይግባኝ ክርክር ምክያንት የሥር ክርክሩ ከታገደም ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት እንዳይቻል የሚያደርግ በመሆኑ ይሕን ለማስቀረት የተቀረጸ ነው፡፡ ጉዳዩ የመጨረሻ ዕልባት ሲያገኝ አብሮ ይግባኝ በማቅረብ ለተከራካሪዎች መብታቸውን ማስከበር የሚችሉበት ሥርዓት ስለሚፈጥር ይግባኝ የማቅረብ መብታቸው ላይ ገደብ እንዳደረገ የሚወሰድ አይደለም፡፡ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውደቅ በመደረጉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲያቀርብ ፍርደ ቤት ዋናው ክርክር ከመጠናቀቁ በፊት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት ይግባኙን ውደቅ ማድረግ ሲገባው የቀረበውን ክርክር ተቀብሎና አከራክሮ ውሳኔውን ማጽናቱ ክርክሩን በሥነ-ሥርዓት ሕጉ አግባብ የመምራትና የመቆጣጠር ኃላፊነቱን አለመወጣቱን የሚያሳይና መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 241335 የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በመደረጉ ያቀረበው ከሥረ-ነገሩ ውሳኔ በፊት ይግባኝ ሊባልበት የሚችል ጉዳይ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- የሥር መዝገብ ይመለስ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሄ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡- 204813እና206556

ቀን፡-30/11/2013ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡-1. ኮ/ል ተክለብርሃን ገ/መድህን

2. ኮ/ል አሰፋ አየለ ይመር

ተጠሪ፡- የደ/ዕዝ ወታደራዊ ዓ/ህግ

በዚህ መዝገብና በሰ/መ/ቁ.206556 የቀረቡት የሰበር አቤቱታዎች በስር ፍርድ በመ/ቁ.24/2013 ከተሰጠው ውሳኔ የተነሱ ክርክሮች በመሆናቸው መዝገቦቹ ተጣምረው ተመርምረው ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የወታደራዊ አገልግሎት ተግባሮችን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን አስመልክቶ ለበላይ አለመታዘዝ እንዲሁም ጠቅላላ የአገልግሎት ደንቦችን መጣስ ወንጀልን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በኢፌዲሪ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የመከላከያ ይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት በመ/ቁ 074/2013 የካቲት 19 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር የቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናት የሰጠውን ፍርድ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ መስከረም 4 ቀን 2013 ዓ.ም በአመልካቾች ላይ በኢፌዴሪ የቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት ባቀረበው የመጀመሪያ ክስ አመልካቾች የመከላከያ ሰራዊት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1100/2011 አንቀጽ 2 (12)፣ የኮቪድ ወረርሽኝ ለመቆጣጠር በወጣው አስቸኳይ አዋጅ ቁጥር 3/2012 በወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና 298/2/ የተደነገገውን በመተላለፍ ሰኔ 23 ቀን 2012 በግምት ከምሽቱ 3፡30 ሲሆን የተደራጁ ህገወጥ ቡድኖች ገጀራ ፣ፌሮ ብረትና ዱላ በመያዝ በሻሸመኔ ከተማ የህብረተሰቡን ንብረት እያቃጠሉ እያወደሙና እየዘረፉ በመሆኑ በክፍሉ አመራር ሜ/ር ጀኔራል ሹማ አብዴታ በስልክ ይህንን ህገወጥ ተግባር ተመጣጣኝ እርምጃ በመውሰድ እንዲቆጣጠሩ እና ህብረተሰቡን እንዲታደጉ የሰጣቸውን ትዕዛዝ በመጣስ ትዕዛዙን ሳይፈጽሙ ቀርተዋል በማለት የከሰሰ ሲሆን፤በሁለተኛው ክስም አመልካቾች የመከላከያ ሰራዊት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1100/2011 አንቀት 2/12፣ የኮቪድ ወረርሽኝ ለመቆጣጠር በወጣው አስቸኳይ አዋጅ ቁጥር 3/2012 እና በኢፌዴሪ ወንጀል ህግ ቁጥር 32/1/ሀ እና 293/2/ የተደነገገውን በመተላለፍ፣ በ1999 ዓ.ም የወጣውን የመከላከያ ሰራዊት ቋሚ የግዳጅ አፈጻጸም ደንብ ቁጥር መከ-002/1999 ተ.ቁ 6.3 እና 7.5 መሰረት ሰራዊቱ ማናቸውም ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ሲደርሱ አደጋውን ለማስቀም ተመጣጣኝ እርምጅ በመውሰድ ህዝቡን ከአደጋ መታደግ እንዳለበት በግልጽ ተደንግጎ እያለ በተደራጁ ህገወጥ ቡድኖች የህብረተሰቡ ህይወት አደጋ ላይ ሲወድቅ ንብረት በከፍተኛ ሁኔታ ሲዘረፍ ሲቃጠል የስር አመልካቾች ግዳጅ ላይ እያሉ በመከላከያ ሀይሎች የአገልግሎት ደንብ መሰረት ተመጣጣኝ እርምጃ በመውሰድ ህብረተሰቡን ከአደጋ ባለመታደጋቸው ጉዳት ሊደርስ ችሏል በማለት ክስ መስርቶባቸዋል፡፡

አመልካቾች ባቀረቡት መቃወሚያም ሰራዊቱ ከኮቪድ ወረርሺኝ ጋር በተያያዘ የመቆጣጠር ትዕዛዝ ስላልተሰጠን በጦርነት ጊዜ የተፈፀመ ወንጀል ነው በሚል መቅረቡ አግባብነት የለውም፤ ሁለቱ ክሶች በአንድ የወንጀል ማድረግ ሀሳብ የተፈጸሙ በመሆናቸው በወ/ህ/ቁ.61(1) መሰረት ተጠቃልለው በአንድ ክስ ስር ሊቀርቡ ይገባል፤ አመልካቾች በአንድ መዝገብ መከሰሳቸው መብታቸውን ለይተው ለመከራከር የማያስችላቸው መሆኑን ጠቅሰው ክሳቸው ተለይቶ እንዲከሰሱ ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡

የኢፌዴሪ የቀዳሚ ወታደራዊ ፍ/ቤት በቀረቡት መቃወሚያዎች ላይ በሰጠው ብይን መቃወሚያዎቹን ውድቅ አድርጎ አመልካቾች እምነት ክህደት ሲጠየቁም ክደው የተከራከሩ በመሆኑ ታህሳስ 16 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የዓ/ህግ ምስክሮችን አስቀርቦ የሰማ ሲሆን 1ኛ የዓ/ህግ ምስክር በሰጠው የምስክርነት ቃልም ከአርቲስት ሀጫሉ ግድያ ጋር በተያያዘ በከተማው እንዳንድ አካባቢዎች የግርግር ምልክት በመኖሩ ወደ 1ኛ አመልካች ሲደውሉ ስላላነሱ ኮ/ል ሰለሞን ለ1ኛ አመልካች ሂዶ ሲነግረው 1ኛ አመልካች መልሶ ሲደውልለት የሁከት ምልክቶች ስላሉ የነገው ስብሰባ ቀርቶ ሰራዊቱ ለግዳጅ ይዘጋጅ ብለው ትዕዛዝ የሰጡት መሆኑን ፤በማግስቱ ጠዋት 12፡30 1ኛ አመልካች ደውሎለት ሜ/ጄ ሰለሞን ደውሎ ነበር ከተማ ውስጥ ቃጠሎዎች ስላሉ ፈጠን ብላችሁ ድረሱ ብሎኛል ታውቃለህ ወይ ሲላቸው ከታዘዛችሁ ግቡ ያላቸው መሆኑን ወደ ሜ/ጄ ሰለሞን ደውሎ ትዕዛዙ የተሰጠ መሆኑን እንዳረጋገጡ፤

ለ1ኛ አመልካች ያለህን መኪና ሰብስበህ በፍጥነት ድረስ ባሉት መሰረት 1ኛ አመልካች ሰራዊቱን በመያዝ ከጧቱ 2፡15 አካባቢ ጥቁር ውሃን ያለፈ መሆኑን በዚህ ጊዜም ለ1ኛ አመልካች ደውለው ምንም ንብረት መቃጠል የለበትም ማስቆም አለባችሁ አመፀኛው የታጠቀ ሀይል አይደለም በዱላ የሚበተን ነው ያሉ መሆኑን አልፎ አልፎ ከ2ኛ አመልካች ጋር ሲገናኙ እንደነበረ፤1ኛ አመልካች ከሽማግሌዎች ጋር እየተነጋገርን ነው በማለት ሲነግራቸው የነበረ ቢሆንም ህብረተሰቡ ስለቃጠሎው መቀጠል ደውሎ ይነግራቸው የነበረ በመሆኑ 1ኛ አመልካችን በስልክ ደውለው አናግረው ድጋሚ ትዕዛዝ የሰጡ ቢሆንም አመራሮቹ ግዴታቸውን ስላልተወጡ ቃጠሎው የቀጠለ መሆኑን፤2ኛ አመልካችን አልፎ አልፎ ቃጠሎ ሲበዛ ይጨቀጭቁት የነበረ መሆኑን እርምጃ ውሰድ ሲሉት ሰው ብዛት አለው ምን ላድርግ ሲላቸው በዱላ የሚበተን ሀይል ነው ያሉት መሆኑን ትዕዛዝ አልቀበልም ግን ያላላቸው መሆኑን፤ በከተማው ውስጥ ጉዳቱ የደረሰው በሰው እጥረት ሳይሆን ቃጠሎውን አመራሮቹ ባለማስቆማቸው መሆኑን ፤በከተማው ውስጥ አስቀድሞ የተጀመረ ቃጠሎ ቢኖርም አብዛኛው ውድመት የደረሰው ሰራዊቱ ከገባ በኋላ መሆኑን፤አመልካቾች 3 ሻለቃ ከ500 የማያንስ ሰው የሚመሩ ሆኖ ከዚህ ውስጥ አንድ ሻምበል ብቻ ግዳጅ ላይ ከመሆኗ ውጪ ሌላው ለግዳጁ የወጣ መሆኑን ቃጠሎውን ያላስቆሙት በሰው እጥረት ሳይሆን መስራት ስላልቻሉ መሆኑን፤1ኛ አመልካች ትዕዛዝ ሲሰጡት ያልተቃወመ ቢሆንም በትዕዛዙ መሰረት ባለመስራቱ ግን ጉዳቱ የደረሰ መሆኑን ፤2ኛ አመልካች በግምገማ ወቀት እርምጃ መውሰድ ጀምረው ያስቆማቸው 1ኛ አመልካች መሆኑን የኦራል ጠባቂ ሆነን ቀረን በማለት የነገራቸው መሆኑን አስረድተዋል፡፡

2ኛ ምስክር የደቡብ ዕዝ ምክትል አዛዥ ሜ/ር ጀኔራል ሰለሞን ኢተፋ ሲሆኑ በሰጡት የምስክርነት ቃልም በእለቱ ከጠዋቱ 12፡10 ሰዓት ሲሆን ለስር 1ኛ ተከሳሽ ደውሎ ችግር መኖሩን ገልጾ በሰው ህይወትና ንብረት ላይ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ሀይል አሰማርተው እንዲያስቆሙት ግዳጅ የሰጣቸው መሆኑን፤1ኛ አመልካች የተሸከርካሪ እጥረት ያለበት መሆኑን ሲገልፅላቸው 5 ፓትሮል የላኩለት መሆኑን፤ከዚያ በኋላ ሂደቱን 1ኛ ምስክር እየተከታተለው ነበር በማለት አስረድተዋል፡፡

3ኛ ምስክር የሻሸመኔ ከተማ ነዋሪና የኢትዮቴሌኮም ሴኩሪቲ ሱፐርቫይዘር መሆኑን ገልጾ አርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳ በመገደሉ ችግር ይፈጠራል በሚል ደቡብ ሪጅን ለሚገኘው አለቃው ደውሎ ያሳወቀ መሆኑን ከለሊቱ 10፡00 ጀምሮ ቃጠሎ እንደጀመረ እና እየሰፋ በመምጣቱ ድጋሚ 1፡00 ሲሆን ለአለቃው እንደደወለለት፣ አለቃው ትንሽ ቆይቶ እንደደወለና ከቶጋ መከላከያ እየመጣ እንደሆነ 1ኛ አመልካች ይመጣልሃል ይህን ስልክ ያዝና ደውልለት እንዳለው፣ ሲደውልም እየመጣን ነው ያሉት መሆኑን መከላከያ ገብቶ ወደ አቦስቶ አልፎ የሄደ መሆኑን ቴሌ አካባቢ ያሉ ቤቶች መቃጠል ሲጀምሩ ለ1ኛ አመልካች ሲደውሉለት እየመጣሁ ነው ይለው የነበረ መሆኑን ቴሌ ማማ ላይ ወጥተው ሲመለከቱ ገጀራ፤ዱላ የያዙት ቤት ሲያቃጥሉ ተዉ የሚላቸው ያልነበረ መሆኑን ንብረቱ ተቃጥሎ ሲያልቅ ሰራዊቱ በርቀት ቆሞ ተመለስ ሲል የነበረ መሆኑን ሰራዊቱ ከጠዋቱ 3፡00 አካባቢ ገብቶ አብዛኛው ንብረት የተቃጠለውም ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 6፡00 ባለው ጊዜ ውሥጥ መሆኑን ፤ ለ1ኛ አመልካች ድጋሚ

ሲደውልም እየመጣሁ ነው ከተማ ውስጥ ነኝ በሚል ሲያናግረው እንደነበር፣ እስከ ቀኑ 5፡00 ሰዓት ድረስ እየደወለለት እነደነበር ከዛ በኋላ ተስፋ በመቁረጥ መደወል እንዳቆመ፣ ሰራዊቱ ጧት 3፡ 00 ጀምሮ እንደገባ ግን ምንም እርምጃ ያልወሰዱ መሆኑን፣ ማታ ሁሉም ነገር ከጠፋ በኋላ ዱላ በመያዝ ማባረር እንደጀመሩ አስረድቷል፡፡

4ኛ ምስክር ሌ/ኮ/ጌታቸው ለማ በቀን 22/10/2012 ዓ.ም ሌሊት 9፡00 ለ1ኛ የስር ተከሳሽ ትዕዛዝ መሰጠቱን ተከትሎ ከስር የሚመራቸውን ሰራዊቶች ዝግጅት እንዲያደርጉ በማድረግ ጠዋት ወደ ከተማው የሄዱ መሆኑን፣ ገጀራና ዱላ የያዘ ሰው እየበዛ ሲሄድ ምስክሩ ለ1ኛ አመልካች እንበትን ሲለው ተው ራሳቸው ይበተናሉ እንዳለው፣እዛው ቆመው ቃጠሎው እየባሰ የሄደ መሆኑን ሰራዊቱ የአመልካቾችን ትዕዛዝ እየተጠባበቀ እስከ ቀኑ 5፡00 ሰዓት ደረስ ቆመው እንደቆዩ 5፡30 ሲሆን አመልካቾች ከአሁን በኋላ መበተን ትችላላችሁ እንዳሉት፣ ከተማ ሲገቡ እየነደዱ የነበሩ ፎቆችና ሆቴሎች እንዲሁም ነደው ያለቁ ህንፃዎች ቢኖሩም እዚያው እያሉ የተቃጠሉም መኖራቸውን ለማሳያነትም የፀጋዬ ህንፃ ከስር ጭስ የነበረው ቢሆንም ተቃጥሎ ያለቀው እዚያው እያሉ መሆኑን፣ 2ኛ አመልካች ግዳጅ መቀበል ያለበት ከ1ኛ አመልካች መሆኑን ገልጾ መስክሯል፡፡

5ኛ ምስክር ደግሞ በጦር ሰፈር የነበረውን ከግዳጅ መልስ ባደረጉት ግምገማ አመልካቾች ግዳጅ ከመፈጸም ይልቅ ከነውጠኛ ጋር ሽምግልና በመያዝ መደራደረ የአመልካቾች ችግር እንደሆነ መገምገሙን መስክሯል፡፡ 6ኛ ምስክር የራሱን አለቃ ሌ/ኮ ጌታቸውን ለምን አንበትናቸውም ሲለው ወደ አመልካቾች ሄዶ አነጋግሮ ሲመለስ ተረጋጉ ትዕዛዝ አየጠበቅን ነው ያለው መሆኑን፣ ነውጠኛው እየጨመረ እና ወደ ምስክሩ ሲቀርቡ ወደ ኋላ ተመለሱ ትዕዛዝ እየጠበቅን ነው በማለት እንደገለጸላቸውና ወደ ኋላ ያፈገፈጉ መሆኑን፣ ከዛም ነውጠኞቹን እንዳሳለፏቸው እነዚህ ያሳለፏቸው አለፍ ብሎ ያለውን ፎቅ ያቃጠሉ መሆኑን ፣ እርምጃ መውሰድ የተጀመረው ከቀኑ 5፡30 በኋላ እንደሆነ አስረድቷል፡፡ ፍ/ቤቱም የዓ/ህግ ምስክሮችን መርምሮ ምስክሮቹና ማስረጃው የዓ/ህግን ክስ ያስረዱ በመሆኑ አመልካቾች እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቷል፡፡

የአመልካቾች 1ኛ ምስክር በመሆን 2ኛ አመልካች ቀርቦ በሰጠው የምስክርነት ቃልም ኮ/ል ከማል በ22/10/2012 ዓም ሌሊት 8፡00-9፡00 ባለው ደውሎ ያንተ ኮሚቴ 1ኛ አመልካች ስልክ አያነሳም ኮ/ል ሹማ ይፈልግሃል ብለህ ንገረው እንዳለው፣ በሰዓቱ ሄዶ ኮ/ል ሹማ እንደሚፈልገው ለ1ኛ አመልካች እንደነገረው የተነጋገሩትን ባያውቅም ከተፈጠረው ችግር ጋር በተያያዘ ተዘጋጁ ስለተባሉ የስራ ክፍፍል አድርገው አድረው ከጠዋቱ 1፡30 ሰራዊት ይዞ መንገድ እያስከፈቱ ሻሸመኔ መግቢያ ላይ ከጠዋቱ 3፡00 የደረሱ መሆኑን 1ኛ አመልካችም የቀረውን ሀይል ይዞ የመጣ መሆኑን፣ እንደደረሱ ንብረት እየተቃጠለና እየወደመ እንደነበር ለኮ/ል ሹማ ሲደውሉ ከተማው ተቃጥሎ አልቋል ለምንድነው የመጣነው አሁን ያሉት ሰዎች ፖስተር ይዘው የሚያለቅሱ ናቸው ምን እናድርግ ሲለው ጠብቁ እደውላለው ያላቸው ሲሆን እና በተደጋጋሚ ከ1ኛ ስር ተከሳሽ ጋር እንደሚደዋወሉ፣ በኋላ 5፡00 አካባቢ

ደውሎ ተመጣጣኝ እርምጅ እንዲወስዱ ደውሎ ለስር 1ኛ ተከሳሽ እንደነገረውና አመልካችም ወደ ተግባር እንደገባ ፤አሳልፈዋቸው ያቃጠሉ ግለሰቦች አለመኖራቸውን አመፅ ከተነሳ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያልተነገራቸው መሆኑን ከታዘዙ በኋላ ግን ግዳጃቸውን የፈፀሙ መሆኑን ወደ ከተማ ከገቡ በኋላ አዲስ የተቃጠለ ነገር ያልተመለከቱ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

2ኛ የመ/ምስክር 1ኛ አመልካች ሲሆን በ22/10/2012 ዓም ሌሊት 2ኛ አመልካች ኮ/ል ሹማ ይፈልግሃል ሲለው ደውሎ ሲያናግረው የተያዘው ስብሰባ ይቅርና አርቲስት ሀጫሉ ስለሞተ ዝግጁ ሁኑ የሚል ትዕዛዝ የተሰጠው መሆኑን፣ ጠዋት 3፡30 ሲሆን የደረሱና ወደ 4፡00 ገደማ ኮ/ል ሲደወልለት ሰላማዊ በሆነ መንገድ ፍቱ ያለው መሆኑን፣ ከቀኑ 5፤00 ሰዓት ላይ እርምጃ እንዲወስዱ ትዕዛዝ የተሰጠው መሆኑን፣ መጀመሪያ ላይ ቀላል የነበርና በቀላሉ መፍትሔ ይገኝ እነደነበር በኋላ ግን ነውጠኛ እየበዛ በመሄዱ አስቸግሯቸው እንደነበር፣በእርምጃ ደረጃ ከታየ የነበረው ያልታጠቀ ስለሆነ ከታጠቀው ሰራዊት አንፃር እርምጃ ለመውሰድ ከአቅም በላይ አለመሆኑን ነገር ግን ሜ/ጀ ሹማ በተቻለ መጠን ህይወት ሳይጠፋ ፍቱ ያላቸው መሆኑን፤እርምጃ እንዲወስዱ ከታዘዙ በኋላ ግን ለ2ኛ አመልካችና ለሻለቃና ሻምበል አመራሮች ትዕዛዝ ሰጥቶ ተግባራዊ መደረጉን አስረድተዋል፡፡

የአመልካቾች 3ኛ የመከላከያ ምስክር በሰጠው የምስክርነት ቃልም በእለቱ ወደ ከተማው ሲደርሱ ከፍተኛ እሳት ስለነበረ እንምታቸው ሲሉ 2ኛ አመልካች ቆዩ ያላቸው መሆኑን፤ከጠዋቱ 3፡20 እስከ 5፡20 ድረስ ቆመው ቆይተው እርምጃ እንድንወስድ ታዘናል ሲሉ ወደ እርምጃ የገቡ መሆኑን ከሰልፈኛው ጋር ከመነጋገር ይልቅ በትነው ማለፍ የነበረባቸው መሆኑን በየደረሱበት ሱቆች እየተቃጠሉ ከመሆኑ ውጪ አዲስ ቃጠሎ አለመኖሩን ያስረዱ ሲሆን ፤4ኛ የመ/ምስክር በበኩላቸው በስፍራው እንደደረሱ ጠሩ ተመጣጣኝ እርምጃ መውሰድ ሲጀምር ቆዩ የተባሉ መሆኑን፤ከደረሱ በኋላ የተቃጠለ ቤት አለመኖሩን፤ለአመልካቾች ከላይ የወረደ ትዕዛዝ ይኑር አይኑር የማያውቅ መሆኑን አስረድቷል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የግራቀኙን ምስክሮች የሠጡትን የምስክርነት ቃል የሰነድ ማስረጃዎችንና የድምፅ ማስረጃዎችን መርምሮ በሰጠው ውሳኔም ተጠሪ ባቀረባቸው ምስክሮች አመልካቾች ገና ከጦር ሰፈራቸው ሲነሱ በሻሸመኔ ከተማ ቃጠሎ የተጀመረ መሆኑ ተነግሯቸው ይህንኑ ቃጠሎና ውድመት እንዲያስቆሙ በሜ/ጀ ሹማ የታዘዙ መሆኑን ትዕዛዙ ለ1ኛ አመልካች በተደጋጋሚ የተሰጠ ቢሆንም 2ኛ አመልካችም የታዘዙ መሆኑን ፤3ኛ ምስክርም እየደረሰ ያለውን ጥፋት መሰረት በማድረግ እንዲደርሱላቸው ቢማፀኑም የንብረት ማቃጠልና የሰው ህይወት ማጥፋት ድርጊቱ የቀጠለ ቢሆንም ሰላማዊ ሰልፍ ነው በማለት የራሳቸውን ትርጉም በመስጠት ትእዛዙን ሳይቃወሙ ግን ትዕዛዙ ወደ ተግባር ተለውጦ የሀገር ሀብት የማዳን ስራ እንዳይሰራ ማድረጋቸውን ማስረዳቱን፤የመከላከያ ምስክሮቹ መጀመሪያም በዱላ በመበተን የሰው ህይወትና ንብረት አድኑ በማለት ከተሰጠው ትዕዛዝ የተለየ ትዕዛዝ መኖሩን ሳያስረዱ ከታዘዝን በኋላ በዱላ እየበተንን የሚቃጠለውን እያስጠፋን ስራችንን ቀጠልን ማለታቸው የተጠሪን ማስረጃ የሚያጠናክር መሆኑን፤ከአመልካቾች ሀላፊነት አንፃር የበላይ አመራር ተመጣጣኝ እርምጃ

እየወሰዳችሁ የህዝብ ንብረት አድኑ ቃጠሎ አስቁሙ ብሎ ማዘዝ ይቅርና በራሳቸውም የስራ ሀላፊነት ከሰራዊቱ የቋሚ ግዳጅ አፈፃፀም ደንብ አንፃር መውሰድ የሚገባቸው መሆኑን፤

1ኛ አመልካች ያቀረበው የስልክ ልውውጥ ድምፅ ቅጂ ከጠዋቱ 4፡14 ከገጠር የመጡት እያቃጠሉ እንደነበረ ለበላይ ሲናገር የነበረ መሆኑን ማስረዳቱ እኛ ከደረስን በኋላ ቃጠሎ አልነበረም በማለት ከገለፁት ጋር የሚቃረን የተጠሪን ማስረጃ የሚያጠናክር መሆኑን፤የድምፅ ቅጂው 4፡14 መጀመሩም አስቀድሞ የተደረገውን ያልያዘ ሆነ ተብሎ የተዘጋጀበትን የሚያሳይ መሆኑን ከረፋዱ 5፡02 እስከ 5፡24 የተቀረፀው ከበላይ አዛዦች ጋር ያለውን የስልክ ልውውጥ ሳይሆን ሆነ ተብሎ ክፍት ተደርጎ የተቀረፀውን መሆኑን ሆነ ብሎ አስቀድሞ በመዘጋጀት የተቀረጣን የሚያሳይ መሆኑን በመጥቀስ በአጠቃላይ አመልካቾች በተጠሪ የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ አለማስተባበላቸውን በመጥቀስ በቀረበባቸው የወንጀል ህግ አንቀጽ መሰረት ጥፋተኛ በማድረግ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ተቀብሎ በመመርመር 1ኛ አመልካች በዘጠኝ አመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት፤2ኛ አመልካች በ6 ዓመት ከ 6 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ በሙሉ ድምጽ የወሰነ ሲሆን ይህ ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ወታደራዊ ፍ/ቤትም ፀንቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡1ኛ አመልካች በሰ/መ/ቁ.204813 መጋቢት 18 ቀን 2013 ዓም በተፃፈ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም አመልካች የተከሰሱት ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ጋር በተያያዘ በተሰጣቸው ግዳጅ አለመሆኑን ከኮቪድ ወረርሺኝ ጋር በተያያዘ የተሰጣቸው የበላይ አመራር ትዕዛዝ እና ጠቅላላ የአገልግሎት ደንብ አለመኖሩን በሰበር መዝገብ ቁጥር 193054 ከተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ ያቀረብነው መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ አግባብ አይደለም፤አመልካች የተሰጣቸውን ትዕዛዝ መጣሳቸው ባልተመሰከረበት፤ሁለቱ ክሶች አብረው ሊሄዱ የማይችሉ ሆነው እያለ አመልካቾች የበላይ አመራር ትዕዛዝ አልፈፀሙም ተብሎ ክስ ቀርቦባቸው እያለ እንደገና በ2ኛው ክስ በራሳቸው ተነሳሽነት እርምጃ መውስድ ነበረባቸው ተብሎ ክስ መቅረቡ አግባብ ባለመሆኑ ምስክር ከተሰማ በኋላም ቢሆን በወ/ህ/ቁ.61(1) መሰረት ተጠቃልሎ በአንደኛ ክስ ስር ሳይቀርብ በሁለቱም ክሶች ጥፋተኛ መባላችን መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፤

የመከላከያ ምስክሮቻችን በቦታው ሲደርሱ ሆቴሎች፤ፎቆችና ሱቆች ተቃጥለው ያለቁና በመቃጠልም ላይ የነበሩ መሆኑን፤እኛ ከደረስን በኋላ እንደ አዲስ ያቃጠሉት አለመኖሩን ሰልፈኞቹ እርማችን ለማውጣት ስለሆነ አሳልፉን ብለው በጠየቁት መሰረት ያለፉ ያደረሱትም ጉዳት አለመኖሩን ትዕዛዝ ከተሰጠን በኋላ እርምጃ በመውሰድ ሰልፉን የበተንን መሆኑን አስረድተው እያለ የቀደመ ትዕዛዝ አለመኖሩን አረጋግጠው መስክረው እያለ ክሱንና ማስረጃውን አላስተባበሉም በሚል የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰጠቱ ቅጣትን አስመልክቶም ሁለቱ ክሶች ወደ ንዑስ 1 ቀይረው ቢያከራክሩ ኖሮ ቅጣቱ ከብዶ የማይወሰን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ቅጣቱ ሲሰላም ለረገርም ጊዜ ሀገራችንን በቁርጠኝነት

ማገልገላችንና በዚህ አገልግሎትም 1ኛ አመልካች ሶስት ጊዜ መቁሰሌ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ቅጣቱ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ካቀረብነው መቃወሚያ አንፃር የተሰጠው ብይን እንዲታረምልኝ፣በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተሽሮ በነፃ እንደሰናበት ይወሰንልኝ ፣ይህ ቢታለፍ ቅጣቱ ከላይ በተመለከቱት ማቅለያዎች አግባብ ቀልሎ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ለአመልካቾች ከበላይ የተሰጣቸው ትዕዛዝ ግልፅ ስለመሆኑና፣የወንጀል ድርጊቶቹን ስለመፈፀማቸው የተረጋገጠበትን አግባብ እንዲሁም ትዕዛዙ እንደ ጦር ሜዳ ግዳጅ ተወስዶ በሁለት ድንጋጌዎች ስር ጥፋተኛ የተባሉበትን አግባብ አግባብነት ካላቸው ህጎች አንፃር ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ለተጠሪ መጥሪያ ደርሶት ሰኔ 10 ቀን 2013 ዓም የተፃፈ መልሱን አቅርቧል፡፡

ተጠሪ በዚህ መልሱም በሁለቱም ክሶች የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ራሳቸውን ችለው የሚቋቋሙ እና ግዙፋዊ ውጤትን የሚያስከትሉ በመሆናቸው ሁለቱም ክሶች ተነጣጥለው መቅረባቸው በአግባቡ ነው፣አንድ የሰራዊት አባል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ለፀጥታ አካላት የሚሰጠውን ግዳጅ በላቀ ውጤት የመፈፀም ግዴታ ያለበት በመሆኑ የተከሰሱባቸው ሁለቱም ወንጀሎች በጦርነት ወቅት እንደተፈፀሙ የሚቆጠሩ በመሆናቸው በወንጀል ህግ አንቀፅ 298(2) እና 293(2) መከሰሱ በአግባቡ ነው፣በወቅቱ በተፈጠረው ህገወጥ ተግባር ምክንያት በሻሸመኔ ከተማ ውስጥ 287 አባወራዎች የተፈናቀሉ፣26 ፎቆችና 179 ቤቶች የተሰባበሩ፣21 ፎቆች 52 መኪናዎች 26 ባጃጆች 40 ሞተር ሳይክሎች 38 ሆቴሎች 23 ሱቆች፣9 ወፍጮ ቤቶችና 196 ቤቶች የተቃጠሉ በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ በመጥቀስ ክሱን ያቀረብን በመሆኑ አመልካች በዚህ ወቅት ከበላይ የተሰጠውን ትዕዛዝ አለመፈፀሙን ያስረዳን በመሆኑ በስር ፍርድ ቤት አግባብነት ያላቸው ማቅለያዎች ተይዘውለት ቅጣቱ የተሰላ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

2ኛ አመልካች ሚያዚያ 19/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም በአንድ ወንጀል ማድረግ ሃሳብ እንደተፈፀሙ የሚቆጠሩ የተቀላቀሉ ድርጊቶችን ነጣጥሎ ሁለት ተደራራቢ ወንጀሎች ክስ ማቅረብ በዚሁ የጥፋተኝነት ፍርድ በአመልካች ላይ ማስተላለፉ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን፣ የወንጀል ድንጋጌዎችን የሚያከብድ ድንጋጌ ስር ለማቅረብ የሚያበቃ ህጋዊ ምክንያት በሌለበት ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት የሌላቸውን የሰራዊቱን ማቋቋሚያ አዋጅ እና ከኮቪድ ወረረሽኝ ጋር በተያያዘ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ መሰረት በማድረግ ክስ መቅረቡ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን፣ በአመልካች ላይ የቀረበው ክስ በስር ፍ/ቤት አብረው ከተከሰሱት የቅርብ አዛዣቸው ክስ ተነጥሎ ያለመቅረቡ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን፣ ተጠሪ በአመልካች ላይ የቀረበውን ክስ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ባላስረዳበት እና አመልካች ባቀረባቸው ማስረጃ በተስተባበለበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ስህተት መሆኑን፣ የቅጣት ውሳኔው በፌ/ጠ/ፍ/ቤት

የወጣውን የቅጣት መመሪያ ቁጥር 2/2006 ተከትሎ ያልተሰጠ መሆኑን በመግለጽ በነጻ እንዲሰናበት ካልሆነ ቅጣቱ እንዲታይላቸው በማመልከታቸው ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአሁን አመልካች አግባብነት ካለው የበላይ አዛዥ ትዕዛዝ የተሰጣቸው ለመሆኑና የቀረበባቸውን የወንጀል ድርጊት ስለመፈጸማቸው የተረጋገጠበት ትዕዙዙም እንደ ጦር ሜዳ ግዳጅ ተወስዶ በወንጀል ህግ አንቀጽ 298/2/ እና 293/2/ ስር በሁለት ህግ ድንጋጌ የጥፋተኝነት እና ቅጣት ውሳኔ የተሰጠበት አግባብነት ከመከላከያ ሰራዊት ማቋቋሚያ አዋጅ 1100/2011 አንቀጽ 2/12/ ፤ የኮቪድ 19 ወረረሽኝ ስርጭት ለመቆጣጠር የወጣው አስቸኳይ አዋጅ ቁጥር 3/2012፣ የወንጀል ህግ ቁጥር 61፣ የኢፌዲሪ የመከላከያ ሰራዊት ቋሚ የግዳጅ አፈጻጸም ደንብ ቁጥር መከ-002/1999 ቁጥር 6.3፣7.5 አንጻር እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ለመመርመር ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በቀን ሰኔ 8/2013 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት መልስ አመልካች የተከሰሰባቸው ወንጀሎች ተደራራቢ መሆናቸውን፣ አመልካች ወንጀሉን በሚያከብድ አንቀጽ መከሰሱ ተገቢ መሆኑን፣ አሰቸኳይ ጊዜ አዋጅ ባለበት ሁኔታ የጸጥታ ሁኔታ በላቀ ሁኔታ ነቅቶ መጠበቅ ሲገባው ግዳጅ ተሰጥቶትም በግዳጁ መሰረት አለመፈጸሙ፣ የተፈጸሙት ሁለቱም ወንጀሎች ጦርነት ባለበት ወቅት እንደተፈጸሙ የሚቆጠሩ መሆኑን፣ አንደኛው ክስ የበላይ አለቃን ትዕዛዝ አለማክበር ራሱን የቻለ ወንጀል ሲሆን 2ኛው ደግሞ የህዝብ ንብረት እየወደመ፣ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት የመከላከል ግዴታ እያለበት ግዴታውን ባለመወጣቱ የተከሰሰው ክስ ራሱን የቻለ ወንጀል መሆኑን፣ ክሱ በሁለቱም በአንድ ላይ የቀረበው ግዳጁ በጋራ የተሰጠና የተከሰሱበት ወንጀል ህግም ተመሳሳይ በመሆኑ መሆኑን፣ ተጠሪ ሁለቱንም ክሶች በበቂ ሁኔታ ያስረዱ መሆናቸውንና አመልካች በማስረጃው ያላስተባበለ መሆኑን፣ የቅጣት ውሳኔ መመሪያውን መጠቀም ነበረባቸው ለሚለው በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መ/ቁ 118227 መመሪያውን የመከተል ግዴታ እንደደለሌበት አስገዳጅ የህግ ትርጉም የተሰጠ መሆኑን፣ በመሆኑም ወንጀሉ በባህሪው ለየት ያለ እና የቅጣት ደረጃ ያልወጣላቸው መሆኑን፣ ጠቅሰው የስር ፍ/ቤት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በአግባቡ በመሆኑ እንዲፀናላቸው ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል እኛም ከሰበር ቅሬታው አኳያ እና ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ይዘት አንፃር የግራ ቀኙን የሰበር ክርክር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡በመሰረቱ በስር ፍርድ ቤት ቀርበው የተሰሙት የተጠሪ ምስክሮች በዋነኝነትም 1ኛ ምስክር ከአርቲስት ሀጫሉ ግድያ ጋር በተያያዘ በከተማው እንዳንድ አካባቢዎች የግርግር ምልክት በመኖሩ በመነሻነት ማታውን በማግስቱ የነበረው ስብሰባ ቀርቶ ሰራዊቱ ለግዳጅ ይዘጋጅ ብለው ማታውን ትዕዛዝ ለ1ኛ አመልካች የሰጡት መሆኑን፤ጠዋቱን አመልካቾች በስራቸው ያለውን ሀይል ይዘው ከካምፓቸው ሲነሱ በሻሸመኔ ከተማ ቃጠሎ የተጀመረ መሆኑ

ተነግሯቸው ይህንኑ ቃጠሎና ውድመት እንዲያስቆሙ በሜ/ጀ ሹማ የታዘዙ መሆኑን ትዕዛዙ ለ1ኛ አመልካች በተደጋጋሚ የተሰጠ ቢሆንም 2ኛ አመልካችም የታዘዙ መሆኑን፤

አመልካቾች ሀይላቸውን ይዘው ወደ ከተማው ሲገቡ ቃጠሎ ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም አብዛኛው ቃጠሎ የደረሰው አመልካቾች የሚመሩት ሀይል ወደ ከተማ ከገባ በኋላ መሆኑን፤በከተማው ውስጥ ጉዳቱ የደረሰው በሰራዊቱ ባለው የሰው ሀይል እጥረት ሳይሆን ቃጠሎውን አመራሮቹ ባለማስቆማቸው መሆኑን ምስክሮቹ ያስረዱ ሲሆን 1ኛ ምስክር ከዚህ በተጨማሪ አመልካቾች ሰራዊቱን እየመሩ ከጠዋቱ 2፡15 ወደ ከተማ ሲገቡ ጀምረው ለ1ኛ አመልካች ደውለው ምንም ንብረት መቃጠል የለበትም ማስቆም አለባችሁ አመፀኛው የታጠቀ ሀይል አይደለም በዱላ የሚበተን ነው ብለው መንገራቸውን ቃጠሎው ሲበዛም 2ኛ አመልካችን ይጨቀጭቁት የነበረ መሆኑን በማስረዳት ከመነሻውም አመልካቾች ወደ ከተማው ሲገቡ በግልፅ የተፈጠረውን ሁከት እንዲያስወግዱ የታዘዙ መሆኑን አመልካቾች ግን ምክንያት እያቀረቡ ትዕዛዙን ሳይፈፅሙ የቀሩ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

አመልካቾች ከራሳቸው ውጪ ለጉዳዩ ገለልተኛ የሆኑ ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን ያቀረቡ ሲሆን ከመነሻውም ለአመልካቾች ከበላይ የተሰጠ ትዕዛዝ መኖር አለመኖሩን አለማወቃቸውን አስረዱ እንጂ የበላይ ትዕዛዝ አለመኖሩን በማረጋገጥ የሰጡት የምስክርነት ቃል የለም፡፡3ኛ እና 4ኛ የመ/ምስክሮች ቃጠሎውን ሲመለከቱ ተመጣጣኝ እርምጃ ለመውሰድ ሲጀምሩ ቆይ መባላቸውን ከማስረዳት ውጪ ተመጣጣኝ እርምጃ መውሰዱ አስፈላጊ የነበረ ከማረጋገጥ ባለፈ አመልካቾች ቆይ ያሏቸው የበላይ ትዕዛዝ ባለመኖሩ መሆኑን አላስረዱም፡፡እኝ ምስክሮች ሰራዊቱ ወደ ከተማ ከገባ በኋላ አዲስ ቃጠሎ አለመኖሩን ያስረዱ ቢሆንም ይህንን የምስክርነት ቃል 1ኛ አመልካች ካስቀረቡት የስልክ ልውውጥ ድምፅ ቅጂ ጋር ስንመረምረው 3ኛ የመ/ምስክር ከጠዋቱ 3፡20 ወደ ከተማው የገቡ መሆኑን አስረድተው እያለ የድምፅ ቅጂው ከጠዋቱ 4፡14 ከገጠር የመጡት እያቃጠሉ እንደነበረ 1ኛ አመልካች ለበላይ ሲናገሩ የነበረ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑ የምስክሮቹ ቃል በመከላከያ ማስረጃነት በቀረበው የድምፅ ቅጂ እንደተስተባበለ ማስረጃን የመስማት፤የመመርምርና የመመዘን ስልጣን ባለው በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ መሆኑን ያሳያል ፡፡

በአጠቃላይ አመልካቾች በእለቱ ሰራዊቱን ይዘው ወደ ከተማ ሲገቡ የተፈጠረውን ሁከት እንዲያሰወግዱ በግልፅ ከበላይ ትዕዛዝ የተሰጣቸው መሆኑን ትዕዛዙን ላለመፈፀም የሰው ሀይል ማነስን በምክንያትነት ያስቀመጡ ቢሆንም በከተማው ውስጥ ጉዳቱ የደረሰው በሰራዊቱ ባለው የሰው ሀይል እጥረት ሳይሆን በተሰጣቸው ትዕዛዝ አግባብ ሰርተው ቃጠሎውን አመራሮቹ ባለማስቆማቸው መሆኑን ተጠሪ ባልተስተባበለ መልኩ ማስረዳቱ ማስረጃን የመስማት፤የመመዘንና የመመርመር ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ነጥብ ነው፡፡

ይህ ፍሬ ነገር በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ከሆነ ደግሞ በቀጣይ ሊመረመር የሚገባው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ድንጋጌ የትኛው ነው የሚለው ይሆናል፡፡በዚህ አግባብም ማንኛውም የመከላከያ

ሰራዊት አባል አስቦ ከበላይ አዛዡ ተግባሩን በሚመለከት በቃል፣በፅሁፍ፣በምልክት ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ በቀጥታ ለራሱ ወይም እርሱ ለሚገኝበት የጦር ክፍል የተሰጠውን ማናቸውንም ትዕዛዝ ሳይፈፅም የቀረ ወይም ለመፈፀም እንቢተኛ ከሆነ ለበላይ ባለመታዘዝ የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ተብሎ ተገቢው የቅጣት ውሳኔ የሚተላለፍበት መሆኑን የወ/ህ/አ.298 (1) ይደነግጋል፡፡በወ/ህ/አ.298(2) ቅጣቱ ከብዶ ሊወሰን የሚችለው ድርጊቱ የተፈፀመው የጦር አደጋ ምልክት በተሰጠበት፣የጦር ክተት በታወጀበት ወይም በጦርነት ጊዜ ከሆነና እንቢተኛነቱም ቁርጠኛ ከሆነ እንደሆነ ድንጋጌው በግልፅ ያሣያል፡፡

በመሰረቱ በህጉ መሰረት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚከናወን የመከለከያ ሰራዊት ግዳጅ የጦር ሜዳ ግዳጅ ተደርጎ የሚወሰድ መሆኑን የኢፌዲሪ መከላከያ ሰራዊት አዋጅ ቁጥር 1100/2011 በአንቀፅ 2(12) የሚደነግግ ሲሆን አሁን በያዝነው ጉዳይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተደርጎ የቀረበው የኮቪድ ወረርሺኝን ለመቆጣጠር የወጣው አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 3/2012 መሆኑን የተጠሪ ክስ ያሳያል፡፡በነዚህ ድንጋጌዎች አግባብ አመልካቾች በወ/ህ/አ.298(2) አግባብ በጦር ሜዳ ግዳጅ ላይ ሆነው ለበላይ አለመታዘዝ የወንጀል ድርጊት ፈፅመዋል ሊባል የሚችለው ከኮቪድ ወረረሽኝ ጋር በቀጥታ በተያያዘ መልኩ አዋጁን ለማስፈፀም አመልካቾች የሚመሩት ሰራዊት በራሱ ብቻውን ወይም ከሌሎች የሀገሪቱ የፀጥታና የደህንነት ተቋማት ጋር ተደራጅቶ በስምሪት ላይ ሆኖ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን በመፈፀም ላይ የነበረ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡አሁን በያዝነው ጉዳይ ለክሱ ምክንያት የሆነው ለበላይ አለመታዘዝ የወንጀል ድርጊት በአመልካቾች የተፈፀመው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን በመፈፀም ላይ እያሉ ስለመሆኑ ክሱም ሆነ ማስረጃው አያሳይም፡፡

ከኮቪድ ወረርሺኝ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ለአመልካቾች በግልፅ ትዕዛዝ የተሰጠ ለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ለክሱ መነሻ የሆነው ሁከት የተፈጠረው የኮቪድ ወረርሺኝ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሀገሪቱ ታውጆ ባለበት ጊዜ ውስጥ ስለሆነ ብቻ አመልካቾች በጦር ሜዳ ግዳጅ ላይ ነበሩ ሊባሉ የሚችሉበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ ከዚህም በተጨማሪ የወ/ህ/አ.298(2) የህጉ መስፈርት ማለትም እንቢተኛነቱ ቁርጠኛ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ከዚህ ይልቅ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች አመልካቾች እንቢተኛ አለመሆናቸውን፣ ሆኖም አሳማኝ ያልሆነ ምክንያት በማቅረብ ትዕዛዙን አለመፈፀማቸውን እያስረዱ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካቾችን በወ/ህ/አ.298(2) ስር ጥፋተኛ በማለት የቅጣት ውሳኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው አመልካቾች ጥፋተኝ ሊባሉ የሚገባው በወ/ህ/አ.298(1) ስር ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ሁለተኛውን ክስ በተመለከተም አመልካቾች በወ/ህ/አ.293 ስር ጥፋተኛ ተብለው የቅጣት ውሳኔ ሊተላለፍባቸው የሚችለው በግልፅ የተሰጠ የበላይ ትዕዛዝ ባይኖርም ከመከላከያ ሰራዊት ቋሚ የግዳጅ አፈፃፀም ደንብ አንፃር በወቅቱ የተፈጠረውን በሰው ህይወትና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከተለውን ሁከት በራሳቸው በሚወስዱት እርምጃ ሊያስቆሙ ሲገባ ይህንን ባለማድረጋቸው የደረሰ ጉዳት መኖሩ

ሲረጋገጥ ሲሆን አሁን በያዝነው ጉዳይ ከበላይ አዛዦች በግልፅ የተሰጠ ትዕዛዝ ስለመኖሩ በተረጋገጠበት በትእዛዙ መሰረት ባለመፈፀማቸውም ከላይ በተመለከተው አግባብ በ1ኛው ክስ ጥፋተኛ በተባሉበት ትዕዛዝ ተሰጥቷችሁ ባለመስራታችሁ የወንጀል ሀላፊነት አለባችሁ እየተባሉ ባትታዘዙም ከመከላከያ ሰራዊት ቋሚ የግዳጅ አፈፃፀም ደንብ አንፃር የወንጀል ሃላፊነት አለባችሁ ተብለው በሁለተኛው ክስ ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ የስር ፍርድ ቤቶች እነዚህን ነጥቦች ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ የሰጡትን ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው በመሻር አመልካቾች ከሁለተኛው ክስ በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ቅጣትን አስመልክቶ አመልካቾች ጥፋተኛ የተባሉበት የወንጀል ድርጊት ከአምስት አመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን ቅጣቱን ለማክበድ የሚያስችል በቂ ምክንያ ያልቀረበ ቢሆንም አመልካቾች በግልፅ የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ባለመፈፀማቸው በሰው ህይወትና አካል ላይ እንዲሁም በንብረቶች ላይ የደረሰውን ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት ፤ትዕዛዙ በቀጥታ በተደጋጋሚ ሲሰጥ የነበረው ለ1ኛ አመልካች መሆኑን እንደሁም ከትዕዛዙ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ያላቸውን የቀደመ ሀላፊነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሌላ በኩል ደግሞ አመልካቾች የተያዘባቸው የቀደመ ሪከርድ አለመኖሩ ያላቸውን መልካም ፀባይ የሚያሳይ መሆኑን፤የቤተሰብ አስተዳዳሪነታቸውን፤ረዥም የውትድርና አገልግሎታቸውንና በዚህ ጊዜም የደረሰባቸውን አካላዊ ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ጊዜ ታስቦ 1ኛ አመልካች በሶስት አመት ፅኑ እስራት ፤2ኛ አመልካች በሁለት አመት ከስድስት ወር ፅኑ አስራት እንዲቀጡ የስር ፍርድ ቤትን የቅጣት ውሳኔ ማሻሻል ፍርድ ሰጥተናል፡፡ስለሆነም የሚከተለው ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1.የቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት የደቡብ ዕዝ ችሎት በመ/ቁ.24/2013 በ16/04/2013 ዓም የሰጠውና ይግባኝ ሰሚችሎቱ በመ/ቁ.074/2013 በ19/06/2013 ዓም በሰጠው ፍርድ ያፀናው የቅጣትና የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ.195 (2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2.አመልካቾች በወ/ህ/አ.298 (1) ስር ለበላይ ባለመታዘዝ የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ናቸው ብለናል፡፡ስለሆነም አመልካቾች በዚህ ጉዳይ የታሰሩበት ጊዜ ታስቦ 1ኛ አመልካች በሶስት አመት ፅኑ እስራት ፤2ኛ አመልካች በሁለት አመት ከስድስት ወር ፅኑ አስራት ሊቀጡ ይገባል ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

1.ማረሚያ ቤቱ በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈፅም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይድረሰው፡፡

2.በዚህ መዝገብ የተሰጠው ውሳኔ ከመዝገብ ቁጥር 206556 ጋር እንዲያያዝ ታዟል፡፡

<u>ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>

ሂ/መ

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

<u>የልዩነት ሃሳብ</u>

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 2 ስር የተሰየምኩት የችሎቱ ዳኛ ከሌሎች ባልደረቦቼ በሚከተለው ምክንያት በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

1. አመልካቾች እየተከራከሩያሉት አገር አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ላይ ብትሆንም የጦርሜዳ ግዳጅ ሊባል አይገባም በሚል በመሆኑ ሰራዊቱ ለግዳጁ እንዲዘጋጅ የግዳጅ አፈፃፀም ካርድ ወጥቶ የነበረ ስለመሆነ በግልጽ በስር ፍ/ቤት ተረጋገጦ ያለ በመሆኑ ይህ የግዳጅ አፈፃፀም ካርድ አልወጣም ግዳጁም ለሰራዊቱ አልወረደም በሚል አመልካቾች የተከራከሩም ሆነ ማስረጃ ባለማቅረባቸውም ከአጠቃላይ ክርክሩ ያላየሁ በመሆኑ፣

   ይህ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የግዳጅ አፈፃፀም ካርድ በሰራዊቱ የተዘጋጀ ስለመሆኑ በክህደት ያልተከራከሩበትና ውድቅ የተደረገ ክርክር ባለመሆኑ ግዳጅ ለሰሪዊቱ እንደተሰጠ የምቆጥረው በመሆኑ፣በጊዜው የኮቪድ 19 አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወጥቆ የነበረው ሰዎች እንዳይቀራረቡ እና በሽታው እንዳይዛመት ከመሆኑ አንፃር በጊዜው የተፈፀመው ነገር ግን ሰዎች በህብረት ሆነው እየዘፈኑ እና እየጮከሩ የነበረ እና በቀጣይም በህብረት ንብረት የማውደምና በሰዎች ህይወት ላይ ጉዳይ እያደረሱ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ የጦር ሜዳ ግዳጅ አይደለም የሚል ክርክር በአመልካዋች የተነሳ ቢሆንም በዚህ አስቸኳይ አዋጅ ከወጣበት አላማ አንፃር አንፃር ስናየው ራሱ አዋጁን የጣሰ ድርጊት የተፈፀመ በመሆኑ፣

   አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የወጣው ለጦርሜዳ አይደለም እንኳን ቢባል ሁለቱም አመልካቾች ግዳጅ ከበላይ ኃላፊያቸው የተቀበሉ መሆኑ ባልተካደበት ይልቁንም ኮ/ል ተክለብርሃን ገ/መድህን በቀጥታ ግዳጁን የተቀበለ መሆኑ፣ በስሩ የሚገኝ ኮ/ል አሰፋ አየለ ግዳጁን ከበላይ ኃላፊው የሰማ እና የቅርብ አለቃውን ኮ/ል ተክለብርሃንን ግዳጁ እንዲፈፀም ሲጠይቀው እንደነበረ፣ ሌሎች የሰራዊቱ አባላትም ለምን እርምጃ አንወስድም እያሉ በተደጋጋሚ ሲጠይቁ የነበረ ቢሆንም ከበላይ ኃላፊያቸው ኮ/ል ተክለብርሃን በቀጥታ እርምጃ እንዲወስዱ ትዕዛዝ ባለመውረዱ ብቻ ወታደራዊ የትዕዛዝ አቀባበል ስርዓቱን ሲጠብቁ በጊዜው ከፍተኛ ጉዳይ የደረሰ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ የመከላከያ ሰራዊት የግዳጃ አፈፃፀም ጉድለት የተፈፀመ እና በሰውና በንብረት ላይ ጉዳይ የደረሰ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ለበላይ ያለመታዘዝ ወንጀል ነው የተፈፀመው ለማለት የማይቻልና ኮ/ል ተክለብርሃን ግዳጁን ተቀብሎ ነገር ግን እንደግዳጁ ያለመፈፀም እና በስሩ ያሉትንም ግዳጁን አውረዶ አደጋውን እንዲታደጉ ያለማድረጉ ግልጽ በመሆኑ በስር ወታደራዊ ፍ/ቤት በኮ/ል ተክለብርሃን ገ/መድህን ላይ የተላለፈው የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ሊሻሻል የሚገባው እና የተጠቀሰውም የህግ ድንጋጌ

ስለማይገባ የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔው ሊፀና የሚገባው ነበር በሚል ከአብላጫው ድምጽ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

2. ኮ/ል አስፋ አየለን አስመልክቶ ግን ምንም አንኳን ግዳጁ ከበላይ ኃላፊያቸው መሰጠቱን ቢያውቅም እንደወታደራዊ የግዳጅ አፈፃፀም ምንም እንኳን ግዳጁ በበላይ ኃላፊ መሰጠቱን ቢስማም ከቅርብ አለቃው ደግሞ በቀጥታ ግዳጁን መቀበል እና ማስማራት ያለበት ከመሆኑ አንፃር በተደጋጋሚም የቅርብ ኃላፊነውን ግዳጁ ሊፈፀም ይገባል በማለት ቢጠይቀም ያልወረደለት በመሆኑ የግዳጁ አወራረዱ ደግሞ የስልጣን ተዋረድን የሚጠይቅ በመሆኑ በቀጥታግዳጁን ተቀብለህ አልፈፀምክም ሊባል የማይገባው በመሆኑ፣ ኮ/ል አሰፋ አየለ ሊጠየቅ የሚገባው ከሆነ ሁሉም በቦታው የነበሩ የሰራዊት አባላት አደጋውን በጊዜው ያላስቆሙት የበላይ ትዕዛዝን እየጠበቁ በመሆኑ ትዕዛዝ መጠበቅ አልነበረባችሁም ተብሎ ሊጠየቁ የሚገባው የነበረ በመሆኑ ከአጠቃላይ በቦታው ላይ ከነበሩ የሰራዊት አባላት ኮ/ል አሰፋ የሚለየው እሱ ከዋናው አዛዥ ግዳጅ መውረዱን በስልክ ስለሰማና ለቅርብ አለቃው አሳውቅ የተባለ በመሆኑ እንጂ እንደማንኛውም ሰላምና ደህንነትን ለመጠበቅ ሰራዊቱን የተቀላቀለ ሁሉ አገር በችግር ውስጥ እየገባች ባለችበትና የህዘብ እና የአካባቢ ሰላም እየደፈረሰ እያየ ዝም ሊል የማይገባው ከመሆኑ አኳያ ከታየ ሁሉም ሊጠየቁ የሚችሉ እንጂ በተለየ ከቅርብ አለቃው ግዳጅ ሳይወርድለት ስላልፈፀመ ጥፋተኛ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ ባለመኖሩ ከቀረበበት ክስ ነፃ ሊወጣ የሚገባው እንጂ ጥፋተኛ ተብሎ ቅጥት ሊወሰንበት አይገባም ነበር በማለት በስር ወታደራዊ ፍ/ቤት የሰጠውንም ይሁን አብላጫው ድምጽ ያሻሻለው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተገቢ አይደለም ብዬ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ሄ/መ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 204746

መስከረም 28 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡-1ኛ. የቂ/ክ/ከ/ወረዳ 10 ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት } አልቀረቡም

2ኛ. የቂ/ክ/ከተማ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት

ተጠሪ፡- አቶ አበበ ደምሴ ካሳ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች በቀን 15/07/2013 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 243668 በቀን 26/05/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልጸው በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻነት ሲሆን አመልካቾች በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከሳሾች የነበሩ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበር፡፡

ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ በቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 10 የሚገኘው የቤት ቁጥር 142/11 አውራሼ ወ/ሮ አሰለፈች ካሳ በግል ጥረትና ገንዘባቸው ያፈሩት ንብረት ሲሆን የካቲት 24 ቀን 1984 ዓም በደብተር ቁጥር 21/09097 በስማቸው ተመዝግቦ ተሰጥቷቸው በአውራሼ ስም ግብር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እየተገበረ ይገኛል፡፡ሆኖም አመልካቾች ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን ያለአግባብ በመያዝ አከራይተው ሊመልሱልኝ አልቻሉም፡፡ስለሆነም በወረዳው ተሸንሽኖ የቤት ቁጥር 140፣ 141 እና 142 የሆነውን ቤት እንዲያስረክቡኝ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካቾች በሰጡት መልስም ተጠሪ ክስ ያቀረበባቸውን ቤቶች መንግስት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ወርሶ እያስተዳደራቸው ያሉ የመንግስት ቤቶች ናቸው፡፡ተጠሪ ቤቶቹ እንዲመለስላቸው ለወቅቱ የአስተዳደር አካል አመልክተው እንዲመለስላቸው ያስወሰኑበትን ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ባለመብት መሆናቸውን የተረጋገጠበትን ውሳኔም አላቀረቡም፤ ደብተሩ እና ግብር የተከፈለበት ደረሰኝ የሚያስረዳው ስለቤት ቁጥር 142/11 እንጂ ክርክር ስለተነሳባቸው ቤቶች አይደለም፡፡ቤቶቹ ያለ አግባብ ከአዋጅ ውጪ ተወርሶብናል የሚል ክስም ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አቅርበው ማስወሰን ይችሉ ነበር፡፡የተጠሪ ጥያቄ በተገቢው ማስረጃ የተረጋገጠ ስላልሆነ ክሱ ውድቅ እንዲደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ከሰማ በኋላ የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ መርምሮ ለተጠሪ አውራሽ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ባለቤትነታቸውን በመቀበል አፅድቆ የሰጣቸውን የባለቤትነት ደብተር በማቅረብ ቤቱ የተፈቀደላቸው መሆኑን ስላስረዱ አመልካቾች በቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 10 የሚገኘው የቤት ቁጥር 140፣141 እና 142 ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት ስላልተገኘ ውሳኔው ተገቢ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም በአጭሩ የስር ፍርድ ቤቶች ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች ለተጠሪ ሊመለሱ ይገባል በሚል ለሰጡት ውሳኔ መነሻ ያደረጉት በተጠሪ በኩል የቀረበውን ደብተር እንደ በቂ ማስረጃ በመቁጠር ሲሆን ደብተር ብቻውን የይዞታ ማረጋገጫ መሆን የማይችል መሆኑን በተመለከተ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ. 170592 በሰጠው ውሳኔ ላይ ደብተር እንደማስረጃ ለመውሰድ ሌሎች ተገቢ ማስረጃዎችን በአንድነት ማገናዘብ እንደሚገባ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች የአውራሻቸው ስለመሆናቸው አግባብ ካለው አካል የተፈቀደላቸው ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ በሌለበት ለረዥም ጊዜ መንግስት ተረክቦ ሲያስተዳድረው የነበረ ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተፈቀደላቸው ስለመሆኑ (በቅፅ 004 ተመላሽ የሆነበት አግባብ በሌለበት) ወይም ከአዋጅ ውጭ ተወስዶብኝል በሚልም ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 110/87 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 572/2000 መሰረት ለቀድሞ የፕራይቬታይዜሽንና

የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ አቤቱታ አቅርበው ውሳኔ አግኝተው ባለመብት መሆናቸውን አላረጋገጡም፡፡

በተጨማሪም አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ቤቶች በተመለከተ ለረዥም ጊዜ እያስተዳደርን ስለመሆኑ በማስረጃ አስደግፈን አረጋግጠን አቅርበን እያለ የስር ፍርድ ቤት ይህን አልፎ የሰጠው ውሳኔ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 14094፣45161፣33924 እና 36320 ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ከተሰጠበት ውሳኔ ጋር ተገናዝቦ ያልተወሰነ እና በበቂ የሕግ ምክንያት ያልተደገፈ በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አመልክተዋል፡፡

ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት መንግስት በአዋጅ ቁጥር 47/67 በመያዝ እያስተዳደረ ባለበት ሁኔታ በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ተጣርቶ ለተጠሪ የተወሰነ ስለመሆኑ ማስረጃ ባልቀረበበት አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክብ የተወሰነበት አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 47/67፣ 572/2000 እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 33924 እና ሌሎች አግባብነት ካላቸው የሕግ ትርጉሞች ጋር በማገናዘብ ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ለተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው መልሳቸው በፅሁፍ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስም በ1984 ዓ.ም ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት እንዲመለስ ተወስኖ ለማስረከብ የተለያዩ አቤቱታ አውራሻችን እያቀረቡ ሳይረከቡ ቆይተዋል፣ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተወረሰበት ሁኔታ አግባብ ያለመሆኑ በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በሚገባ ታይቶ እንዲመለስልን ውሳኔ አግኝቶ በውሳኔው መሰረት ደብተር ተሰጥቶን በስማችን እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ ግብር እየገበርን ቆይተናል፡፡በዚሁ መሰረት ከተጠቀሰው አዋጅ ውጭ የግለሰብ ቤት የሚወረስበት ሕግ አልነበረም፡፡ስለሆነም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት አልተፈፀመበትም በማለት ውሳኔው እንዲፀናልኝ እና የአመልካቾች አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች የመልስ መልሳቸውን አላቀረቡም፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ለረዥም ጊዜ በመንግስት እጅ ሆነው እየተዳደሩ የሚገኙ ቤቶችን በተመለከተ ቤቱ ይለቀቅልኝ የሚለው ወገን ጥያቄውን በቀጥታ ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ የሚችለው ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀፅ 12(2) መሰረት በተገቢው አካል የተፈቀደለት መሆኑን በማስረዳት አልያም ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሳኔ አግኝቶ ባለመብትነቱን ያረጋገጠበትን ማስረጃ በማቅረብ ሊሆን እንደሚገባ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥሮች 14094፣45161 እና በሌሎች ተመሳሳይ መዝገቦች አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡አከራካሪው ቤት(በኋላ በአደረጃጀት ምክንያት ሶስት

የቤት ቁጥሮችን የያዘው) ለረገርም ጊዜ በመንግስት እጅ ሆኖ ሲተዳደር የነበረ መሆኑ ግራ ቀኙ ያልተካካዱበት ነጥብ ሲሆን ተጠሪ ቤቱ ተለቅቆ ልረከብ ይገባል የሚሉት ለአውራሻቸው በተገቢው አካል የተፈቀደላቸው መሆኑን መነሻ በማድረግ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፡፡

ከአዋጅ ቁጥር 47/67 መውጣት በኋላ የሚያዙ ቤቶችን በተመለከተ በህጉ አግባብ መያዛቸው በወቅቱ በነበረው አደረጃጀት በስራና ቤቶች ሚኒስቴር ተጣርቶ ካልፀደቀላቸው አያያዙ የማይፀና መሆኑን የአዋጁ አንቀፅ 12(2) እና 2(16) የጋራ ንባብ ያሳያል፡፡አሁን በያዝነው ጉዳይ ለአከራካሪዎቹ ቤቶች በተጠሪ አውራሽ ስም የኢትዮጲያ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር በ24/06/1980 ዓም የሰጠው ደብተር በተጠሪ የቀረበ መሆኑ ማስረጃን የመስማት፣የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች መረጋገጡ ተጠሪ ቤቶቹ እንዲመለሱላቸው የጠየቁት በተገቢው አካል የተፈቀደላቸው መሆኑን በማስረዳት መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ይህ ከሆነ ደግሞ አከራካሪዎቹን ቤቶች አመልካቾች በመልቀቅ ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መወሰኑና ይህ ውሳኔም በከፍተኛ ፍርድ ቤቱ መፅናቱ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ህግና አስገዳጅ የሰበር ውሳኔዎችን መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላላገኘነው የሚከተለው ተወስኗል፡፡

<u>**ውሳኔ**</u>

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 65683 በቀን 29/11/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 243668 በቀን 26/05/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ፍርድ በማፅናት የሰጠው ፍርድ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ መዝገብ በቀን 21/07/2013 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>**ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ:- 204608

ቀን:-29/02/2014ዓ.ም

ዳኞች:-እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች:- 1) ታጁዲን እንድሪስ

2) የተሁለደሬ ወረዳ እስልምና ጉዳዮች ፅ/ቤት

ተጠሪዎች:- 1)እንድሪስ ሰይድ

2) ዘሙየ የሱፍ

የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ለዚህ ውሣኔ ምክንያት የሆነው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-30456 ጥር 3ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት ቀደም ሲል በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተጣርቶ የቀረበለትን ጉዳይ በመለወጥ እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ስር ፍርድ ቤቱ መመለሱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲወሰንላቸው አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡

ክርክሩ በተጀመረበት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተሁለደሬ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪዎች ከሣሽ የአሁን 1ኛ አመልካች ተከሳሽ እንዲሁም ሁለተኛ አመልካች ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ በይዞታ ማረጋጫ ደብተራቸው ተራቁጥር 2 ላይ ተመዝግቦ የሚገኘውን 0.48 ሔክታር ስፋት ካለው ይዞታቸው ላይ 1ኛ አመልካች የመስጊዱ ተወካይ ነኝ በሚል በወርድ 25 ሜትር በቁመት 60 ሜትር በመግፋት ይዞታቸውን የወሰዱባቸው መሆኑን ይህን መሬት ቢያካራዩት ያገኙት የነበረውን 20 ሽህ ብር ከፍሎ ይዞታውን እንዲመልስላቸው እንዲወሰንበት ክስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው የተጠሪዎችን መሬት ገፍተን አልያዝንም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክር ከመረመረና በማስረጃ ካጣራ በኋላ አመልካቾች የተጠሪዎችን ይዞታ ገፍተው መያዛቸው አልተረጋጠም ሲል የተጠሪዎችን ክስ ውድቅ ያደረገ ቢሆንም የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ አመልካቾች ከተጠሪዎች ይዞታ በጥቅሉ 48 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው መሬት ገፍተው መያዛቸው ተረጋግጧል በሚል እንዲለቁ ወስኗል፡፡ ይህን ውሣኔ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ተደርጎበት ሰበር ሰሚ ችሎቱ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሣኔ በመሻር የተጠሪዎች ይዞታ በሰሜን በኩል የሚያዋስነው መንገድ ነው ወይስ የሁለተኛ አመልካች ይዞታ ነው የሚለው ተጣርቶ እንደወሰን በነጥብ መልሶለታል፡፡ በዚህ መሰረት የወረዳው ፍርድ ቤት የደቡብ ወሎ ዞን የገጠር መሬት አስተዳር መምሪያ በቦታው በመገኘት አጣርቶ እንዲያቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የቀረበለትን ማስረጃ የመሬት ደልዳዮች ከሰጡት ምስክርነት ቃል ጋር በማገናዘብ የተጠሪዎችን ይዞታ በሰሜን በኩል የሚያዋስነው የመስጊዱ ይዞታ መሆኑን ሆኖም ከጠቅላላ ይዞታቸው ላይ አመልካች በደቡብ(ከራሱ ይዞታ) በኩል 70 ሣንቲ ሜትር ወርድ ያለው ይዞታ ግፍቶ ያላዘባቸው ስለመሆኑ ተረጋግጧል ሲል ይህን መሬት አመላከቾች እንዲለቁ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኙት ተጠሪዎች ክርክራቸውን እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ በመዝብ ቁጥር 03-30456 ጥር 3ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት አመልካቾች የተጠሪዎችን መሬት ገፍተው ስለመያዛቸውና አወሣኛቸውም መስጅድ ሣይሆን መንገድ ስለመሆኑ ቀደም ሲል የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-19494 ውሣኔ የሰጠበት መሆኑን፤ የስር ፍርድ ቤቱ እንዲያጣራ የታዘዘው መጠኑን እንጅ አመልካቾች ተጠሪዎችን ይዞታ ገፍተው መያዝ አለመያዛቸውን አለመሆኑን ከዘረዘረ በኋላ በዚህ መሰረት እስከ መንገድ ያለውን ስፋት ያለውን መሬት ካስለከና በሚቀርብለት ውጤት መሰረት አመልካቾች እንዲለቁ መወሰን ሲገባው የተጠሪዎችን ይዞታ ብቻ ለክተው መያዝ ከሚገባቸው 70 ሣንቲ ሜትር ባነሰ ይዘዋል በሚል ስሌት 70 ሣንቲ ሜትር ብቻ እንዲለቀቅቸው መወሰኑ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህን ያልተከተለ ነው ሲል ሽሮ የተጠሪዎች ይዞታ በሰሜን በኩል እስከ መንገዱ ድረስ ተለክቶ መጠኑ ላይ ውሣኔ እንዲሰጥ በድጋሚ በነጥብ መልሶታል፡፡ አመልካቾች ይህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲታረምላቸው ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አመልካቾች መጋቢት 15ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ ዘጠኝ ገፅ የሰበር አቤቱታቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሕግ ከተሰጠው የዳኝነት ስልጣን ውጪ ማስረጃ መዝኖ ውሣኔ መስጠቱ፣ በቀረበለት የሰበር አቤቱታ ዳኝነት እንዲሰጥበት ባልተጠየቀ ጉዳይ ጭብጥ ይዞ መወሰኑ፣ የዞኑ መሬት አስተዳደር የሰጠውን ማስረጃ የማይገባውን የማስረጃ ዋጋ በመስጠት ውሣኔ መስጠቱ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰጠው ውሣኔ የተጠሪዎች ይዞታ አዋሳኝ መንገድ ነው ወይስ መስጅድ ነው የሚለው ነጥብ በማስረጃ ተጣርቶ እንዲወሰን የሰጠውን ውሣኔ ከሕግና ከአመንክዮ ውጪ ሸሮ መጠኑ ብቻ እንዲጣራ ነው የተወሰነው የሚል አቋም በመያዝና በስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን ማስረጃዎች ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር መሰረት ያላደረገ መደምደሚያ በመያዝ መጠኑ ብቻ እንደገና ተጣርቶ እንደወሰን መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል ጉዳዩ ተመልክቶ ተጠሪዎች ይዞታ በሰሜን በኩል እስከ መንገድ ድረስ የሚዋሰን መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ እንዲወሰን በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተጣርቶ የተወሰነው ውሣኔ ሲቀርብለት እንደገና እስከመንገዱ ድረስ በማስለካት አመልካቾች እንዲለቁ እንዲወሰን ሲል ጉዳዩን ወደ ስር ፍርድ ቤት የመመለሱ ተገቢነት ላይ ግራ ቀኙ ክርክር አድርገውበት እንዲወሰን በመታዘዙ የግራቀኙ የፅሁፍ ክርክር ተጠናቋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው ሰኔ 10ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ በሰባት ገፅ የመልስ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡ በጥቅሉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተገቢውን የክርክር አመራር ስነ-ስርዓት የተከተለ መሆኑን ፣ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት የተጠሪዎች አዋሣኝ መንገድ ነው የሚለው ትንሽ መንገድ መሆኑን ለማመልከት እንጅ ዋናውን መንገድ የሚመለከት አይደለም ሲሉ የሚያቀርቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሣ መሆኑን፣ በጠቅሉ አመልካቾች በዚህ ችሎት ከሚያቀርቡት ክርክር አንፃር የስር ፍርድ ቤቱ ውሣኔ የሚነቀፍ አይደለም የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር የአመልካቾች የሰበር ክርክር ውድቅ እንዲደረግላቸው ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው የግራቀኙ ክርክር ተጠናቋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥና የግራ ቀኙን ክርክር ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካቾች የተጠሪዎችን ይዞታ መግፋታቸው በመዝገብ ቁጥር 03-19494 በሆነው ውሣኔ ያገኘ ጉዳይ ነው መጠኑን በሚመለከት እስከ መንገድ ድረስ ያለው ተለክቶ በሚገኘው ውጤት መሰረት አመልካቾች እንዲለቁ እንዲወሰን ሲል ወደ ስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመመለሡ የፈፀመው መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን በጨብጥነት ይዘን የግራ ቀኙን ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው የክርክሩ መነሻ ተጠሪዎች በይዞታ ማረጋገጫ ደብተራቸው ላይ በተራቁጥር 2 ከተመዘገበው ይዞታቸው ላይ አመልካቾች ተገፍቶ ተይዞብናል የሚሉትን ይዞታ ለማስመለስ በቀረበ ክስ ነው፡፡ በዚህ ክስም የሁለተኛ አመልካች አመራር የሆነው አንደኛ አመልካች በወርድ 25 ሜትር በቁመት 60ሜትር

ይዞታቸውን የወሰደባቸው መሆኑንና ይህ ይዞታ ቢከራይ ኖሮ ያስገኝ የነበረውን 20 ሺኅ ብር በመክፈል ይዞታቸውን እንዲለቅላቸው እንዲወሰንበት ጠይቀው በጣልቃገብነት ወደ ክርክሩ የገባው ሁለተኛ አመልካችና 1ኛ አመልካች የተጠሪዎችን ይዞታ ገፍተው አለመያዛቸውን ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን የመረመሩት የስር ፍርድ ቤቶች በሰጡት ውሣኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል በተጠሪዎች የቀረበውን አቤቱታ የመረመረው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር03-19494 በሰጠው ውሣኔ ጉዳዩ እንደገና እንዲጣራ ወስኗል፡፡

በዚህ ችሎት አከራካሪ ከሆኑት ጉዳዮች መካከል አንዱ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-19494 የሰጠው ውሣኔ ይዘትን የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ውሣኔው የተጠሪዎች ይዞታ በሰሜን በኩል የሚዋሰነው ከመንገድ ጋር መሆኑ እና አመልካቾች የተጠሪዎችን ይዞታ መግፋታቸው መደምደሚያ የተደረሰበትና መጣራት የማየስፈልገው መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ መልስ ለመስጠት የክርክሩን አመጣጥ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-30456 በሰጠው ፍርድ የትንተና ክፍል ላይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-19494 በሰጠው ውሣኔ አመልካቾች የተጠሪዎችን ይዞታ መግፋታቸው እና የተጠሪዎች የሰሜን አዋሳኝ መስጅድ ሣይሆን መንገድ ስለመሆኑ ተረጋግጦ ቀደም ሲል ፍርድ የተሰጠበት ጉዳይ መሆኑን ይዘረዝራል፡፡ ሆኖም ይኸው ችሎት እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን ከታዘዘ በኂላ በስር ፍርድ ቤት የቀረቡትን ማስረጃዎች መርምሮ የስር ፍርድ ቤት መደምደሚያ ተገቢነት የለውም ሲል አቋም መያዙን ራሱ የሰጠው ፍርድ ያስገነዝባል፡፡ አንድ ፍርድ ቤት ቀደም ሲል በተሰጠ ውሣኔ መደምደሚያ የተደረሰበት ጉዳይ ነው ካለ ይህንኑ ጉዳይ በማስረጃ የሚያጣራበት ሂደት አለመኖሩ የሚያከራክር አይሆንም፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰጠው ውሣኔ አመልካቾች የተጠሪዎችን ይዞታ መግፋታቸው እና የተጠሪዎችም ይዞታ እስከ መንገድ ድረስ መሆኑ ፍርድ የተሰጠበት ነው ካለ የስር ፍርድ ቤቱ የማስረጃ ምዘን ሂደት ተገቢነት ሊመረምር ባለተገባው ነበር፡፡

ሆኖም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በሰጠው ውሣኔ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት እንደገና በማስረጃ ተጣርቶ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር የተደረሰበት መደምደሚያ ተገቢነት የሌለው ነው ካላቸው መካከል አንዱ የተጠሪዎች አዋሳኝ መስጅድ መሆኑ ተረጋግጧል የተባለው መደምደሚያ ነው፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-19494 በሰጠው ውሣኔ የተጠሪዎች ይዞታ አዋሳኝ መስጅድ ሣይሆን መንገድ መሆኑ መደምደሚያ የተደረሰበት ካለ የስር ፍርድ ቤት እንደገና በማስረጃ አጣርቶ የያዘው አቋም ከቀረበት ማስረጃ አንፃር ተገቢነትን መምርመሩ ቀደም ሲል በተሰጠው ፍርድ የተጠሪዎች ይዞታ በሰሜን በኩል የሚዋሰነው ከመንገድ ጋር ነው ወይስ ከመስጅድ ይዞታ ጋር የሚለው ነጥብ እንዲጣራ ትዕዛዝ የተሰጠበትን ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ሆኖ ሣለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ለሰጠው ፍርድ መደምደሚያ ላይ የደረሰው ተቃርኖ ያላቸውን መንደርደሪያ ሐሳቦች ምክንያቶች በመጠቀም መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የወረዳው ፍርድ ቤትና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት በፍርድ ሐተታቸው ላይ እንዳሰፈሩት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-19494 በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የተጠሪዎች ይዞታ በሰሜን በኩል የሚዋሰነው ከመንገድ ጋር ነው ወይስ ከመስጅድ ይዞታ ጋር ነው የሚለው ነጥብ እንዲጣራ ትዕዛዝ መስጠቱንና በዚሁ መሰረት ያጣሩ መሆናቸውን እንዲሁም ተጠሪዎች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጣቸው ትዕዛዝ በመውጣት አጣርተዋል የሚል ክርክር አለማቅረባቸው ተጠቃሎ ሲታይ ቀደም ሲል በተሰጠው ውሣኔ የተጠሪዎች አወሣኝ መንግድ ስለመሆኑ መደምደሚያ የተደረሰበ

ት ሣይሆን በማስረጃ የሚጣራ ጉዳይ የነበረ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በሌላ በኩል የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝብ ቁጥር 03-19494 የሰጠው ውሣኔ አከራካሪ ቢሆንም እንኳ ክርክሩ በነጥብ ከተመለሰ በኂላ የተጠሪዎች ይዞታ በሰሜን በኩል የሚዋሰነው ከመጅድ ይዞታ ጋር ነው ወይስ ከዋና መንገድ ጋር ነው የሚለው ነጥብ የተጣራበትን ሁኔታና የተደረሰበትን መደምደሚያ ተገቢነት ከሙግት አመራር እና ከማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር መመርምሩ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ እንደገና ከተመለሰለት በኂላ የተጠሪዎች ይዞታ በአመልካቾች ተገፍቶ መያዝ አለመያዙን ለማጣራት እንዲሁም አወሣኙስ ተጠሪዎች እንደሚያቀርቡት መንገድ ነው ወይስ የመስጅዱ ይዞታ የሚለው ነጥብ ላይ ማስረጃዎችን መርምሯል፡፡ በዚህ መሰረት በተጠሪዎች የይዞታ ማረጋገጫ ላይ በተራ ቁጥር ሁለት የተመዘገበው መሬታቸው በሰሜን በኩል ከመንገድ ጋር እንደሚዋሰን የተገለፀ ቢሆንም የዞኑ መሬት አስተዳደር በቦታው ተገኝቶ ባደረገው ማጣራትና የመሬት ደልዳዮች እንዲሁም ሌሎች ምስክሮች በሰጡት ቃል በጥቅሉ ከተጠሪዎች ይዞታና ከዋናው መንገድ መካከል ተጠሪዎች ይዘውት የማያውቁ የመንግስት ይዞታ የነበረ መሆኑን ይህ ይዞታ ቀደም ሲል ለካስ መጫዎቻነት አገልግሎት ይሰጥ የነበረ መሆኑን በኂላም ለኢንቨስትመንት ተሰጥቶ አልሚው በተሰጠው ፈቃድ መሰረት ስላልሰራበት ከእርሱ ተነስቶ ለመስጊዱ የተሰጠ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በአንፃሩ ተጠሪዎች በይዞታ ማረጋገጫ ደብተራቸው ላይ ይዞታቸው በሰሜን በኩል መንገድ የሚያዋስናቸው መሆኑን ተመዝግቦልናል ከሚል ክርክራቸው ውጪ ይዞታውን ይዘው ሲጠቀሙበት የነበረ ይዞታቸው የነበረ ስለመሆኑና በአመልካቾች የተወሰደባቸው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የተሻለ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ በመሆኑም ለአንድ ባለይዞታ የተሰጠ የይዞታ ምስክር ወረቀት ላይ አዋሣኙ መንገድ መሆኑ መጠቀሱ ብቻውን ገለልተኛ በሆኑት የመሬት አስተዳደር አካላት በቦታው ተገኝተው ይዞታውን በመለካት እንዲሁም ተቀባይነት ባላቸው የማጣራት ሂደት ተከትለው ከሚሰጡት ማስረጃ ሁል ጊዜ የተሻለ ክብደት ሊሰጠው የሚገባና የማይስተባል ነው በሚል የሚቀርበው የተጠሪዎች ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀደም ሲል በመዝገብ ቁጥር 03-19494 በሰጠው ውሣኔ ፍፁማዊ አቋም ያልያዘበትን ጉዳይ ማለትም የተጠሪዎች ይዞታ በስተሰሜን በኩል በአመልካቾች ስለመገፋቱና የሚዋሰኑትም ከመንገድ ጋር ስለመሆኑ እንደተረጋገጠ በመገንዘብ ይልቁንም ጉዳዩ በነጥብ

ከተመለሰ በኂል የስር ፍርድ ቤት ባከናወነው የማጣራት ሂደት የተጠሪዎች ይዞታ በሰሜን በኩል የሚዋሰነው ከመንገድ ጋር ሳይሆን ቀደም ሲል ከመንግስት ይዞታ ጋር አሁን ደግሞ ከመስጂድ ይዞታ ጋር ስለመሆኑ በተረጋገጠበት የተጠሪዎች ይዞታ እስከመንገድ የሚዘልቅ ነው በሚል በማስረጃ ያልተረጋገጠ መደምደሚያ እስከመንገዱ ድረስ ተለክቶ የሚገኘውን ውጤት አመልካቾች እንዲለቁ እንዲወሰን ክርክሩን መመለሱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343(1) ድንጋጌንና የማስረጃ ምዘና መርህን ያልተከተለ መሰረታዊ የሕግ ስህተት

የተፈፀመበት ውሣኔ ሆኖ ስላገኘው ተከታዩን ውሣኔ ወስነናል፡፡

ውሣኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-30456 ጥር 3ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዘገብ ቁጥር 46898 በሆነው ህዳር 10ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት የስር የተሁለዴ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15117 በሆነው የካቲት 20ቀን 2012ዓ/ም የሰጠውን ውሣኔ በማፅናት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ይህ የሰበር ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ /መ/ቁ፡- 204300

ቀን፡- መስከረም 28 ቀን 2014ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለስልጣን - ነ/ፈ አሰፋ እሸቱ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ዶ/ር በድሩ ሁሴን

2. ወ/ሮ አዜብ አመልማል — ጠበቃ ማርሻል ፍቅረማርቆስ ቀረቡ

3. አቶ ኪሮስ መሐሪ

4. አቶ ሽፈራው በየነ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 10 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 268995 በቀን 22/12/2012 ዓ.ም አመልካች በመንገድ ሥራ ምክንያት የፈጠረው የሁከት ተግባር እንዲወገድ ሲል የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 259606 በቀን 19/06/2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ሁከት ይወገድልኝ በሚል የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው። በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪዎች ከሳሾች፤ የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል። የአሁን ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በማዕድን እና ኢነርጂ የመኖሪያ ቤት ሥራ ማሕበር በ 1981 ዓ.ም በተሰጠን የማሕበር ይዞታ በቦሌ ክፍለከተማ ወረዳ 14 ክልል ውስጥ ቤት ሰርተን ሕጋዊ ካርታ ተሰጥቶን የምንገለገልበት ይዞታ አለን፤ በመሠራት ላይ ያለው እና በይዞታችን ፊት ለፊት የሚያልፈው መንገድ ፕላን 20 ሜትር ነው፤

አመልካች መንገዱን አሻሽዬ እሰራለሁ በማለት 9ኛ እና 10ኛውን ማስተር ፕላን በሚጻረር ሁኔታ የመንገድ ግንባታውን በማከናወን ከመንገዱ አጋማሽ ጀምሮ የተጠሪዎች ይዞታ በሚገኝበት በመንገዱ ቀኝ በኩል አምስት ሜትር እና በላይ የሚያፈርስ ድርጊት በማከናወን ሁከት የፈጠረ በመሆኑ የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ ይወሰንልን የሚል ነው።

የአሁን አመልካች በሰጠው መልስ ክሱ በድጋሚ የቀረበ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ ደግሞ ከከተማው መሪ ፕላን ውጪ የሠራው ሥራ እንደሌለ በመግለጽ የተጠሪዎች ክስ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራቀኙን በመስማት እና አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ በመስጠት ጉዳዩን ካጣራ በኋላ አመልካች እያናከናወነ ባለው የመንገድ ሥራ ምክንያት የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ ሲል ወስኗል። አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም አቤቱታው በትዕዛዝ ውድቅ ተደርጓል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- ጉዳዩ በድጋሚ የቀረበ ክስ ነው በማለት የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚ ውድቅ የተደረገው አላግባብ ነው፤ በፕላኑ ላይ የቀረበ ቅሬታ ሳይኖር የመንገድ ግንባታው ሕጋዊ ነው? ወይስ አይደለም? በማለት የተያዘው ጭብጥ ተገቢ አይደለም፤ የጸደቀ መሪ ፕላን እያለ የሰው ምስክሮችን በመስማት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕላን እና ልማት ኮሚኒኬሽን መንገዱ እየተሰራ ያለው በጸደቀው የመንገድ ዲዛይን መሠረት መሆኑን መግለጫ ሰጥቶ ባለበት ሁኔታ አመልካች በመንገድ ሥራው ምክንያት የፈጠረው የሁከት ተግባር እንዲወገድ በማለት የመወሰኑን አግባብነት ከ9ኛው እና 10ኛው ማስተር ፕላን እንዲሁም ከጋራ መኖሪያ ቤቶች ሳይት ፕላን ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የተጠሪዎች መልስ ይዘት በአጭሩ፦ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የፍሬነገር እና ማስረጃ ምዘናን የሚመለከት እንጂ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት መመዘኛን አያሟላም፤ የስር ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጠው በአግባቡ አጣርቶ በመሆኑ ውሳኔው ሊጸና ይገባል የሚል ነው።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ የስር ፍርድ ቤት አስቀድሞም ቢሆን በጉዳዩ ላይ ውሳኔ የሰጠው ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን ኖሮት ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል።

የአሁን ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ አመልካች 9ኛ እና 10ኛውን ማስተር ፕላን በሚጻረር ሁኔታ የመንገድ ግንባታ በማከናወን በተጠሪዎች ይዞታ ላይ የፈጠረው የሁከት ተግባር እንዲወገድ የሚል ሲሆን የአመልካች መከራከሪያ ደግሞ የመንገድ ግንባታው በከተማው ማስተር ፕላን መሠረት የሚሠራ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም የሚል ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/1/ሀ የከተማውን መሪ ኘላን አፈፃፀም የሚመለከት የይዞታ ባለመብትነት፣ የፈቃድ አሠጣጥ ወይም የቦታ አጠቃቀምን በተመለከተ በሚነሡ ጉዳዮች ላይ የሚቀርበው ክርክር የከተማው አስተዳደር ፍ/ቤቶች ሥልጣን መሆኑን ይደነግጋል።

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ 9ኛ እና 10ኛውን ማስተር ፕላን በሚጻረር ሁኔታ የመንገድ ግንባታ በማከናወን በተጠሪዎች ይዞታ ላይ የፈጠረው የሁከት ተግባር እንዲወገድ የሚል በመሆኑ እና አመልካችም በከተማው ማስተር ፕላን መሠረት መንገዱን በመገንባት ላይ ያለ መሆኑን በመግለጽ የሚከራከር በመሆኑ የግራቀኙ ክርክር የከተማውን መሪ ኘላን አፈፃፀምን የሚመለከት ነው። በመንገድ ምክንያት ይዞታው ላይ ሁከት የተፈጠረበት ሰው ደግሞ እርምጃው ከሕግ ውጪ ነው የሚል ከሆነ የከተማውን መሪ ፕላን መሠረት ተደርጎ ምላሽ የሚያገኝ እንጂ የይዞታ ባለመብትነትን ብቻ መሰረት በማድረግ በሚቀርብ የሁከት ይወገድልኝ ክስ የሚወሰን ጉዳይ አይደለም። ይህንኑ አስመልክቶም የፌዴራል ጠቅለይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 18552፤ 56273፤100554 እና በሌሎችም መዛግብት አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል።

ስለሆነም ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ከመንገድ ሥራ ጋር በተገናኘ የከተማውን መሪ ፕላን አፈጻጸም የሚመለከት ሆኖ ሳለ ጉዳዩን የማየት የሥረ-ነገር ስልጣን የለኝም በማለት መመለስ ሲገባው አከራክሮ ውሳኔ መስጠቱ፤ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የሥር ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል።

ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 268995 በቀን 22/12/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 259606 በቀን 19/06/2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል።
2. የስር ፍርድ ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የሰጠው ፍርድ የሥረ ነገር ስልጣን ሳይኖረው የተሰጠ ነው በማለት ወስነናል።
3. ተጠሪዎች ያቀረቡትን የሁከት ይወገድልኝ ክስ ሥልጣኑ ለሚፈቅደው ፍርድ ቤት አቅርበው ተገቢውን ዳኝነት የመጠየቅ መብታቸውን ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም።
4. መጋቢት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል። ይጻፍ

   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል። ይመለስ

ሄ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 204264

ህዳር 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት (ኮርፖሬሽን) -አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ተሚማ ፋጂ- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ክርክሩ በገጠር መሬት ይዞታ የመጠቀም መብት ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሳ ለማስከፈል የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የቡኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ተከሳሽ፣ የኢፌድሪ ውሃ፣ መስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ታህሳስ 12 ቀን 2012 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ክስ በቡኖ በደሌ ዞን ጋቺ ወረዳ ዲዴሳ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ በስሜ የተመዘገበ ስፋቱ 2.5 ሄክታር የሆነ ለውዝ እየዘራው የምጠቀምበትን ይዞታ አመልካች ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በመቆፈር የጠጠር ድንጋይ በማውጣት ይዞታው ለየትኛውም አገልግሎት እንዳይውል አድርጎብኛል፡፡ ተጠሪ ከይዞታው በየአመቱ 50 ኩንታል ምርት የማገኝ ሲሆን የአንዱ ኩንታል ዋጋ ብር 1,200 ሁኖ የተለያዩ ወጪዎች ተቀናሽ ተደርጎ የተጣራ አመታዊ ትርፍ ብር 50,000

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አገኛለው፡፡ አመልካች ይህን ጥቅም ስላሳጣኝ እና በዘላቂነት ስላፈናቀለኝ የ10 ዓመት ካሳ ብር 500,000 ወጪና ኪሳራን ጨምሮ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የፕሮጀክቱ ባለቤት የውሃ መስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ስለሆነ ልከሰስ አይገባም፤ ጉዳዩም ከውል ውጪ ግንኙነትን መሰረት ያደረገ ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 2143 መሰረት በይርጋ ይታገዳል፤ የፕሮጀክቱ ባለቤትም ወደ ክሱ ጣልቃ እንዲገባ ይታዘዝልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ በፍሬ ጉዳይ ላይ በሰጠው መልስ አመልካች ከፕሮጀክቱ ባለቤት ጋር ጥር 31 ቀን 2011 እ.አ.አ. ባደረገው የአርጆ ዲዴሳ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ውል አንቀፅ 11(ኤ-1) መሰረት በፕሮጀክቱ አካባቢ ባሉ ባለይዞታዎች ላይ ለሚደርስ ጉዳት አስፈላጊውን ክፍያ ለመፈፀምም ሆነ የስራ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ኃላፊነት ያለበት የፕሮጀክቱ ባለበት ነው፤ ይዞታው ከመጀመሪያው በፕሮጀክቱ ክልል ውስጥ የሚገኝ ጥራት ላለው ድንጋይና ገረጋንቲ ምርት ተለይቶ በአማካሪ መሀንዲሱ የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት የተፈቀደ ነው፡፡ በክሱ እና በይዞታ ማረጋገጫው ላይ የተጠቀሰው የይዞታው ስፋት ልዩነት አለው፡፡ ይዞታውም ለእርሻ የማይውል ድንጋያማ እና ተራራማ ነው፡፡ ለምርት ይውላል ቢባል እንኳ በየአመቱ አንድ አይነት የለውዝ ምርት ብቻ ሊመረትበት አይችልም፡፡ ለምርታማነት የሚያስፈልጉ የምርት ግብዓት ወጪዎች በባለሞያ ሊጣራ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የውሃ መስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴርም ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ታዞ በሰጠው መልስ በፕሮጀክቱ ክልል ውስጥ ለተካተቱ ይዞታዎች ተገቢውን የካሳ ክፍያ መፈጸሙን፤ አከራካሪው ይዞታ ከፕሮጀክቱ ክልል ውጪ የሚገኝ፤ አመልካች በፕሮጀክቱ ባለቤት እና አማካሪ ድርጅት ከተሰጠው ዲዛይን ውጪ በመውጣት አከራካሪውን ይዞታ ቆፍሮ ድንጋይ እና ገረጋንቲ በማውጣት ጥፋት የፈጸመ በመሆኑ ለክሱ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 59979 ቅፅ 11 ላይ እንደታተመው በዚህ መዝገብ ከተያዘው ተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የሚቀርብ ክስ በ2 ዓመት ይርጋ የማይታገድ መሆኑን ገልጾ ውሳኔ ስለሠጠ ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት መቃወሚያውን አልፎታል፡፡ በፍሬ ጉዳይ ላይ የግራ ቀኙን የሰነድ ማስረጃ፣ የሰው ምስክር እንዲሁም ከተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በተውጣጣ ኮሚቴ ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የቀረበውን ማስረጃ መዝኖ የተጠሪ ምስክሮች በይዞታው ላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑን አስረድተዋል፤ የአመልካች ምስክሮችም የተለያዩ ምክንያቶችን ይስጡ እንጂ በተጠሪ ይዞታ ላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑን አልደበቁም፡፡ የጋቺ ወረዳ አስተዳደር ፅ/ቤትም ከተለያዩ መስሪያ ቤት ተወካዮች ጋር በመሆን ጉዳዩን አጣርቶ ከይዞታው ላይ የሚገኘውን የምርት መጠን ግምት እንዲሁም ይዞታውን ወደ ፊት ለምርት አገልግሎት እንዲውል ለማስቻል የተከመረውን አሸዋ ለማስተካከል የሚያስፈልገውን ወጪ ገልጾ ሚያዝያ 30 ቀን 2011 በቁጥር ቲ-33/862/2011 ዓ.ም የፃፈው ደብዳቤ በተጠሪ ይዞታ ላይ ጉዳት መድረሱን አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም አመልካች በፍ/ሕ/ቁጥር 2027(2) እና 2028 መሰረት ኃላፊነት ያለበት ሲሆን አመልካች በፕሮጀክቱ ባለቤት

ከተሰጠው የፕሮጀክቱ ክልል ውጪ በመውጣት ካሳ ባልተከፈለበት ይዞታ ላይ ጉዳት ያደረሰ ስለሆነ ጣልገብ ለክሱ ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስኗል፡፡ የካሳ መጠኑን በሚመለከትም የተለያዩ የሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች የላኩትን ማስረጃ መነሻ በማድረግ በደንብ ቁጥር 135/1999 አንቀፅ 16(2,3) ተጠሪ ባለፉት 5 ዓመታት በአመት በአማካይ የሚያገኙት ብር 39,390 በ10 ተባዝቶ በድምሩ ብር 393,390፣ ውሳኔ ባረፈበት የገንዘብ መጠን ከሚሰላ ከ10 በመቶ የጠበቃ አበል እንዲሁም የዳኝነት ክፍያ ጋር አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ተጠሪ በይዞታቸው ላይ በ2006 ዓ.ም ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ገልፀው ክሱን ያቀረቡት ታህሳስ 12 ቀን 2012 ዓ.ም 2 ዓመት ካለፈ በኂላ ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 2143 እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 20 በታተመው መዝገብ ቁጥር 119563 በሰጠው ውሳኔ መሰረት ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮታል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ ክሱን ያቀረቡት አመልካች ከ2006 ጀምሮ ይዞታቸውን ቆፍሮ ድንጋይ በማውጣት ይዞታው አገልግሎት እንዳይሰጥ በማድረግ ያፈናቀላቸው መሆኑን በመግለፅ ስለሆነ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው ከውል ውጪ ድንጋጌ ሳይሆን የህገ መንግስቱ አንቀፅ 40(8) ሁኖ ተመጣጣኝ ካሳ ሊከፈል የሚገባ ስለመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 11 በታተመው በመ/ቁጥር 59979 ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ በፍሬ ጉዳይ ላይ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ውሳኔ ይስጥ በማለት በነጥብ መልሶታል፡፡

አመልካች መጋቢት 7 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው ይህን የክልሉን የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ ጉዳዩን በመጀመሪያ በተመለከተው የቡኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኢፌድሪ ውሃ መስኖ እና ኢነርጂ ሚስቴር በጣልቃ ገብነት የተከራካሪ በመሆኑ የክልሉ ፍርድ ቤት ጉዳን የተመለከተው በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80(3) መሰረት በውክልና ስልጣኑ ስለሆነ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መመልከቱ ተገቢ አይደለም፤ ይዞታውም ለህዝብ አገልግሎት የዋለ ስላልሆነ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለውን የፍ/ሕ/ቁጥር 2143 በመተው ተፈጻሚነት የሌለውን ውሳኔ መነሻ በማድረግ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የይርጋ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ አከራክሮ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው መሆን? አለመሆኑን? ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ታዟል፡፡

ተጠሪም ግንቦት 23 ቀን 2012 ዓ.ም የተፃፈ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ የመልሱ ይዘት ባጭሩ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ክስ ያቀረብኩት በአመልካች ላይ ነው፤ በአመልካች ጠያቂነት ወደ ክርክሩ የገባው የስር ጣልቃ ገብ ከሃላፊነት ነፃ የተባለ በመሆኑና አመልካችም ጣልቃ ገቡ ነፃ መባሉን በመቃወም ይግባኝ ስላልጠየቀ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ይዞታውንም ለህዝብ ጥቅም ሲባል አመልካች ለም አፈሩን ቆፍሮ በማውጣት በቋሚነት ያፈናቀለኝ ስለሆነ የአዋጅ ቁጥር 455/97፣ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 40(8) እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 59979 በሰጠው አስገዳጅ ትርጉም መሰረት የይርጋው መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም ሰኔ 8 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሱን ያቀረበ ሲሆን የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የመመልከቱን እንዲሁም ክሱ በይርጋ አይታገድም የመባሉን አግባብነት በስር ፍ/ቤት ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በዋናነት የሚከራከረው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም፤ ለክርክሩ ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌም የፍ/ሕ/ቁጥር 2143 ሁኖ እያለ ክሱ በይርጋ አይታገድም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በስር ፍርድ ቤት ክርክር ጣልቃ ገብ የነበረው ተከራካሪ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ ስለተወሰነና አመልካች ይህን በመቃወም ያቀረበው ይግባኝ ስለሌለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ አመልካች ከይዞታው በቋሚነት ያፈናቀለኝ በመሆኑ ክሱ በይርጋ አይታገድም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመጀመሪያ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የመመልከቱን ተገቢነት መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር ተመልክቶ ውሳኔ በሰጠበት ታህሳስ 13 ቀን 2013 ዓ.ም ስራ ላይ በነበረው የፌደራል ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 5(1) መሰረት የፌደራል መንግስት አካል ተከራካሪ የሚሆንባቸውን ጉዳዮች የመመልከት የፍትሐ ብሔር የዳኝነት ስልጣን የፌደራል ፍርድ ቤቶች መሆኑ ተመላክቷል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ በተመለከተው የቡኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ክስ ያቀረቡት በአመልካች ላይ ብቻ በመሆኑ ጉዳዩ ከመነሻው የክልል ጉዳይ ነበር፡፡ ነገር ግን በአመልካች ጠያቂነት የኢ.ፌ.ድ.ሪ. ውሃ መስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ታዞ የክርክሩ ተሳታፊ መሆኑ ጉዳዩን በፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር እንዲወድቅ አድርጎታል፡፡ በክርክሩ መጨረሻ ጣልቃ ገብ ለክሱ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ ተወስኗል፡፡ አመልካች በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሲያቀርብ 2ኛ መልስ ሰጪ ተደርጎ የነበረ ቢሆንም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታ ሲቀርብ ግን ጣልቃ ገብ የነበረው የፌደራል ተቋም በተከራካሪነት

ሳይሰየም ቀርቷል፡፡ ጉዳዩን በፌደራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር እንዲወድቅ አድርጎት የነበረው ምክንያት ማለትም የፌደራል መንግስት ተቋም የነበረው የስር ጣልቃ ገብ ከክርክሩ ውጪ መሆኑ ጉዳዩ የፌደራል መንግስት እንዲሆን ያደረገው ምክንያት ቀሪ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህም ጉዳዩ የክልል ጉዳይ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 16 በታተመው በመዝገብ ቁጥር 95033 ላይ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል መንግስት ተቋም ተከራካሪ ሳይደረግ በተጠሪ በቀረበለት የሰበር አቤቱታ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ መወሰኑ በሌለው ስልጣን ነው የሚያስብል ሁኖ አላገኘነውም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ጉዳይ በተጠሪ የቀረበው ክስ በይርጋ አይታገድም የመባሉ አግባብነት ነው፡፡ ተጠሪ ጉዳዩን በመጀመሪያ በተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሳቸውን የመሰረቱት አመልካች ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ስፋቱ 1.5 ሄክታር የሆነ ለውዝ እያመረቱ የሚገለገሉበትን ይዞታ ቆፍሮ ጠጠር እና ገረጋንቲ በማውጣት ለማንኛውም አገልግሎት እንዳይውል አድርጓል በሚል ነው፡፡ ተጠሪ በክሳቸው ላይ ይዞታው በኢ.ፌ.ድ.ሪ. ውሃ መስኖና እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ባለቤትነት ለሚገነባው የአርጆ ዲዴሳ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት እንዲውል ይዞታው ሙሉ ለሙሉ ተወስዶብኛል በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ የለም፡፡ ክሳቸው በአመልካቹ ድርጊት ይዞታው ለሌላ አገልግሎት እንዳይውል ስለተደረገ አመልካቹ ካሳ ሊከፈለኝ ይገባል የሚል ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካቹ በፕሮጀክቱ ባለቤት እንዲሁም አማካሪው የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ከተሰጠው ዲዛይን ውጪ በመውጣት የተጠሪን ይዞታ በመቆፈር ጠጠር እና ገረጋንቲ በማውጣት ጉዳት ያደረሰ መሆኑ እንዲሁም ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት እንዲቻል ከተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤት በተውጣጡ ባለሞያዎች ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በቀረበው ማስረጃ በይዞታው ላይ የተከመረውን አሸዋ በማሽን በመደልደል ለማስተካከል 7 ሰዓት እንደሚፈጅ እና ለአንድ ሰዓት ብር 3,000 ክፍያ የሚጠይቅ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም የተጠሪ ይዞታ በፕሮጀክቱ ባለቤት ለመስኖ ግድብ ግንባታው የተወሰደባቸው አለመሆኑን እንዲሁም በአመልካች በተፈጸመው ጥፋት በይዞታው ላይ ጉዳት የደረሰ ቢሆንም በግንባታ ማሽኖች ይዞታውን በ7 ሰአታት ውስጥ እንዲስተካከል በማድረግ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ማድረግ የሚቻል መሆኑን የሚያስገነዝብ በመሆኑ ተጠሪ ለሕዝብ አገልግሎት ሲባል ከይዞታቸው በቋሚነት አለመፈናቀላቸውን የሚያመላክት ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በፕሮጀክቱ ምክንያት ከይዞታቸው ለዘለቄታው ተፈናቅለዋል ሊባል አይችልም፡፡

ጉዳዩ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለን ግንኙነት መሰረት በማድረግ አመልካች ከፕሮጀክቱ ክልል ውጪ በመሔድ በይዞታቸው ላይ ያደረሰውን ጉዳት የሚመለከት ከውል ውጪ የሆነን ኃላፊነት የሚያስከትል ስለሆነ ይርጋን በተመለከተ ለክርክሩ ተገቢነት ያለው ድንጋጌ የፍ/ሕ/ቁጥር 2143 ነው፡፡ በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር 1 ስር ተበዳዩ ክስ ማቀረብ ያለበት ካሳ የሚጠይቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በ2 ዓመት ውስጥ መሆን እንዳለበት ተመላክቷል፡፡ ተጠሪ አመልካቹ ይዞታቸውን በመቆፈር ጠጠር እና ገረጋንቲ ማውጣት

የጀመረው 2006 ዓ.ም መሆኑን በክሳቸው የገለጹ ሲሆን ክሱን ያቀረቡት ታህሳስ 12 ቀን 2012 ዓ.ም ድርጊቱ መፈጸሙ ከታወቀ ከ2 ዓመት በኂላ ነው፡፡

ስለዚህ በፍ/ህ/ቁጥር 2143/1 እና በተመሳሳይ ጉዳይ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 20 በታተመው በሰበር መዝገብ ቁጥር 119563 በሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት የተጠሪ የጉዳት ካሳ ክስ በሁለት አመት ውስጥ ባለመቅረቡ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ ውድቅ መደረግ እያለበት ከዚህ በተቃራኒ የሆኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 11 የታተመውን የሰ/መ/ቁጥር 59979 በልማት ምክንያት ከይዞታቸው በቋሚነት እንዲፈናቀሉ የተደረጉ አርሶ አደሮች የሚያቀርቡት የካሳ ይከፈለኝ ክስ ላይ ተግባራዊ መደረግ ያለበትን የይርጋ ጊዜ በሚመለከት የሰጠውን የሕግ ትርጉም በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚ በማድረግ ክሱ በ 2 ዓመት ይርጋ አይታገድም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በአብጫ ድምፅ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ውሳኔ**</u>

1. የቡኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 03498 ሰኔ 20 ቀን 2011 ዓ.ም እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 333952 ታህሳስ 13 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 220314 ጥር 28 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የልዩነት ሃሳብ

ሥሜ በተራ ቁጥር ሦስት ላይ የተሰየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ሃሳብ የተለየሁበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

ኢትዮጵያ የፌደራል የመንግሥት አወቃቀር ሥርዓትን በ1987 ዓ/ም በወጣው የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት መከተሏን ተከትሎ ሥልጣን በክልሎችና በፌደራል መንግሥት የተከፋፈለ ስለመሆኑ በሕገ-መንግሥቱ ከአንቀጽ 50-52 ላይ ተመልክቷል፡፡ በዚህም ክልሎች በሥልጣናቸው ሥር ባሉ ጉዳዮች ሉዓላዊ ሥልጣን አላቸው፡፡ ክልሎች እንደ ፌደራል መንግሥት ሕግ-አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚና የዳኝነት አካል ያደራጃሉ፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 78 መሠረት የዳኝነት አካሉ በፌደራል እና በክልል መንግሥት ደረጃ መቋቋሙ እና በአንቀጽ 80(1)(2) ላይ በፌደራል ጉዳዮች የፌደራል ፍርድ ቤት፤ በክልላዊ ጉዳዮች የክልል ፍርድ ቤት የመጨረሻ ሥልጣን ያለው መሆኑ መመልከቱ በፌደራልና በክልል መንግሥታት መካከል የፍርድ ቤት የሥልጣን ክፍፍል እንዳለ ያሳያል፡፡ የፌደራል ወይም የክልል ጉዳዮች የሚለው በጉዳይ ዓይነት የተከፋፈለ ሥልጣን ስለሆነ የፍርድ ቤቶች ሥልጣን የተለየው የሥረ-ነገር ሥልጣንን መሠረት ያደረገ ቢመስልም ጉዳዩ ከሉዓላዊ ሥልጣን እና ክልላዊ ጉዳይ በፌደራል ፍርድ ቤት ቢታይ ከጣልቃገብነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ጉዳዩ የብሔራዊ ዳኝነት ሥልጣንን የሚያስነሳ ነው፡፡ በፌደራል መዋቅር የብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን መሠረቱ ዓለምአቀፍ ሕግ ሳይሆን ሕገ-መንግሥት ነው፡፡ ሕገ-መንግሥቱ የፌደራልን ሆነ የክልልን ፍርድ ቤቶች ያቋቋመና አክብረው ለማስከበርም ግዴታ የጣለ ነው፡፡ ውጤቱም እንደ ሀገር የሚመረመረው የብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን ከሌላ ሀገር ዜጋ ጋር በተያያዘ እና ሌሎች ሀገሮች ጋር የዲፕሎማቲክ ቅራኔንም ሊፈጥር የሚችል ሲሆን በፌደራልና በክልል መንግሥታት መካከል ያለው ግን በአንድ ሀገር ያሉና በሕገ-መንግሥቱ የሕግ የበላይነትን በማረጋገጥ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማሕበረሰብ ለመፍጠር በሚሠሩ ተቋማትና ዜጎች ላይ፣ የተለያየ ሥልጣን ቢሆንም የጋራ የሆኑ ጉዳዮች ደግሞ ባላቸው ተቋማት መካከል የሚነሳ ስለሆነ የተለየ ያደርገዋል፡፡ በፌደራል መዋቅር የፌደራል መንግሥት ሉዓላዊነቱ

በመላው የኢትዮጵያ ግዛት ነው፡፡ ነገር ግን በግዛቱ ሥር ሁሉንም በፈቃዱ መወሰንና መፈጸም የሚችል ሳይሆን በግልጽ በሕግ በተዘረጋው ሥርዓት ሥልጣኑን የሚጠቀም መሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ለክልል ፍርድ ቤት ሥልጣን መሠረቱ ግን በግዛት ክልል ሥር ያለ ሠውና ንብረት መሆን አለመሆኑን መሠረት ያደረገ (limited sovereignty) ነው፡፡

በሕገ-መንግሥቱ የሥልጣን ክፍፍሉም የክልል ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የፌደራል ጉዳዮችን በውክልና ማየት የሚችሉ ሲሆን ክልላዊ ጉዳዮች በክልሎች ሉዓላዊ ሥልጣን ክልል ውስጥ (exclusive jurisdiction of state courts) ያለ በመሆኑ፤ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3)(ሀ) ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት የተሠጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ማየት አይችሉም፡፡ ይሕም ክልላዊ ጉዳዮች ላይ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ሥልጣን (judicial jurisdiction) የሌላቸው መሆኑን ሲያሳይ በውክልና እና በጣምራ ሥልጣናቸው ከሚመለከቱት በሥተቀር የክልል ፍርድ ቤቶች የፌደራል ጉዳዮችን ማየት አይችሉም፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ መመርመር ያለበት በሕገ-መንግሥቱ የተመለከተው የፍርድ ቤቶች የጣምራነት ሥልጣን (concurrent jurisdiction) እና የፌደራል ጉዳዮች የሚወሰኑበት ሥርዓት ነው፡፡ የፌደራል ጉዳዩች ምን እንደሆኑ በሕገ-መንግሥቱ ያልተወሰነ ቢሆንም በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 3 መሠረት የፌደራል ጉዳዮች ሕገ-መንግሥቱን፣ የፌደራል መንግሥት ሕጎችንና ዓለም አቀፍ ሥምምነቶችን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች (based on laws)፤ በፌደራል ሕግ ተገልጸው በተወሰኑ ባለጉዳዮች (parties) እና በሕግ በተገለጹ ቦታዎች (places) ላይ የሚነሱ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 4 እና 5 መሠረት የተዘረዘሩት የፌደራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት ሥልጣኑ የሚመለከታቸው ሕግንና ባለጉዳዮችን መሠረት አድርጎ የተለዩ የፌደራል ጉዳዮች ሲሆን በሌሎች ሕጎች በግልፅ ለፌደራል ፍርድ ቤት የተሠጡ ጉዳዮችን ይጨምራል፡፡ የአዋጁን አንቀጽ 11 እና ተከታዮችን ሥንመለከት ደግሞ ቦታን መሠረት በማድረግ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች ላይ የሚነሡ ጉዳዮች የፌደራል ፍርድ ቤት የሚመለከታቸው የፌደራል ጉዳዮች ስለመሆናቸው ተደንግጓል፡፡

በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 3 መሠረት ሕግን መሠረት አድርጎ የተለዩት የፌደራል ጉዳዮች ውስጥ የፌደራል መንግሥት ሕጎችን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች ያሉበት በመሆኑና በአዋጁ የትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(3) ላይ የፌደራል መንግሥት ሕጎች ማለት በሕግ በተሠጠው ሥልጣኑ ክልል ሥር ያሉ ነባር ሕጎችን የሚጨመር መሆኑ ሲታይ በሕግ በግልጽ የፌደራል ፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር ከተመለከቱት ሕግን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች እና በፌደራል ሥልጣን ሥር እንዲታዩ ከተወሰኑት ባለጉዳዮች ውጭ ያሉ የፌደራል ሕግን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች የፌደራልና የክልል ፍርድ ቤቶች በጣምራ ሥልጣናቸው የሚመለከቷቸው ናቸው፡፡ ሥለሆነም የፌደራል ሕግን መሠረት ያደረጉ ሌሎች ጉዳዮች እንደተነሱበት ቦታ የፌደራል ፍርድ ቤት ወይም የክልል ፍርድ ቤት በክልላዊ ሥልጣኑ ሊመለከተው ይችላል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ የፌደራል ሥርዓት መሠረት አድርጎ የተዋቀረው የዳኝነት ሥልጣን የፌደራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ካላቸው የጣምራነት ሥልጣን ባለፈ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 78(2) እና 80(4-6) የፌደራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት ሥልጣኑ የሚመለከታቸውን ጉዳዮች የክልል ጠቅላይና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በውክልና እንዲመለከቱ ሥልጣን ሰጥቷል። ይህም ሕገ-መንግሥቱ የክልል ፍርድ ቤቶችን ማብቃትን (empowerment)፣ የክልሎችን ተሳትፎ ማሳደግ ላይ ዓላማ ያለውና ተቋሞቻቸው ላይ አመኔታ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል። በሕገ-መንግሥቱ የዳኝነት አካል በፌደራልና በክልል ደረጃ በየእርከኑ መዋቀሩ ሲታይ አደረጃጀቱ በተዋረድ ያለ የትይዩ አቀራረጽ (dual system) ያለው ቢሆንም የፌደራልና የክልል ጉዳይን የክልል ፍርድ ቤቶች መመልከታቸው የተደባለቀ (integrated system) እንደሚከተልም ያሳያል።

የክልል ፍርድ ቤቶች በጣምራ ሥልጣናቸው በክልል ግዛታቸው የተነሱ ጉዳዮች የመመልከት ሥልጣን ያላቸው በመሆኑ የፌደራል ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አይኖረውም። ጉዳዩ በክልል ፍርድ ቤት የሚታየው ጉዳዩ የተነሳበትን ቦታና ተከራካሪውን መሠረት በማድረግ ነው። የጣምራነት ሥልጣን መሠረቱ የፌደራል መንግሥት ሕግን መሠረት ያደረገ የፌደራል ጉዳይ በመሆኑ የፌደራል ፍርድ ቤት በፌደራል ጉዳይ ላይ ብሔራዊ የመዳኘት ሥልጣን የለውም ሊባል አይችልም። ነገር ግን በፌደራል ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 25/1988 አቀራረጽ መሠረት ከተለዩት ውስን የፌደራል ፍርድ ቤት ሥልጣኖች ውጭ ያሉ በክልል ግዛት የሚነሱ ጉዳዮችን የክልል ፍርድ ቤቶች እንዲመለከቷቸው የተተወ በመሆኑ ጉዳዩ የሥረ-ነገር ሥልጣን ጥያቄ የሚያስነሳ ይሆናል። በተመሳሳይ የክልል ፍርድ ቤቶች በፌደራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት እንዲታዩ የተለዩ ጉዳዮችን (exclusive jurisdiction) በግዛታቸው በተከሠቱ ጉዳዮች፣ ባሉ ሠዎች ወይም ንብረቶች ጋር የሚነሱ ሲሆን በውክልና (delegation) እንዲመለከቱ በሕገ-መንግሥት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል። የክልል ፍርድ ቤቶች በግዛታቸው ባሉ ሠዎች ወይም ንብረቶች ጋር የሚነሳ የፌደራል ጉዳይን ውክልናቸው እስካልተነሳ ድረስ የመመልከት ሥልጣን አላቸው።

በዚህም መሠረት በተያዘው ጉዳይ በግራቀኙ ክርክር በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የኢፌዴሪ ውሃ፣ መስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር በክርክሩ በጣልቃገብነትና በመልስ ሰጭነት ተከራክሯል። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የፌደራል መንግሥት አካል በመሆኑ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(1) መሠረት ክርክሩ የፌደራል ጉዳይ ሆኗል። የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክሩን የተመለከተውም የፌደራል ጉዳይን በውክልና የማየት ሥልጣን ያለው በመሆኑ ነው። የአመልካች ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከታየ በኋላ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ሊመከተው አይችልም። የክልል ሠበር ሰሚ ችሎቶች በክልላዊ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 80(3)(ለ) ላይ ተመልክቷል። የክልል ፍርድ ቤቶች በውክልና የሚመለከቷቸው ጉዳዮች የፌደራል ጉዳዮች በመሆናቸው የክልል ሠበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አይኖረውም።

ጉዳዩን የፌደራል ያደረገው ተከራካሪ በክርክሩ አለመሳተፉ ጉዳዩን መልሶ ክልላዊ ጉዳይ አያደርገውም፡፡ ጉዳዩ የፌደራል የሆነው በጉዳዩ ዓይነት ወይም በተከራካሪዎች አድራሻ ወይም በተከራካሪዎች ማንነት ቢሆንም ጉዳዩ አንዴ የፌደራል ጉዳይ ከሆነ እስከመጨረሻው በፌደራል ፍርድ ቤት ወይም የፌደራል ጉዳይን በውክልና ለመመልከት ሥልጣን ባላቸው የክልል ፍርድ ቤቶች ሊታይ የሚችል የፌደራል ጉዳይ እንጂ የውክልና ሥልጣን በሌለው ፍርድ ቤት ወይም ችሎት ሊታይ የሚችል ክልላዊ ጉዳይ ሊሆን አይችልም፡፡ ጉዳዩ የፌደራል ወይም ክልላዊ ጉዳይ መሆን አለመሆን በሕገ-መንግሥቱ ከተቀረጸው የፌደራል አወቃቀርና ከፌደራል መንግስት ሆነ ከክልሎች ሥልጣን ጋር ግንኙነት ያለው በመሆኑ አንድ ጉዳይ በፌደራል መንግሥቱ ሥልጣን ሥር ካረፈ በኋላ ተመልሶ ጉዳዩ የክልል መንግሥት ሥልጣን የሚሆንበት ሥርዓት ሊፈጠር አይችልም፡፡ ሥለሆነም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በተጠሪ የቀረበው የሠበር አቤቱታን ለመመልከት ሥልጣን የለኝም በማለት መወሰን ሲገባው የሰበር አቤቱታውን መመልከቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻሩ ተጠሪ ጉዳዩ ላይ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 321(2) መሠረት በሁለተኛ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የማቅረብ መብት ያላቸው በመሆኑና ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት ስለሆነ በሥረ-ነገሩ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊመረመር አይገባም በማለት በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

ማ/አ   የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 204140
መስከረም 28 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ዘላለም አማረ - ከጠበቃ አሸናፊ ጌታቸው ጋር ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ አዜብ ወዳጆ
2. አቶ ግርማ አያሌው
3. አቶ ፋሲካ ባራኪ
4. ወ/ሮ አስቴር ወዳጆ
} አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 08 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ፡- የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 64514 ጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 261539 መጋቢት 02 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የቤት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪዎች ከሳሾች፤ የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ሟች እናታቸው ወ/ሮ እልፍነሽ በቀለ በቀድሞ አጠራር ከፍተኛ 21 ቀበሌ 19 አካባቢ በመንግስት ቦታ ላይ በግላቸው የገነቡት ቤት በልማት ምክንያት ሲፈርስ በአሁኑ አጠራር ቂርቆስ ክፍለከተማ ወረዳ 06 ቤ.ቁ የሌለውን 4 በ 3 የሆነ ቤት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በ 1999 ዓ.ም የሰሩ መሆኑን፤ እናታቸው በመታመማቸው ምክንያት ወደ 1ኛ ተጠሪ ቤት ሲመጡ በብር 600 ቤቱን ለአመልካች ያከራዩት መሆኑን፤ አመልካችም የቤቱን ኪራይ በ1ኛ ተጠሪ ስም በተከፈተ የነባክ ሂሳብ እስከ መጋቢት ወር 2010 ዓ.ም ድረስ ሲከፍል ቆይቶ ከሚያዝያ ወር 2010 ዓ.ም ጀምሮ ኪራዩን መክፈል ያቆመ መሆኑን በመግለጽ ያልከፈለውን ውዝፍ የቤት ኪራይ እንዲከፍል፤ ቤቱን ሲከራይ በቤቱ ውስጥ የነበረውን ቁምሳጥን እና ምንጣፍ በአይነት እንዲመልስ ወይም ግምቱን እንዲከፍል እና ቤቱን እንዲያስረክባቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በሰጡት መልስ የተጠሪዎች እናት ቤቱን አልሰሩም፤ አመልካች የወረዳው የቀድሞ አመራሮች ፈቅደውልኝ ቆሻሻውን አጽድቼ በመንግስት ባዶ ቦታ ላይ የሰራሁት ቤት ነው፤ ቤቱን በ1999 ዓ.ም ሰርቼ የተጠሪዎችን እናት በሰብአዊነት አስጠግቻቸዋለሁ፤ በልማት ምክንያት ቤት ሲፈር የሚሰጠው የኮንዶሚንየም ቤት ወይም የቀበሌ ቤት ነው፤ የተጠሪዎች እናት ለአመልካች የሰጡት ቁምሳጥን እና ምንጣፍ የለም፤ እናታቸው በሕይወት በነበሩ ጊዜ ያፈሩት ገንዘብ እንዳይጠፋ እና እንዳይሰረቅ በአደራ በእኔ እጅ እንዲቀመጥላቸው ብር 12,000 ሰጥተውኛል፤ እናታቸው ባስፈለጋቸው ጊዜ ብሩን ሲሰጣቸው ነበር፤ እናታቸው ሲታመሙ ተጠሪዎቸ አንድም ቀን ሳይጠይቋቸው ወደ 1ኛ ተጠሪ ቤት ስለወሰዷቸው በ1ኛ ተጠሪ ስም በተከፈተ ሂሳብ በየጊዜው የራሳቸውን ገንዘብ ስልክላቸው ነበር፤ ከወረዳው ተገኘ የተባለው የግንባታ ፈቃድ ሀሰተኛ ነው፤ ስለሆነም ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ እና ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ ቤቱ የተሰራው ያለግንባታ ፈቃድ መሆኑ መረዳት ተችሏል፤ የተጠሪዎች ምስክሮች የአፍሪካ ሕብረት የማስፋፊያ ስራ ሲሰራ የተጠሪዎቸ እናት ቤት እና የሌሎቹም ቤት እንዲፈርስ ሲደረግ ሕጋዊ ሰነድ ያላቸውን መንግስት ምትክ ቦታ እና ካሳ ሲሰጣቸው በቀበሌ ቤት የሚኖሩትን ደግሞ ሌላ የቀበሌ ቤት ተሰጥቷቸዋል፤ እንደ ተጠሪዎች እናት ያሉትን ሕጋዊ ማስረጃ የሌላቸውን ደግሞ በቡልጋሪያ አካባቢ ወንዝ ዳርቻ ቆሻሻ አጽድተው እንዲሰሩ ተፈቅዶላቸው የተጠሪዎች እናት በ1999 ዓ.ም ይህን ቤት እንደሰሩ፤ እናታቸው ሲታመሙ 1ኛ ተጠሪ እንደወሰዷቸው እና ቤቱን ለአመልካች እንዳከራዩት፤ ኪራዩንም ቤት እየመጣ ሲከፍል ቆይቶ በኋላ ላይ በ1ኛ ተጠሪ ስም በተከፈተ የባንክ ሒሳብ ሲያስገባ እንደነበር የተጠሪዎች ምስክሮች አስረድተዋል፤ በማስረጃነት የቀረበው የባንክ ደብተርም አመልካች በየወሩ ብር 600 አልፎ አልፎ ብር 1200 ሲከፍል እንደነበር ያሳያል፤ የተጠሪዎች እናት ልጆቻቸው እያሉ በስጋም ሆነ በጋብቻ ለማይዛመዳቸው አመልካች ገንዘቡን በአደራ ይሰጣሉ ተብሎ ስለማይገመት አመልካች ይህንኑ ለማስረዳት ያቀረባቸው ምስክሮች ቃል እምነት የሚጣልበት አይደለም፤ ስለሆነም አመልካች ያልከፈለውን የቤት ኪራይ ከሚያዝያ 2010 ጀምሮ እስከ ጥር 2011 ድረስ ያለውን ብር 6000 / ስድስት ሺህ / ከፍሎ ቤቱን ለቆ ለተጠሪዎች እንዲያስረክብ በማለት የወሰነ ሲሆን ምንጣፉን እና ቁምሳጥኑን በሚመለከት የቀረበውን ጥያቄ ተጠሪዎች አላስረዱም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይህ ውሳኔ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ጸንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች ያቀረብኩት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ አግባብ አይደለም፤ ተጠሪዎች ቤቱን በሚመለከት ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ የለም፤ የግራቀኛችን ክርክር እና ማስረጃ በአግባቡ አልተመዘነም፤ ከወሳኝ ኩነት መጣ የተባለው ሰነድ ሀሰተኛ ነው፤ ቤቱን በሚመለከት የቀረበ በቂ የሆነ የሰነድ ማስረጃ እስከሌለ ድረስ ጉዳዩ የሚመለከተው አካል ማብራሪያ እንዲሰጥበት በማድረግ ሊወሰን ይገባው ነበር፤ ስለሆነም ይህ ታልፎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የአሁን ተጠሪዎች ስለመሆኑ ከሚመለከተው አካል የተመዘገበበ የሰነድ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ አመልካች አከራካሪውን ቤት ለተጠሪዎች እንዲያስረክብ የመወሰኑን አግባብነት ከመሠረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆዎች ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪዎች መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያቀረባቸው መቃወሚያዎች መታለፋቸው ተገቢ ነው፤ የስር ፍርድ ቤት በጉደዩ ላይ ውሳኔ የሰጠው የግራቀቀኛችንን ክርክር እና ማስረጃ በአግባብ መርምሮ እና መዝኖ በመሆኑ ውሳኔው ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊታረም ይገባል በማለት የሚከራከሩት አመልካች የወረዳው የቀድሞ አመራሮች ፈቅደውልኝ ቆሻሻውን አጽድቼ በመንግስት ባዶ ቦታ ላይ የሰራሁት ቤት ነው፤ የተጠሪዎችን እናት በሰብአዊነት ያስጠጋኋቸው እንጂ ቤቱን አልሰሩም ለአመልካችም አላከራዩም፤ ተጠሪዎችም ቤቱ በእናታቸው የተሰራ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረቡም በሚል ነው፡፡ አመልካች በዚህ አግባብ የሚከራከሩ ቢሆንም ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች በልማት ምክንያት የተጠሪዎቸ እናት ቤት እና ሌሎችም በአካባቢው ያሉት ቤቶች ሲፈርሱ በወቅቱ ሕጋዊ ማስረጃ ለነበራቸው ምትክ ቤት የተሰጠ መሆኑን፤ እንደ ተጠሪዎች እናት ያሉ ሕጋዊ ማስረጃ የሌላቸው ደግሞ በቡልጋሪያ አካባቢ ያለውን የወንዝ ዳርቻ አጽድተው እንዲሰሩ ተፈቅዶላቸው የተጠሪዎች እናት በ1999 ዓ.ም ይህን ቤት እንደሰሩ ቤቱን የሰሩ መሆኑን፤ የተጠሪዎች እናት ሲታመሙም ወደ 1ኛ ተጠሪ ቤት የተወሰዱ እና ለአመልካች በብር 600 / ስድስት መቶ / ቤቱን ያከራዩት መሆኑን እና ኪራዩን በእጅ እና በባንክ ሒሳብ ሲከፍል የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/1 መሠረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የለውም፡፡

የተጠሪዎች እናት አከራካሪ የሆነውን ቤት ሰርተው በሕመም ምክንያት ልጃቸው ወደ ሆኑት 1ኛ ተጠሪ ቤት ሲሄዱ ለአመልካች በብር 600 / ስድስት መቶ ብር / የተከራየ ስለመሆኑ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ እና ይህ ችሎትም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የሌለው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠውን ፍሬነገር መሠረት በማድረግ አመልካች ያልከፈሉትን ውዝፍ የቤት ኪራይ ከፍለው አከራካሪውን ቤት ለተጠሪዎች ሊያስረክቡት ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 64514 ጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 261539 መጋቢት 02 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ፡-204074

ቀን፡-29/03/2014ዓ.ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ኑረዲን ከድር

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- በደሴ ከተማ የሆጤ ክፍለ ከተማ አስተዳደር - አልቀረቡም

ተጠሪዎች ፡- 1ኛ. የወ/ሮ ማሚቴ ሁሴን ወራሾች - አልቀረቡም

1ኛ. አያል አብርሃ

2ኛ. መዓዛ አብርሃ

3ኛ. ገነት አብርሃ

4ኛ. ዳኛቸው አብርሃ

5ኛ. ቴዎድሮስ አብርሃ

6ኛ. ዋሲሁን አብርሃ

2ኛ. አቶ ሽፈራው ሰይድ- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ክርክሩ የመንግስት የንግድ ቤትን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ተከሳሽ እንዲሁም 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

1ኛ ተጠሪ ግንቦት 13 ቀን 2010 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡተ ክስ 2ኛ ተጠሪ በሆጤ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥሩ 200 የሆነን የንግድ ቤት ከአመልካች ተከራይቶ ሲጠቀምበት ቆይቶ በእሳት አደጋ ሙሉ ለሙሉ በመውደሙ ምክንያት ከአመልካች ፍቃድ ተሰጥቶት ብር 500,000 ከራሱ ወጪ በማድረግ ምድር ቤት እና 18 መኝታ ቤት (አልቤርጎ) ያለው ፎቅ ገንብቶ እስከ 2008 ዓ.ም ሲገለገልበት ቆይቷል፡፡ 2ኛ ተጠሪ የንግድ ቤቱን የግል ንብረቱ በማስመሰል የቤት ቁጥሩ 196 ከሆነ ሌላ የግል ንብረቱ ጋር አጠቃሎ በብር 1.8 ሚሊዮን ሸጦልኛል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ግዢውን በቅን ልቦና ያከናወንኩ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ የንግድ ቤቱን ስመ ሀብት እንዲያዞርልኝ ክስ መስርቼ የከተማው ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12269 ውሳኔ ከሰጠ በኋላ አመልካች የፍርድ መቃወሚያ በማቅረቡ የንግድ ቤቱ የአመልካች ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ በሌላ በኩል 2ኛ ተጠሪ ለንግድ ቤቱ ግንባታ ያወጣው ወጪ በኪራይ እንዲካካስለት በደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 105/2009 አመልካች ላይ ክስ መስርቶ በኪራይ ውል የይካካስልኝ ጥያቄ የማቅረብ መብት እንዳለው የተረጋገጠ ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በመዝገብ ቁጥር 26087 2ኛ ተጠሪ የንግድ ቤቱን በኪራይ ይዞ መገልገል እንደሚችል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ 1ኛ ተጠሪ የንግድ ቤቱን በቅን ልቦና የገዛው ስለሆነ 2ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ የሚኖሩትን መብቶች በእሱ እግር በመተካት የመጠየቅ መብት አለኝ፡፡ የንግድ ቤቱ በአሁን ሰዓት የ1ኛ ተጠሪ ከሆነው የቤት ቁጥሩ 196 ጋር የተያያዘ፣ የራሱ መውጫና መግቢያ በር የሌለው፣ የቤት ቁጥሩ 196 የሆነው ቤት ኩሽና እና ሽንት ቤት ከንግድ ቤቱ ጋር ተቀጣጥለው የተሰሩ በመሆኑ አመልካች የንግድ ቤቱን ለሌላ ሰው ማከራየት አይችልም፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተጠሪ የንግድ ቤቱን በኪራይ ይዤ እንድቀጥል፤ ይህ የሚታለፍ ከሆነም የግንባታ ወጪውን ብር 500,000 እንዲከፍለኝ፤ ይህ በበቂ ምክንያት የሚታለፍ ከሆነና የንግድ ቤቱ አሮጌ በመሆኑ ለመልሶ ማልማት የሚውል ከሆነ ቅድሚያ እንዲሰጠኝ፣ ወጪና ኪሳራን ጨምሮ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ግንቦት 29 ቀን 2010 ዓ.ም ባቀረበው መልስ 1ኛ ተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ጉዳይ ላይ በሰጠው መልስ 2ኛ ተጠሪ በደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤት በንግድ ቤቱ ላይ ካርታ በስሙ ተሰርቶ እንዲሰጠው አመልካች ላይ ክስ መስርቶ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 26087 ክርክር ተደርጎ የንግድ ቤቱ በ2ኛ ተጠሪ ወጪ የተሰራ ቢሆንም ንብረትነቱ የመንግስት ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡ ቤቱን በኪራይ ይዞ እንዲቀጥል የተሰጠ ውሳኔ የለም፡፡ ለቤቱ ግንባታ ያወጣውን ወጪ ስልጣል ላለው አካል አቅርቦ ማስወሰን ይችላል ተብሎ መወሰኑ ክስ የማቅረብ መብቱን ለ1ኛ ተጠሪ ለማስተላለፍ አያስችልም፡፡ ቤቱን የሚያስተዳድረው አመልካች ለ3ኛ ወገን የሚያከራይበት አግባብ በመመሪያ ቁጥር 1/2009 የሚወሰን እንጂ ለማን ያከራይ የሚለው በፍርድ የሚወሰን አይደለም፡፡ ይህም በቅፅ 12 በታተመው በመዝገብ ቁጥር 42150 አስገዳጅ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ የከተማ ይዞታ ለመልሶ ማልማት የሚውልበትን አግባብ የመወሰን ስልጣንም የከተማ አስተዳደሩ ነው፡፡ ይዞታው የራሱ መግቢያ እና መውጫ አለው፡፡ የለውም ቢባል እንኳ በህግ አግባብ መንገድ መጠየቅ ስለሚቻል ክሱ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመቃወሚያው ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ 2ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን የ1ኛ ተጠሪን ክስ በማጠናከር እንደ ክሱ ሊወሰንላቸው ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም በጣልቃ ገብ መልስ ላይ ግራ ቀኝ መልስ እንዲሰጡበት ካደረገ በኋላ መቃወሚያውን በብይን ውድቅ አድርጎ በፍሬ ነገር ላይ የግራ ቀኙን የሰው ምስክር፣ የሰነድ ማስረጃ፤ በደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 105/2009፣ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 26087፣ በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12269 የተሰጠውን ውሳኔ እንዲሁም ከደቡብ ወሎ ዞን ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ የቀረበውን ውጤት አብሮ መርምሯል፡፡ የ1ኛ ተጠሪ ምስክር የሆኑት 2ኛ ተጠሪ የንግድ ቤቱ መግቢያ የቤት ቀጥሩ 196 የሆነው ሳሎን ቤት መሆኑን፤ የመብራት እና የውሃ ቆጣሪው ከቤት ቀጥሩ 196 ጋር የተያያዘ መሆኑን እና የቤት ቁጥሩ 196 የሆነው ቤት የራሱ ሽንት ቤት የሌለው መሆኑን ገልፀው መስክረዋል፡፡ ከደቡብ ወሎ ዞን ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ በቁጥር ታህሳስ 16 ቀን 2011 ዓ.ም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የተላከው ማስረጃ ቤቱ እራሱን ችሎ ለሌላ ለ3ኛ ወገን መተላለፍ የማይችል፣ የራሱ መግቢያ መውጪያ፣ መብራትና ውሃ የሌለውና ከቤት ቁጥር 196 ጋር በጋራ የሚጠቀም፣ በኮንክሪት መወጣጫ የተያያዘ መሆኑ እንዲሁም የግንባታ ወጪው ብር 481,425.49 መሆኑን ገጸው መልስ የሠጡ ስለሆነ በኪራይ ለሌላ 3ኛ ወገን ሊተላለፍ አይችልም፡፡ የንግድ ቤቱን ግንባታ ያከናወነው 2ኛ ተጠሪ መሆኑን ግራ ቀኙ ስላልተካካዱና ግንባታውን ማዘጋጃ ቤቱ እና ቀበሌው ፈቅደውለት ያከናወነ ሲሆን ለ1ኛ ተጠሪ በሽያጭ አስተላልፏል፡፡ በፍ/ሕ/ቁጥር 1161(1) መሰረት ሌላ ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ ንብረቱን በእጁ ያደረገው ሰው በቅን ልቦና እንደገዛ የሚገመት በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ያወጣውን ወጪ ሊቀበሉ የሚገባው 1ኛ ተጠሪ ስለሆኑ 2ኛ ተጠሪ ይከፍሉት በነበረው የቤት ኪራይ ዋጋ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን ይዘው ሊገለገሉ ይገባል፡፡ አመልካች በዚህ የማይስማማ ከሆነ የቤቱ የግንባታ ወጪ ብር 481,425.81 በኪራይ እንዲታሰብ ወይም ይህን ገንዘብ እንዲከፍል እንዲሁም 1ኛ ተጠሪ የሊዝ ወይም የቀድሚያ መግዛት መብት እንዲጠበቅላቸው ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ይግባኙን ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት በመሰረዙ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታውን ቢያቀርብም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348 መሰረት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

አመልካች የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው ይህን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ በደሴ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12269 በነበረው ክርክር በተጠሪዎች መካከል የተደረገው የሽያጭ ውል ከቅን ልቦና ውጪ የተደረገ መሆኑ ተረጋግጦ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ በዚህም ምክንያት በተጠሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት ስለተቋረጠ 2ኛ ተጠሪም ለ1ኛ ተጠሪ የሚያስተላልፈው መብት ስለሌለ 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም፡፡ ክሱም እድሳቱ ከተደረገ ከ15 ዓመት በኋላ የቀረበ ነው በማለት አመልካች ያነሳነው መቃወሚያ መታለፉ ተገቢ አይደለም፡፡ 2ኛ ተጠሪ የቤቱን ግንባታ በ1990 ዓ.ም በማከናወን እንያንዳንዱን አልጋ በቀን ብር 50 ከ18ቱ ክፍሎ በቀን ብር 900 በወር ብር 27,000 በዓመት ብር 324,000

በ15 ዓመት ውስጥ 4.860,000 ገቢ በማግኘት ተካክሷል፡፡ አመልካች መክፈል ካለበትም የግንባታው ወጪ ብር 47,506.81 ብቻ ነው በማለት ተከራክሮ እያለ ቤቱ በታደሰበት ጊዜ በነበረው ዋጋ በገለልተኛ አካል እንዲጣራ ሳይደረግ መወሰኑ፣ አመልካች ለ3ኛ ወገን የሚያስተላልፍበት አግባብም በመመሪያ ቁጥር 1/2009 መሰረት የሚወሰን በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ በኪራይ ይዘው እንዲቀጥሉ እንዲሁም የከተማ ቦታን የማስተዳደር እና የማስተላለፍ ስልጣን የከተማ አስተዳደሩ ሁኖ እያለ 1ኛ ተጠሪ በሊዝ ቅድሚያ የመግዛት መብት ሊከበርላቸው ይገባል መባሉ፤ አከራካሪው የቀበሌ ቤት የራሱ መውጪያ እና መግቢያ ያለው ሲሆን የለውም ቢባል እንኳ በህግ አግባብ መንገድ እንዲከፈትለት መጠየቅ የሚቻል መሆኑን በሚቃን ሁኔታ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚል ነው፡፡

አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የመንግስት መሆኑ ያልተካደ በመሆኑ፤ ያለአመልካች ፍቃድ ተጠሪዎች ይዘው ኪራይ እየከፈሉ እንዲጠቀሙ የተሰጠውን ውሳኔ ከአመልካች የመዋዋል ነፃነት አንፃር ለመመርመር ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪዎች መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ታዟል፡፡

የ1ኛ ተጠሪ ጉዳዩ በክርክር ላይ እያሉ ከዚህ አለም በሞት በመለየታቸው ወራሾቻቸው ሐምሌ 19 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ 2ኛ ተጠሪ ቤቱ ሙሉ በሙሉ በመውደሙ ምክንያት በአመልካች ፍቃድ በ1990 ዓ.ም አከራካሪውን ቤት የሰራ መሆኑ፣ 1ኛ ተጠሪም በ2003 ዓ.ም ይህን ቤት በቅን ልቦና መግዛታቸው፣ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 26087 2ኛ ተጠሪ ከማንም ተከራይ የበለጠ እና ቤቱን የመጠቀም መብት እንዳለው መወሰኑ ተረጋግጧል፡፡ 2ኛ ተጠሪ የኪራይ እና የመጠቀም መብት ያለው፣ ቤቱን በሽያጭ ሲያስተላልፍ የመጠቀም መብቱ ያልተቋረጠ እንዲሁም ከማይንቀሳቀስ ንብረት ጋር የተገናኙ መብቶች በሽያጭ የሚተላለፉ በመሆኑ አመልካች ያልነበረ የኪራይ ውልን ተገዶ እንዲዋዋልና

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የመዋዋል ነጻቱን በመጋፋት የተሰጠ ውሳኔ አስመስሎ ያቀረበው መከራከሪያ ተገቢነት የለውም፡፡ አከራካሪው የንግድ ቤት ከ1ኛ ተጠሪ ህጋዊ ቤት ጋር የተያያዘ፣ ለብቻው መጠቀም የማይቻል፣ በማናቸውም መንገድ ራሱን ችሎ ለ3ኛ ወገን መተላለፍ የማይችል በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ በተከራይነት ይገኘው ካልቀጠልኩ የንብረት መብት፤ የህጋዊ ቤትን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት የሚጎዳ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ የቀዳሚነት የመልሶ ማልማት መብት ተጠብቆ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ በተከራይነት እንድትቀጥል የተሰጠው ውሳኔ በአማራጭ የተሰጠ፣ አመልካች ከፈለገ የግንበታ ወጪውን ብር 481,425.91 በካሳ መልክ እንዲከፍል እና ቦታው በሊዝ ለ3ኛ ወገን የሚተላለፍ ከሆነም ለ1ኛ ተጠሪ እንዲቻቻል የሚል ሁኖ እያለ እንደ ብቸኛ አማራጭ ተደርጎ የቀረበው መከራከሪያ አግባብ አይደለም፡፡ አከራካሪው ቤት የተገነባው የፕላን ፈቃድ ለማግኘት በቀረበው ግምት ልክ ካለመሆኑም በላይ የግምቱ ክፍያ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተሰልቶ ሊከፈል የሚገባው ክርክር ሲደረግ በነበረው የገበያ ዋጋ ብር 481,425.91 መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪም የ1ኛ ተጠሪ ወራሾች የሠጡትን መልስ በማጠናከር መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካች በበኩሉ ጥቅምት 4 ቀን 2014 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሱን ያቀረበ ሲሆን የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ባጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን አመልካች 1ኛ ተጠሪ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም፣ ክሱም በይርጋ ይታገዳል በማለት ያነሳው መቃወሚያ መታለፉ አግባብ ነው? ወይስ አይደለም? መቃወሚያው መታለፉ አግባብ ነው ከተባለ 1ኛ ተጠሪ የንግድ ቤቱን በኪራይ ይዘው እንዲቀጥሉ ወይም የንግድ ቤቱን ግምት ብር 481,425.91 አመልካች እንዲከፍል እና ቤቱ ለልማት የሚፈለግ ከሆነ ቅድሚያ ለ1ኛ ተጠሪ እንዲያመቻች የመወሰኑን አግባብነት በስር ፍ/ቤት ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ ተገቢነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎችጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

በቅድሚያ ምላሽ ማግኘት ያለበት 1ኛ ተጠሪ አመልካች ላይ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት አመልካች ያቀረበው መቃወሚያ በስር ፍ/ቤቶች የመታለፉ አግባብነት ነው፡፡ ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ወይም ሀብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ማንኛውም ሰው ክስ የማቅረብ መብት የሌለው መሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33(2) ላይ ተመላክቷል፡፡ አከራካሪ የሆነውን የንግድ ቤት 2ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በተደረገ የኪራይ ውል ስምምነት የያዘው መሆኑ፤ ይህ የንግድ ቤት በደረሰበት የእሳት አደጋ ምክንያት ሙሉ ለሙሉ በመውደሙ 2ኛ ተጠሪ በራሱ ወጪ ግንባታውን እንዲያካሒድ አመልካች በሰጠው ፍቃድ መነሻነት 2ኛ ተጠሪ በ1990 ዓ.ም 18 ክፍል የመኝታ ክፍል (አልቤርጎ) ያለው ባለ አንድ ፎቅ ሕንጻ ገንብቶ ሲገለገልበት መቆየቱ፤ ከዚህ የንግድ ቤት አጠገብም የቤት ቁጥሩ 196 የሆነ የግል ቤት እንደነበረው፤ ይህን ከአመልካች በኪራይ ይዞ ሲገለግልበት የነበረውን የንግድ ቤት ከአጠገቡ ከሚገኘው የግል ቤቱ ጭምር በ2003 ዓ.ም በ1.8 ሚሊየን ብር ለ1ኛ ተጠሪ በሽያጭ ማስተላለፉ፣ በዚህም መነሻነት 1ኛ ተጠሪ 2ኛ ተጠሪ የንግድ ቤቱን ስመ ሀብት እንዲያዞርላቸው በደሴ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12269 ክስ መስርተው ስመ ሀብቱን እንዲያዞርላቸው ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የፍርድ መቃወሚያ በማቅረቡ በንግድ ቤቱ ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል እንዲፈርስ እና ቤቱም የአመልካች ነው ተብሎ መወሰኑ፤ ይህንንም ተከትሎ 2ኛ ተጠሪ በደሴ ከተማ ነክ ጉዳዮች ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 105/2009 ክስ መስርቶ የንግድ ቤቱን የግንባታ ወጪ ከሶ የመጠየቅ መብቱ ተጠብቆ ውሳኔ የተሰጠ መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

1ኛ ተጠሪ ከስር ጀምሮ የሚከራከሩት የንግድ ቤቱን አጠገቡ ከሚገኘው የ2ኛ ተጠሪ የግል ንብረት ከነበረው ቤት ጋር በቅን ልቦና የገዙት መሆኑን በመግለፅ እንዲሁም በከተማ ነክ ፍርድ ቤቱ በነበረው ክርክር 2ኛ ተጠሪ የግንባታ ወጪውን ከሶ የመጠየቅ መብት ስለተጠበቀለት 2ኛ ተጠሪ በተጠበቀለት መብት በመተካት

ዳኝነት መጠየቅ የሚችሉ መሆኑን በመግለፅ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ አከራካሪውን የንግድ ቤት በ2003 ዓ.ም ከገዙት በኋላ የቤቱ ትክክለኛ ባለቤት አመልካች መሆኑ ተረጋግጦ የንግድ ቤት የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ተወስኗል፡፡ በተጠሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት መነሻም ይህ በ2003 ዓ.ም የተደረገው የሽያጭ ውል በመሆኑ ውሉ እንዲፈርስ ሲወሰን በንግድ ቤቱ ላይ በተጠሪዎች መካከል የነበረው ግንኙነት ተቋርጧል፡፡ ውሉ በመፍረሱም 1ኛ ተጠሪ ከንግድ ቤቱ ጋር በተያያዘ ምንም አይነት መብት የላቸውም፡፡ በከተማ ነክ ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር 2ኛ ተጠሪ የግንባታ ወጪውን በሚመለከት ክስ የማቅረብ መብቱ መጠበቁም የአመልካችን እና የ2ኛ ተጠሪን ግንኙነት የሚወሰን እንጂ የሽያጭ ውሉ ከፈረሰ እና የተጠሪዎች ግንኙነት ከተቋረጠ በኋላ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ እግር በመተካት ክስ ለማቅረብ የሚችሉበትን መብት የሚፈጥርበት አግባብ የለም፡፡ የግንባታ ወጪን በተመለከተ አመልካች ላይ ክስ እንዲያቀርብ መብት የተጠበቀለት 2ኛ ተጠሪ ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪም ይህን መብቱን በፍ/ሕ/ቁጥር 1962 በተደነገገው አግባብ ለ1ኛ ተጠሪ ያደረገው ትክክለኛ የመብት ማስተላለፍ ስለመኖሩ የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡

በፍ/ሕ/ቁጥር 33(2) መሰረት ክስ የማቅረብ መብት እና ጥቅም የሚመነጨው ከውል ወይም ከህግ ወይም ከሁለቱም ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ አላማም በአንድ ጉዳይ የተለያዩ ሰዎች በአንድ ሰው ላይ በተለያየ ጊዜ ወይም በተመሳሳይ ጊዜ ክስ እንዳያቀርቡ በማድረግ ትክክለኛው ባለመብት ብቻ ክስ እንዲመሰርት በማስቻል ባለጉዳዮችንም ሆነ የፍርድ ቤትን ጊዜና ወጪ በመቆጠብ የባለጉዳዮችን እንግልት ማስቀረት እና ክርክሮች ባጠረ ጊዜ እልባት እንዲያገኙ ማስቻል ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ በንግድ ቤቱ ላይ መብት አግኝቼበታለሁ የሚሉበት የሽያጭ ውል እንዲፈርስ ከተደረገ አመልካች የንግድ ቤቱን በተመለከተ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ምንም አይነት መብት የላቸውም ማለት ነው፡፡ የሽያጭ ውሉ እንኳን አልፈረሰም ቢባል ውሉ የተደረገው በተጠሪዎች መካከል በመሆኑ የንግድ ቤቱ ባለቤት በሆነው አመልካች ላይ ውሉ ለ1ኛ ተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት አይሰጣቸውም፡፡ በመሆኑም ከዚህ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች 1ኛ ተጠሪ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት ያነሳውን መቃወሚያ ተቀብለው ክሱን ውድቅ አለማድረጋቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ቀሪዎቹን ነጥቦች መመርመር ሳያስፈልግ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 21528 መጋቢት 27 ቀን 2011 ዓ.ም የሠጠው ውሳኔ፣ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 42361 ግንቦት 16 ቀን 2011 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-91593 ጥር 28 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. 1ኛ ተጠሪ አመልካች ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት እና ጥቅም የላቸውም በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ፡- 204021

ቀን፡-05/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ኮሜርሻል ኖሚኒስ ኃ/የተ/የግል ማሕበር - አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- 1. አቶ ነገራ ለታ
2. አቶ አዱኛ ለገሰ
3. አቶ ጌቱ ሙሉጌታ
4. አቶ ታምሩ ጉታ
5. አቶ ያዴሳ እጅጉ
6. ወ/ሮ አበባ ድሪባ
7. አቶ ዳምጠው ገለጠ
8. አቶ ተፈራ ፈይሳ
9. አቶ ዘነባ ተስፋዬ
10. ወ/ሮ አያንቱ ተስፋዬ
11. አቶ ደበበ ተስፋዬ
12. አቶ መገርሳ ኩሹሌ
13. አቶ አበበ ኢዶ
14. ወ/ሮ ሕይወት መኮንን
15. አቶ አበራ ካባ

የ15ቱ ተጠሪዎች ጠበቃ ገዳ ቡታ- ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ተከሳሽ ሲሆን ተጠሪዎች ከሳሾች ነበሩ፡፡ ተጠሪዎች የካቲት 30 ቀን 2012 ዓ/ም ባቀረቡት የተሻሻለ ክስ ከአመልካች ጋር በጥበቃ ሥራ ውል በኮንትራት ጊዜያዊ ውል

አድርገናል፤ እስከ ነሀሴ 25 ቀን 2013 ዓ/ም ድረስ ውላችን ተራዝሟል። የ15 ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሥራ ቅጥር ውል ጊዜ ሳይጠናቀቅ ከሐምሌ 30 ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ አላግባብ በሕገ-ወጥ መንገድ ከሥራ አሰናበቶናል። ስለሆነም የተለያዩ ክፍያዎች አመልካች ሊከፍለን ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል። አመልካች ያቀረበው መልስ ከተጠሪዎች ጋር ባደረግነው የሥራ ውል ላይ ውሉን ማቋረጥ የፈለገ ወገን የ15 ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ ይፈቅዳል። ከኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ ጋር ሠራተኛ ለማቅረብ የነበረን ውል በመቋረጡ ምክንያት ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር ያላቸው ውል ተቋርጧል። የሥራ ውሉ መቋረጡ ሕጋዊ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የኢሉ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 29252 ጉዳዩን መርምሮ አመልካች የሠው ኃይል አቅራቢ እንጂ ለራሱ ሥራ ተጠሪዎችን የቀጠረ አይደለም። የኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ የሠው ኃይል አቅርቦት ውሉን በ20/11/2011 ዓ/ም በማቋረጡ የአመልካች ሥራም በዚሁ ምክንያት ቆሟል። በመሆኑም በውላቸውና በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሀ) መሠረት የሥራ ውሉ መቋረጡ ስንብቱ ሕጋዊ ነው። ደመወዝ ተከፍሏል፣ የዓመት ዕረፍት ያልተወሰደ ስለመኖሩ አልተረጋገጠም፣ የጡረታ መዋጮ ክፍያ የሥራ ውል ሲቋረጥ በአሠሪው ተመላሽ የሚደረግ ክፍያ አይደለም በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ ወስኗል። ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ያቀረቡትን ይግባኝ በመቀበል አከራክሮ ለኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ የአገልግሎት አቅርቦት ዋጋ እና ሁኔታዎችን ለማደስና ለማመቻቸት ካልተስማማችሁ የሰው ኃይል አቅርቦት ውሉ ከ01/12/2011 ዓ/ም ጀምሮ የሚቋረጥ ስለመሆኑ ማስጠንቀቂያ በ20/11/2011 ዓ/ም የጻፈው አመልካች ነው። ባንኩም በሠጠው ምላሽ ያቀረባችሁትን የሥራ ማቋረጥ ውሳኔ እንቀበላለን ብሏል። ይሕም አመልካች በራሱ ተነሳሽነት ያደረገው መሆኑን ያሳያል። በተጨማሪም አመልካች ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ የጻፈው ለባንኩ ከመጻፉ በፊት በ12/11/2011 ዓ/ም ነው። የ15 ቀን ማስጠንቀቂያ ሰጥቻለሁ ያለውም ከአሠሪና ሠራተኛ ሕጉ ውጭ ነው። ሥራውን የሚያስቆም አስገዳጅ ሁኔታ ከመፈጠሩ በፊት ሁኔታዎች አመቻችቶ የሥራ ውላቸው ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት ማቋረጡ የሥራ ውሉን እና የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሀ) መሠረት ያላደረገ ስለሆነ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት የሥራ ስንብት ክፍያ፣ ካሣ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ የሁለት ወር ደመወዝ፣ ክፍያ ለዘገየበት ቅጣት ለእያንዳንዳቸው ብር 24,149.00 አመልካች ከወጭና ኪሣራ ጋር እንዲከፍል ወስኗል። የዓመት ዕረፍትና የጡረታ መዋጮ ክፍያ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሏል። የክልሉ ሰበር ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ሠርዟል።

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ተጠሪዎች የተቀጠሩበት ባንክ ከአመልካች ጋር ያለውን የአንድ ዓመት ውል አቋርጦ ከሌላ ኤጀንሲ ጋር ውል በመፈጸሙ ምክንያት በውላችን አግባብ የ15 ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት ውሉን ማቋረጣችን ተገቢ ነው። ከባንኩ ጋር የገባነው ውል ተጠናቋል። ተጠሪዎች ከሌላ ኤጀንሲ ጋር በባንኩ ሥራቸውን ቀጥለዋል። በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 28(3)(ሀ) መሠረት የሥራ ውል ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ያለ በመሆኑ የሥራ ስንብቱ ሕጋዊ ነው። የሥራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ነው ተብሎ መወሰኑ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሕግን የተከተለ አይደለም የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ የኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ ውሉን ማቋረጡን ከማሳወቁ እና ግራቀኙ ካደረጉት ውል አንጻር ሕገ-ወጥ ስንብት ነው መባሉ ሕጋዊነቱን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ያዘዘ ሲሆን ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ከባንኩ ጋር ያለውን ውል ለማቋረጥ ማስጠንቀቂያ በመጀመሪያ የጻፈው አመልካች ነው፡፡ ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ የሠጠው ባንኩ ደብዳቤ ከመጻፉ በፊት ነው፡፡ የሥራ ውላችን ተቋርጦ ለችግር ተጋልጠን ከብዙ ወራት በኋላ በሌላ ኤጀንሲ የተቀጠርነው፤ በሥርም የቀረበ ክርክር አይደለም፡፡ ውሳኔው ሊጸና ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕግ አግባብ ስለመሆን አለመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለውን ሕግና በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች አንጻር መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪዎች የካቲት 30 ቀን 2012 ዓ/ም ባቀረቡት የተሻሻለ ክስ በሕገ-ወጥ መንገድ አመልካች ከሥራ አሰናብቶናል በማለት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን አመልካች በበኩሉ የሥራ ውላቸው የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ግራቀኙ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሠረት በማድረግ የተከራከሩ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶችም አዋጅ ቁጥር 1156/2011ን ለጉዳዩ ተፈጻሚ አድርገዋል፡፡ ተጠሪዎች ከሥራ የተሰናበቱት የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 በሥራ ላይ ባለበት ጊዜ ሀምሌ 30 ቀን 2011 ዓ/ም ነው፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 190(5) ላይ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ያለው ሲሆን በዳኝነት አካል ላይ በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት ጊዜ በነበረው ሕግ መሠረት ፍጻሜ እንደሚያገኙ አስቀምጧል፡፡ በመርሕ ደረጃ መሠረታዊ ሕግ ተፈጻሚ መሆን ያለበት በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ በተከሰቱ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ ክሱ የቀረበው አዋጅ ቁጥር 1156/2011 በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ በ2012 ዓ/ም ቢሆንም ለተጠሪዎች የሥራ ውል መቋረጥ ምክንያት የሆነው ድርጊት የተከሰተው አዋጅ ቁጥር 377/1996 በሥራ ላይ ባለበት ጊዜ ስለሆነ የተግባሩ ሕጋዊነትም መመርመር ያለበት ይሕንኑ ሕግ መሠረት በማድረግ ሊሆን ይገባል፡፡ ስለሆነም የሥራ ውል መቋረጥ ተግባር ሕጋዊ መሆን አለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የሥራ ውል የሚቋረጠው አንደኛው በሕግ ወይም በሥምምነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተዋዋይ ወገኖች አነሳሽነት ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 24 በሕግ መሠረት ውል የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች ተዘርዝረዋል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 25 ደግሞ በሥምምነት ውል ስለሚቋረጥበት ሁኔታ ይገልጻል፡፡ በአሠሪው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበት ሁኔታ በአዋጁ ከአንቀጽ 26-30 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 31 እና 32 ደግሞ በሠራተኛው አነሳሽነት የሥራ ውል የሚቋረጥበትን ሁኔታ ደንግጓል፡፡ የአዋጁ ድንጋጌ አንቀጽ 31 በአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ለአሠሪው በመስጠት ሠራተኛው ውሉን ማቋረጥ እንደሚችል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሚገልጽ ነው፡፡ ሌላው በሠራተኛው አነሳሽነት የሚፈጸም የሥራ ውል ማቋረጥ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 32(1)(ሀ እስከ ሐ) የተመለከተ ሲሆን በሕጉ የተዘረዘሩት ምክንያቶች አሠሪው የሠራተኛውን ሠብዓዊ ክብርና ሞራል መንካቱ፣ በወንጀል የሚያስቀጣ ተግባር በሠራተኛው ላይ መፈጸም፣ ለሠራተኛው ደኅንነት ወይም ጤንነት አደጋ ሊያደርስ የሚችል ምክንያት እያለ አሠሪው ተገቢውን እርምጃ ካልወሰደ ወይም ሌላ አሠሪው ለሠራተኛው መፈጸም ያለበትን ግዴታ በመደጋገም ካልፈጸመ ሠራተኛው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉን ማቋረጥ የሚችልበትን ሁኔታ አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ማዕቀፎች ውጭ አሠሪው ሠራተኛን ከሥራ ሲያሰናብት ሕገ-ወጥ የሥራ ስንብት ይሆናል፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ አሠሪው በፈለገ ጊዜ የሠራተኛን የሥራ ውል ማቋረጥ እንዳይችልና የሠራተኛው የሥራ ዋስትና መረጋገጥን ዓላማ ያደረገ ሲሆን በሌላ በኩል የኢንዱስትሪው ምርትና ምርታማነት ለመጨመርና አሰሪው ላይ ያልተገባ ጫና እንዳይፈጠርበት ሁለቱን ተወዳዳሪ ጥቅሞች/ፍላጎቶች የማስታረቅ ግብ ይዟል፡፡ አመልካች በቅጥር ውሉ ላይ የሥራ ውሉን ማቋረጥ የፈለገ ወገን የ15 ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ እንደሚችል ስለተመለከተ በዚህ መሠረት የሥራ ውሉ መቋረጡ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አሠሪ በሥራ ውል ወይም ደንብ ወይም በሕብረት ሥምምነት መሠረት በሕጉ ከተመለከተው ያነሰ መብት ሊዋዋል የማይችል መሆኑ እና ቢዋዋልም ሕጋዊ ውጤት የሌለው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 4(5) እና 133(1) ላይ ተመልክቷል፡፡ በሕጉ ሥራው ሳያልቅ ለአሠሪው የ15 ቀን ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሠራተኛውን የሥራ ውል እንዲያቋርጥ መብት አልሠጠውም፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የአመልካች ክርክር ሕጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ሥራዎችን ከሦስተኛው ወገን በውል እየወሰደ የሚሰራ አሠሪ መሆኑን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪዎችም የተቀጠሩት የኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ የጥበቃ ሥራን ለሦስተኛ ወገን (outsource) በማድረጉና ሥራውን አመልካች በውል ለመሥራት በመውሰድ ተጠሪዎችን በመቅጠሩ ነው፡፡ ሥራውን ለአመልካች የሠጠው ባንክም ውሉን ከሀምሌ 20 ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ ያቋረጠ ስለመሆኑ አመልካች ያቀረበውን ክርክር ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተመለከተው ወረዳ ፍርድ ቤት ተቀብሎታል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ ለኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ የአገልግሎት አቅርቦት ዋጋ እና ሁኔታዎችን ለማደስና ለማመቻቸት ካልተስማማችሁ የሰው ኃይል አቅርቦት ውሉ ከ01/12/2011 ዓ/ም ጀምሮ የሚቋረጥ ስለመሆኑ ማስጠንቀቂያ በ20/11/2011 ዓ/ም የጻፈው አመልካች ስለመሆኑ፣ ባንኩም በሠጠው ምላሽ ያቀረባችሁትን የሥራ ማቋረጥ ውሳኔ እንቀበላለን ማለቱ፣ አመልካች ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ የጻፈው ለባንኩ ከመጻፉ በፊት በ12/11/2011 ዓ/ም መሆኑ ሲታይ ሥራውን የሚያስቀም አስገዳጅ ሁኔታ ከመፈጠሩ በፊት ሁኔታዎች አመቻችቶ የሥራ ውላቸው ጊዜው ከመጠናቀቁ በፊት አመልካች ማቋረጡን በፍሬ ነገር ደረጃ አረጋግጧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ማስረጃን የመመዘን እና ፍሬ ነገርን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለው በመሆኑ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ

ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን ያልተሰጠው በመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተደረሰበትን ድምዳሜ ተቀብለነዋል፡፡

ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አመልካች በራሱ አነሳሽነት የውሉ ሁኔታ እንዲለወጥ በማድረግ የሥራ ውሉን ማቋረጡ ተገቢ ነው በሏል፡፡ አመልካች እንደ ድርጅት የንግድ ሥራውን በምን አግባብ መምራት እንዳለበት የመወሰን ሥልጣን እና ነጻነት ሊኖረው ይገባል፡፡ አመልካች ከኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ ጋር የገባው ውል ባይጠናቀቅ እንኳን የንግድ ሁኔታ ለውጦች ካሉ እና ለአሠሪውም ሕልውና ችግር ውስጥ የሚከት ጉዳይ ከተፈጠረ የውሉ ሁኔታ እንደሊወጥ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩ የሦስተኛ ወገን ጥቅም ያለበት ማለትም የሠራተኞች የሥራ ዋስትና ጋርም የተያያዘ በመሆኑ አሠሪው ሲወሰን ይሕንንም የውሳኔ ሂደቱ ላይ ማስገባት አለበት፡፡ ፍርድ ቤት የንግድ ሁኔታዎችን መዝኖ ለመወሰን ሥልጣን እና ሙያው ባይኖረውም አመልካች ለሠራተኞች ውል መቋረጥ ምክንያት የሆነ ከኦሮሚያ ሕብረት ሥራ ባንክ ጋር የገባውን ውል ሁኔታዎች እንዲለወጡ የጠየቀበት አመላካች ምክንያቶችን አቅርቦ ሊከራከር ይገባል፡፡ አመልካች የውል ሁኔታዎች ለመለወጥ ማሳያ ምክንያቶችን ባላሳየበት ሁኔታ ለተጠሪዎች የሥራ ወል መቋረጥ የሆነው ምክንያት በራሱ አነሳሽነት መውሰዱና ውሉን ማቋረጡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 28(2)(ሀ) የተመለከተውን ለውል መቋረጥ የሚያስከትል ሁኔታ መከሰት የሚለውን የሚያሟላ ባለመሆኑ የሥራ ሥንብቱ ሕገ-ወጥ ነው፡፡ ተጠሪዎች በሚሰሩበት ባንክ በሌላ ኤጀንሲ ሥራ ቀጥለዋል የሚለው የአመልካች ክርክር በሥር ያልቀረበና አዲስ ክርክር በመሆኑ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329(1) መሠረት ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ተጠሪዎች ሥራ ማግኘትና መቀጠል የአመልካችን የሥንብት እርምጃ ሕጋዊ አያደርገውም፡፡ በአጠቃላይ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የክልሉ ሰበር ችሎት የተጠሪዎች የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው በማለት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው የሠጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 335812 የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ/ም እና የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 54351 የካቲት 12 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሄ/መ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

??/? /??? 203890
?? 27/3/2014 ?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - አቶ ደመላሽ ሙልጌታ

የቀረበ

ተጠሪ - የአራዳ ክ/ከተማ አስተዳደር ገንዘብ ቁጠባ ጽ/ቤት የህብረት ሥራ ማህበር

ነ/ፈ - ሀብታሙ ውበቱ -ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች መጋቢት 3 ቀን 2013 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 254081 ታህሳስ 20 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 176095 ታህሳስ 22 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤት ብር 59,879 እንድከፍል ሲወስን የግራ ቀኙን የሰው ምስክር ሳያዳምጥ ሳይጣራና ትክክለኛ የኦዲት ሪፖርት ሳይቀርብ የተሰጠብኝ ውሳኔ በመሆኑ፣ ለጉዳዩ መነሻ በሆኑት ቼኮች ሁላችንም ፈርመንበት እያለ ይህም የሶስታችን ፊርማ ለመሆኑ በፎረንሲክ ተረጋግጦ እያለ የጋራ ተጠቂዎች መሆን ሲገባ አመልካች ብቻ ኃላፊ ነው ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ተከሳሾች 1. የአሁን አመልካች 2. አቶ ፍቃዱ በቀለ 3. ወ/ሮ ዘነበች ለማ ከመጋቢት 2003 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 2008 ዓ/ም ድረስ የከሳሽ ማህበር ሂሳብ ሹም፣ ሊቀመንበር እና ገንዘብ ያዥ ሆነው ሲሰሩ 1ኛ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ሂሳብ ሹም ሆኖ ሲሰራ በእጁ በስራ ምክንያት የገባውን የማህበሩን ቼክ ከፊት ለፊቱ ቁጥር በመጨመር በማበላለጥ ብር 29,499 በህገ ወጥ መንገድ የወሰደ በመሆኑ፣ ተከሳሾች የማህበሩ አመራር እና ቼክ ላይ ፈራሚ በመሆናቸው በእጃቸው የሚገኘውን ቼክ እና የወጪ ደረሰኝ በመጠቀም የማህበሩ አባል ላልሆነ ሰው ለአቶ ሙላቱ ደፋር ብር 10,199 እንዲከፈል ያደረጉ በመሆኑ እንዲሁም በተለያዩ ቼኮች በ1ኛ ተከሳሽ ስም ብር 54,380.80 በአጠቃላይ ብር 83,879,80 ለግል ጥቅሙ ያዋለ በመሆኑ ከወለድ ጋር ይክፈሉኝ ሲል ጠይቋል፡፡ ተከሳሾችም 1ኛ ተከሳሽ በሰጠው መልስ 2ኛ ተከሳሽ የማህበሩ ሊቀመንበር የሆነው በ10/12/2004 ዓም ጽፎ በሰጠኝ ክሊራንስ ከሳሽ ከእዳ ነጻ መሆኔን አረጋግጦ አሰናብቶኛል፡፡ በመሆኑም ያጎደልኩት ገንዘብ ሳይኖር ከ6 ዓመት በኋላ ያለምንም ኦዲት ሪፖርት ሊከሰኝ አይገባም፡፡ በተጠቀሱት ቼኮች ብቻ፣ ቼክ የገንዘብ እንቅስቃሴን የሚያሳይ ሆኖ እያለ ካለ ኦዲት ሪፖርት ልከሰስ አይገባም፡፡ ካሁን በፊት በወንጀልም ተከስቼ በነጻ የተሰናበትኩ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ ብሏል፡፡ የ2ኛ እና የ3ኛ ተከሳሾች ደግሞ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር ሆነን ባገለገልንበት ጊዜያት 1ኛ ተከሳሽ ያለውን እውቀት በመጠቀም በተለያየ ቀን በተዘጋጀ ቼክ ለአባላቱ የአጭር ጊዜ ብድር ተብሎ በእያንዳንዱ ቼክ 800 ብር ተዘጋጅቶ ለ1ኛ ተከሳሽ ሲሰጠው ከ2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች እውቅና ውጪ ከፊት ለፊቱ ቁጥር 9 በመጨመር በድምሩ ብረ 29,499 ለግል ጥቅሙ አውሏል፡፡ የማህበር አባል ላልሆነ ሰውም የ10,199 ብር ቼክ አዘጋጅቶ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሽን አስፈርሞ በቼኩ ጀርባ ላይ በራሱ ስም በመፈረም ለግል ጥቅም አውሎታል፡፡ በሌሎች ቼኮችም በተመሳሳይ መልኩ በአጠቃላይ ብር 82,100 ለግል ጥቅሙ አውሏል፡፡ በዚሁ መሰረት ይህን ደርሰንበት ለፖሊስ አሳውቀን በስሙ መውሰዱ ስለተረጋገጠ ቅድሚያ 15,000 ብር ከፍሎ በየወሩ 1,000 ብር እየከፈለ ለመጨረስ ተስማምቶ በ9 ወር 9,000 ብር ከፍሏል፡፡ እስከ 2007 ዓ/ም ኦዲት ተደርጎ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ ብር 82,180 ተገኝቶበታል፡፡ በመሆኑም 1ኛ ተከሳሽ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በነጻ እንሰናበት ብለዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 176095 ታህሳስ 22 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የከሳሽ ማህበር ብር 83,879 ስለመጉደሉ በኦዲት የተረጋገጠ ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ እኔ በሌለሁበት የተደረገ የኦዲት ሪፖርት ነው ቢልም ሌላ ኦዲት ለማዘዝ በቂ ምክንያት የሚሆን ያቀረበው ምክንያትና ማስረጃ የለም፡፡ ለአቶ ሙላቱ ደፋር ለወጣው ገንዘብ 1ኛ ተከሳሽ በራሱ ስም የተጻፈ ቼክ በመሆኑ እንዲሁም በቼኮቹ ላይ ቁጥር ስለመጨመሩ በኦዲት የተረጋገጠ ሲሆን ስላለመጨመሩ ያላስረዳ በመሆኑ በኦዲት ሪፖርቱ መሰረት ብር 83,879 ሊሰበሰብ የሚገባው ከ1ኛ ተከሳሽ እንደሆነ ስለሚያስረዳ እንዲሁም 1ኛ ተከሳሽ የደረሰውን ጉድለት ተቀብሎ ለመክፈል ተስማምቶ መክፈል የጀመረ በመሆኑ 1ኛ ተከሳሽ ኃላፊነት አለበት፡፡ ከብር 83,879.80 ውስጥ ብር 81,000 1ኛ ተከሳሽ ለመክፈል ስለተስማማ እና ከዚህ ውስጥ 24,000 ብር በመክፈሉ ቀሪውን ብር 59,879 ለከሳሽ ሊከፍል ይገባል፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ብር 10,199 ላይ የፈረሙ ቢሆንም 1ኛ ተከሳሽ የማህበር አባል ላልሆነ ሰው እንዲከፈል ቼክ ላይ የፈረሙት ለፊርማ ሊቀርብላቸው የማይገባውን አቅርቦላቸው ያስፈረማቸው እና ለራሱ ጥቅም ያዋለ መሆኑ በኦዲት በመረጋገጡ 2ኛ እኛ 3ኛ ተከሳሾች ሊጠየቁ አይገባም፡፡ ክሱም 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጥፋታቸው ምን እንደሆነ በማስረጃ ተደግፎ ስላልቀረበና ያደረሱት ጉዳት ስላልተረጋገጠ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር ሊጠየቁ አይገባም፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ብር 59,879 ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ እስኪ ጠናቀቅ ድርስ ከ9% ወለድ ጋር ለከሳሽ ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 254081 ታህሳስ 20 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቼክ የሰር ከ1-3 ያሉት ተከሳሾች መፈረማቸው ባልተካደበት ሁኔታ 1ኛ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ብቻ ክፈል የተባለበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ሐምሌ 16 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ሐምሌ 27 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በነበረው ክርክር የአሁን አመልካች የአሁን ተጠሪ ማህበር ሂሳብ ሹም ሆኖ ሲያገለግል በስራ አጋጣሚ በእጁ የገባውን የማህበሩን ቼክ አብረው የተከሰሱትን 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች አሁን በክርክሩ ውስጥ የሌሉትን ካስፈረመ በኋላ በቼኩ ላይ ከተሞላው ገንዘብ መጠን ኋላ ቁጥር በመጨመር ከባንክ ወጪ በማድረግ ለግል ጥቅሙ አውሏል በሚልና ገንዘብ ሊከፈለው ለማይገባ ሰው ቼክ እንዲታዘዝ ካደረገ በኋላ በቼኩ ጀርባ ለራሱ እንዲከፈል በማድረግ ለግል ጥቅሙ አውሏል ተብሎ ክስ የቀረበበት ሲሆን የአሁን አመልካች በቼኩ ላይ የፈረምነው ሶስት ሆነን እያለ እኔ ብቻ ኃላፊ ልሆን አይገባም የሚልና በማስረጃነት የቀረበው የኦዲት ሪፖርት እኔ በሌለሁበት የተሰራ ኦዲት በመሆኑ በማስረጃነት ሊቀርብብኝ አይገባም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም አከራክሮ ግራ ቀኙን ያከራከረው የማህበር ገንዘብ የመጉደል ጉዳይ በሰነድ ማስረጃ የሚጣራ ሆኖ በማስረጃነት የቀረበውን የኦዲት ሪፖርት የአሁን አመልካች የቀረበበትን ክስ የፈጸመ ስለመሆኑ ያረጋገጠበት በመሆኑ ለጎደለው ገንዘብ ኃላፊ መሆኑን ወስኖ የአሁን አመልካች ቀደም ሲል የማህበሩን ገንዘብ ያጎደለ መሆኑን አምኖ ክፍያ የፈጸመው ተቀንሶለት እንዲከፍል ተወስኖበታል፡፡ የአሁን አመልካች ቅሬታ ሶስት ሆነን በቼኩ ላይ ፈርመን እያለ እኔ ብቻ ኋላፊ ሊሆን አይገባም የሚል ሲሆን ገንዘቡ የጎደለበት ሁኔታ በቼኩ ላይ ሶስቱም ከፈረሙበት በኋላ ሌሎቹ ሁለቱ ሳያውቁ የአሁን አመልካች በቼኩ ላይ ከተጻፈው ቁጥር ከኋላ በመጨመርና ከቼኩ ጀርባ ለራሱ እንዲከፈል በመፈረም ለግል ጥቅሙ ያዋለው ስለመሆኑ በቀረበው የሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠበት በመሆኑ ድርጊቱን የግሉ የሚያደረገው ነው፡፡ ሌላው የኦዲት ሪፖርት እንከን ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ የቀረበ እንደሆነ በድጋሚ ኦዲት እንዲደረግ ሊታዘዝ የሚችል ወይም የኦዲት ሪፖርቱ ውድቅ ሊደረግ የሚችል ሲሆን የኦዲት ሪፖርቱ ማስረጃ አይሆንብም የሚል ቅሬታ ስለቀረበበት ብቻ ውድቅ የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም ማስረጃ የመስማትና የመመዘን ሥልጣን የተሰጣቸው የስር ፍ/ቤቶች ግራ ቀኙን አከራክረው በቀረቡው ማስራጀ አጣርተው የሰጡት ውሳኔ ጉድለት የተፈተመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 41526 ላይ በሰጠው ውሳኔ አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ ከማስረጃ ምዘና ጋር የተያያዘና የፍሬ ነገር ክርክር ላይ ያተኮረ እንደሆነ በሰበር ችሎት ሊስተናገድ የማይቸል ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት ይገኛል፡፡ የአሁን አመልካች የቀረበብኝ ክስ በማስረጃ አልተረጋገጠብኝም የሚል የማስረጃ ምዘናን ጉዳይ ያቀረበው ቅሬታ ለሰበር ሰሚው ችሎት ሊቀርብ የሚችል ቅሬታ ባለመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ውሳኔ</u>

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 254081 ታህሳስ 20 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 176095 ታህሳስ 22 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡

2. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

3. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

ማ/አ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 203886

ቀን ፡- ሕዳር 27 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- 1. ሀብታም ንጉሴ
2. ዳንኤል ተሾመ
3. አበበች ነገደ
4. ወይንሸት ፍሬው
5. ሮቤል ገመቹ
6. ጣሂር አማን
7. ትዕግስት ገ/ክርስቶስ
8. ሕይወት ገዛኸኝ
9. ፍቅሩ ቢረጋ
10. ዓለምፀሐይ ከተማ
11. ሽብር ደምሴ
12. ሐይማኖት አጌና
13. ሐያት አብዱ
14. አልያስ ትኩዬ
15. ኤልያስ ለሪሶ
16. እየሩስ ስብሀት
17. ደጀኔ ገመቹ
18. ወንድምአገኘሁ አስፋው
19. ታረቀኝ አማኑ
20. ብርሃኑ ኃይሉ
21. ቤተልሔም ፀጋዬ
22. ሚኪያስ ሙሉዓለም
23. ፋኖስ ጨንገሬ
24. ሐዊ ወሀበይ - የአመልካቾች ጠበቃ አንድነት በየነ -ቀረቡ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪ ፡- አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ መረጃና ምዝገባ ኤጀንሲ ዐ/ህግ ሰለሞን ብርሃኑ - ቀረቡ

ይሕ መዝገብ ከሰበር መዝገብ ቁጥር 203885 ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

<u>ፍርድ</u>

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካቾች የስር ከሳሾች ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበር፡፡ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ከተጠሪ መሥሪያ ቤት ጋር በተለያዩ የሥራ መደቦችና ኃላፊነቶች ላይ ስንሰራ ቆይተናል፡፡ የሥራ ቅጥር ውላችንን ከሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ የሚቋረጥ መሆኑን ስላሳወቀን ቋሚ ሠራተኞች መሆናችን እንዲታወቅና ቅጥሩ እንዲቋረጥ የሠጠው ትዕዛዝ እንዲሰረዝ ሆኖ ወደሥራችን እንድንመለስ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ያቀረበው መልስ አመልካቾች በጊዜያዊነት የተቀጠሩት ለመሬት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሥራ ነው፡፡ በጊዜያዊ ቅጥር ውሉ መሠረት ሥራው ሲቀነስ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሥራ ውሉን ማቋረጥ ይቻላል፡፡ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለተጠሪ መሥሪያ ቤት ሆኖ በመደራጀቱ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በመታጠፉ ምክንያት እንዲሰናበቱ መደረጉ በሕግ አግባብ የተከናወነ ነው ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሠው ሀብት ልማት ቢሮ አስተዳደር ፍርድ ቤት ባደረገው የቃል ክርክር አመልካቾች የሚከራከሩት የተቀጠርነው በጊዜያዊነት ቢሆንም እየሰራንበት ያለው የሥራ መደብ ቀጣይነት ያለው፣ ሥራውን ለመስራት በማሰብ ይዞታ ማረጋገጥ ዳይሬክቶሬት በማቋቋም ሠራተኞችን እየቀጠረ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ከ2006 - 2009 ዓ/ም ብቻ ሕልውና የነበረው ሲሆን ፕሮጀክቱ ካለቀም በኋላ የሥራ መደቡን ይዘን ቆይተናል፤ ይሕም ግንኙነታችን ቀጣይነት ያለው መሆኑን ያሳያል ያሉ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የተቀጠሩበት ፕሮጀክት ታጥፏል፡፡ ፕሮጀክቱ ሲታጠፍ መረጃ የመሰብሰብ ሥራው በተጠሪ መሥሪያ ቤት ተካቶ ሥራው እየተሰራ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ያለቀው በ2011 ዓ/ም እንጂ በ2009 ዓ/ም አይደለም ብሏል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች የተቀጠሩት ለፕሮጀክት ጽ/ቤት ስለመሆኑ የተካካዱበት ነጥብ አይደለም፡፡ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ከፈረሰ በኋላም ሥራችን ቀጥለናል በማለት አመልካቾች የተከራከሩ ቢሆንም አዲስ የፈጸሙት ውል ሆነ የነበራቸው ያደሱበት አግባብ በሌለበት ሁኔታ ቋሚ ሠራተኞች መሆናችን ተረጋግጦ ወደሥራ ተመልሰን ያልተከፈለን ደመወዝ እንዲከፈለን በማለት ያቀረቡት ዳኝነት ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ግራቀችን አከራክሮ ውሳኔውን አጽንቷል፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የአመልካቾችን የሠበር አቤቱታ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ከነሀሴ ወር 2006 ዓ/ም ጀምሮ ዘላቂነት ባላቸው የሥራ መደቦች ላይ ተቀጥረን ስንሰራ ቆይተናል፡፡ ስንሰራቸው የነበሩ ሥራዎች አሁንም በተጠሪ መሥሪያ ቤት ሥር የመሬት ይዞታ ማረጋገጥ ዳይሬክቶሬት በማቋቋም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እየሰራበት ይገኛል። ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከ2009 ዓ/ም በኋላ ሕልውና አልነበረውም፤ ከ2009 ዓ/ም በኋላ የሥራ ቅጥር ውሉን ውጤቶች ስንፈጽም የነበረው በቀጥታ ከተጠሪ ጋር ነው። በቋሚነት ስንሰራ ስለነበር ወደሥራችን ልንመለስ ይገባል የሚል ነው። የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ውሉ መታደስ የነበረበት በ2009 ዓ/ም ሆኖ እያለ አመልካቾች እስከ 2011 ዓ/ም መስራታቸው ባልተካደበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤት የታደሰ ውል አላቀረባችሁም በማለት የወሰነበት አግባብነትን ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ያዘዘ ሲሆን ተጠሪ ያቀረበው መልስ አመልካች ለፕሮጀክት ሥራ በጊዜያዊ ቅጥር ውል የተቀጠሩ ናቸው። በጊዜያዊ ቅጥር ውሉ ሆነ በአዋጅ ቁጥር 56/2010 መሠረት የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት የተቋረጠ ስለሆነ ስንብቱ ሕጋዊ ነው። ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሕልውናውን ያጣው በ2011 ዓ/ም ነው። ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለተጠሪ መሥሪያ ቤት ሆኖ ቆየ እንጂ አመልካቾች ቀጥታ ከተጠሪ ጋር የሥራ ግንኙነት አልነበራቸውም። ውሳኔው ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል ብሏል። አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ የሠበር አጣሪ ችሎት የያዘውን ጭብጥ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል።

እንደመረመርነው አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ከተጠሪ መሥሪያ ቤት ጋር በተለያዩ የሥራ መደቦችና ኃላፊነቶች ላይ ስንሰራ ቆይተናል። የሥራ ቅጥር ውላችንን ከሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ የሚቋረጥ መሆኑን ስላሳወቀን ቋሚ ሠራተኞች መሆናችን እንዲታወቅና ቅጥሩ እንዲቋረጥ የሠጠው ትዕዛዝ እንዲሰረዝ ሆኖ ወደሥራችን እንድንመለስ ይወሰንልን በማለት ላቀረቡት ዳኝነት ተጠሪ የሚከራከረው አመልካቾች በጊዜያዊነት የተቀጠሩት ለመሬት ፕሮጀክት ጽ/ቤት ሥራ ነው። ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለተጠሪ መሥሪያ ቤት ሆኖ በመደራጀቱ ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ በ2011 ዓ/ም በመታጠፉ ምክንያት እንዲሰናበቱ መደረጉ በሕግ አግባብ የተከናወነ ነው ብለዋል።

ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል። ክርክር የሚወሰነው በተጠየቀው ዳኝነት አግባብ እንደሆነ የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182(2) ላይ ተመልክቷል። ፍርድ ቤቱም ከቀረበው ዳኝነት አኳያ ከግራቀኙ ክርክር በመነሳት በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 246 እና ተከታዮቹ መሠረት በተነሱት ጉዳዮች ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለበት። አመልካቾች የሚከራከሩት የተቀጠርነው በጊዜያዊነት ቢሆንም እየሰራንበት ያለው የሥራ መደብ ቀጣይነት ያለው፣ ሥራውን ለመስራት በማሰብ ይዞታ ማረጋገጥ ዳይሬክቶሬት በማቋቋም ሠራተኞችን እየቀጠረ ነው። ፕሮጀክቱ ከ2006 - 2009 ዓ/ም ብቻ ሕልውና የነበረው ሲሆን ፕሮጀክቱ ካለቀም በኋላ የሥራ መደቡን ይዘን ቆይተናል፤ ይሕም ግንኙነታችን ቀጣይነት ያለው መሆኑን ያሳያል በሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የተቀጠሩበት ፕሮጀክት ታጥፏል። ፕሮጀክቱ ሲታጠፍ መረጃ

የመሰብሰብ ሥራው በተጠሪ መሥሪያ ቤት ተካቶ ሥራው እየተሰራ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ያለቀው በ2011 ዓ/ም እንጂ በ2009 ዓ/ም አይደለም ብሏል፡፡ ስለሆነም ክርክራቸውን ለመወሰን ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ መቼ ነው ሕልውናውን ያጣውና የተቋረጠው፡- በ2009 ዓ/ም ወይስ በ2011 ዓ/ም? አመልካቾች በቋሚነት የሥራ መደብ ላይ ሲሰሩ ነበር ወይስ አልነበረም? የሚለው በጭብጥነት በመያዝ ግራቀኙ ባቀረቡት ሆነ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ባለው ሌሎች ማስረጃዎች በማጣራት ፍሬ ነገሩን ካረጋገጠ በኋላ ሕጋዊ ውጤቱስ ምንድን ነው የሚለውን መወሰን ሲገባ ተገቢውን ጭብጥ ሳይያዝ የአመልካቾች ውል አልታደሰም በማለት ክሱ ውደቅ መደረጉ መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ግድፈት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ውሳኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥሮች 32586 እና 32587 ሕዳር 25 ቀን 2013 ዓ/ም፣ የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥሮች 31640 እና 31639 ሚያዚያ 05 ቀን 2012 ዓ/ም እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሠው ሀብት ልማት ቢሮ አስተዳደር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥሮች 1282/2011 እና 1314/2011 ሕዳር 04 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሠው ሀብት ልማት ቢሮ አስተዳደር ፍርድ ቤት ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ መቼ ነው ሕልውናውን ያጣውና የተቋረጠው፡- በ2009 ዓ/ም ወይስ በ2011 ዓ/ም? አመልካቾች በቋሚነት የሥራ መደብ ላይ ሲሰሩ ነበር ወይስ አልነበረም? ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ፈርሶ አመልካቾች ሥራቸውን ከቀጠሉ ሕጋዊ ውጤቱ ምንድን ነው? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ እና ፍሬ ነገሮችን በማስረጃ በማጣራት የመሠለውን እንዲወስን በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343(1) መሠረት ጉዳዩን መልሠናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሠው ሀብት ልማት ቢሮ አስተዳደር ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ የማይነበብ የአምሰት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 203882
መስከረም 28 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. አቶ ብርሃኑ ሺይ
2. ወ/ሮ ምህረት ሺይ
3. ሲ/ር እየሩሳሌም ሺይ
4. ወ/ት አለምጸሐይ ሺይ
} አልቀረቡም ከተባለ በኋላ ጠበቃ ነብያት ግርማ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1. የአዲስ ከተማ ክፍለከተማ የይዞታ አስተዳደር የሽግግር ጊዜ አገልግሎት ፕሮጀክት ጽ/ቤት
2. የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ቤቶች አስተዳደር - ዐ/ህግ ለታ ባይሳ ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 03 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 276300 መጋቢት 28 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 254780 በቀን 01/03/2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የከተማ ቤት ሁከት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች ከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በቀድሞ አጠራር ወረዳ 05 ቀበሌ 15 በአሁኑ በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የሚገኝ ቁጥሩ 1141 የሆነ ቤት ከወላጆቻቸው በውርስ የተላለፈላቸው እና በቀን 24/05/2008 ዓ.ም በስማቸው ካርታ የተሰጣቸው መሆኑን፤ በዚሁ ቤት ግቢ ውስጥ አውራሾቻቸው በሕይወት እያሉ የዋናው ቤት አካል ሆኖ የሚጠቀሙበትን ማድቤት እና መጸዳኛ ቤት ያለ መሆኑን፤ ወላጆቻቸው በሕይወት እያሉ ማድቤቱን በችግር ላይ ለነበረች ሴት ለጊዜው ሰጥተዋት የነበሩ መሆኑን፤ ሆኖም አዋጁ ሲታወጅ የሴትየዋ ልጅ በወቅቱ ቀበሌ ይሰራ ስለነበር ስልጣኑን ተጠቅሞ ቤቱን እንደተከራየ አድርጎ ቁጥር 1140 የሚል ቁጥር ያሰጠው መሆኑን፤ ግለሰቧም ቤቱን ለቃ ለአውራሻቸው ሳታስረክብ የሄደች መሆኑን፤ አመልካቾች በይዞታቸው ስር አድርገው ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑን፤ ሆኖም 1ኛው ተጠሪ በሰጣቸው ካርታ ላይ ይህንኑ ማድቤት እና መጸዳኛ ቤት የመንግስት ብሎ በመስራት፤ 2ኛ ተጠሪም ቤቱ የራሴ ነው በማለት ሁከት እየፈጠሩባቸው የሚገኙ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪዎች የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ በሰጡት መልስ የአመልካቾች አውራሾች ክስ የቀረበበትን ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 አስረክበዋል፤ 2ኛ ተጠሪ ቀደም ሲል ቤቱን ለአቶ ወርቁ አበዙ አከራይቶ ኪራይ ሲሰበስብበት የቆየ ነው፤ ተከራይ ቤቱን በምን አግባብ እንደለቀቀ ሳይታወቅ አመልካቾች ክስ የቀረበበትን ቤት ቀላቅለው ይዘዋል፤ ስለሆነም ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ፤ ቁጥራቸው 1140 እና 1141 የሆኑትን ቤቶች ማሕደሮች አስቀርቦ ከተመለከተ እና ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲላክለት ካደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች ካርታ ያቀረቡ ቢሆንም አከራካሪው መጸዳጃ ቤት እና ማዕድ ቤት በይዞታ ማረጋገጫ ካርታው ውስጥ የማይካተት መሆኑ ተረጋግጧል፤ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል በሰጠው መልስ ቁጥሩ 1140 የሆነው ቤት መጸዳኛ ቤት እንደሆነ እና አመልካቾች የያዙት ቢሆንም በሲአይኤስ ላይ የቀበሌ ቤት በሚል የተፈለጸ ነው የሚል ምላሽ ልኳል፤ 2ኛ ተጠሪ የመንግስት ነው የሚለው ቤት አመልካቾች ለመጸዳጃ ቤት የሚገለገሉበት እና 2ኛ ተጠሪም ይህን ቤት እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ ሲያከራየው የነበረ ነው፤ 2ኛ ተጠሪ ቤቱ በምን አግባብ ከእጁ ሊወጣ እንደቻለ አላስረዳም፤ የአመልካቾች ምስክሮች አመልካቾች ቤቱን ሲገለገሉበት እንደነበረ ያስረዱ ቢሆንም ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ ስለሌለ አከራካሪው ቤት የአመልካቾች አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ጸንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የስር ፍርድ ቤት ከቀረበለት የሁከት ይወገድልኝ ክስ ጭብጥ ወጥቶ የባለቤትነት ፍርድ መስጠቱ አግባብ አይደለም፤ ሁከት እንዲወገድ በሚል በሚቀርብ ክስ ላይ ተከሳሽ የሚያነሳው ባለቤትነትን የተመለከተ ክርክር አግባብነትት የለውም፤ አመልካቾች ወደፊት ለክርክሩ መነሻ በሆነው መኖሪያ ቤት ላይ

የምናነሳውን የባለይዞታነት ክርክር በሚገድብ መልኩ የተሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ሁከት ይወገድ የሚል ክስ አቅርበው ሳለ አከራካሪው ቤት የአመልካቾች የግል ሀብት አይደለም በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪዎች መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች የአመልካቾች መሆን አለመሆናቸው ጭብጥ ተይዞ ውሳኔ የተሰጠው አመልካቾች የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን በመግለጽ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ስላቀረቡ ነው፤ የስር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አስፈላጊ የሆነውን ጭብጥ በመያዝ እና አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በማስቀረብ ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ ውሳኔው ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት 1ኛው ተጠሪ በሰጣቸው ካርታ ላይ አከራካሪ የሆነውን ማድቤት እና መጸዳጃ ቤት የመንግስት ብሎ በመስራት፤ 2ኛ ተጠሪም ይህንኑ ቤት የራሴ ነው በማለት ሁከት የፈጠሩብን በመሆኑ ሁከቱ እንዲወገድልን የሚል ነው፡፡ ሆኖም የአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ ሁከት ይወገድልን የሚል ቢሆንም ይህንኑ ዳኝነት ሊጠይቁ የቻሉት አከራካሪ የሆነው ማድቤት እና መጸዳጃ ቤት ከአውራሾቻቸው የወረሱት ቤት አካል መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ ይህም አመልካቾች የአከራካሪው ማዕድ ቤት እና መጸዳጃ ቤት ባለቤት መሆናቸውን በመግለጽ በዚሁ ቤት ላይ ተፈጠረ የሚሉት ሁከት እንዲወገድ ክስ ያቀረቡ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች አከረካሪ የሆነው ማዕድ ቤት እና መጸዳጃ ቤት የቀበሌ ቤት መሆኑ እና 2ኛ ተጠሪም እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ ሲያከራየው የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/1 መሠረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የለውም፡፡
በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት በአከራካሪው ማዕድ ቤት እና መጸዳጃ ቤት ላይ በተጠሪዎች ተፈጥሯል የሚሉት ሁከት እንዲወገድ የሚል ቢሆንም ይህንኑ ዳኝነት ሊጠይቁ የቻሉት አከራካሪ የሆነው ማድቤት እና መጸዳጃ ቤት ከአውራሾቻቸው የወረሱት ቤት አካል መሆኑን እና የቤቱ ባለቤት መሆናቸውን በመግለጽ በመሆኑ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የስር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ፍርድ ቤት ጉዳዩን አጣርቶ አመልካቾች የአከራካሪው ማዕድ ቤት እና መጸዳጃ ቤት የአመልካቾች የግል ሐብት አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ አመልካቾች ለጠየቁት ዳኝነት ምላሽ የሰጠ እና በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 276300 መጋቢት 28 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 254780 በቀን 01/03/2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
3. ሚያዝያ 05 ቀን 2013 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ፡- 203809

ቀን፡-26/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- 1. ወ/ሮ የብርኳል በላይነህ } አልቀረቡም
2. አቶ ተክሌ ዝብሉ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ እቴነሽ መብራት } ወኪል ሙላቱ ባንቲጌ ቀረቡ
2. ወ/ሮ አስረሳች መብራት

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

<u>ፍርድ</u>

ጉዳዩ የይግባኝ ማስፈቃጃ አቤቱታን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካቾች የአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01-18421 ሕዳር 11 ቀን 2012 ዓ/ም በሠጠው ውሳኔ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለማቅረብ የ60 ቀናት ጊዜው ያለፈባቸው በመሆኑ ጥር 20 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ በማቅረብ ጊዘው ያለፈው የኮሮና ወረሽኝ በሽታ በመኖሩ፣ በሚኖሩበት አካባቢ የጸጥታ ችግርና የትራንስፖርት ችግር ያጋጠማቸው መሆኑን በመጥቀስ ከአቅም በላይ

የሆኑ ምክንያቶች መሆናቸውን በማንሳት ይግባኙን ማቅረብ እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በአቤቱታው ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ካደረገ በኋላ ይግባኝ የሚባልበት ፍርድ የተሰጠው ሕዳር 11 ቀን 2012 ዓ/ም ሲሆን የኮሮና ወረሽኝ የተከሰተው ደግሞ ከየካቲት ወር 2012 ዓ/ም በኋላ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች በኮሮና ወረሽኝ ምክንያት በከፊል ተዘግተው የነበረ ቢሆንም በሙሉ ሥራ ከጀመሩ በኋላ አቤቱታው የቀረበው ዘግይቶ ከአምስት ወር በኋላ ነው፡፡ የአገሪቱ የጸጥታ ችግርም አልፎ አልፎ የሚከሰት በመሆኑ አመልካቾች ይግባኝ ለማቅረብ ከወሰዱት የአንድ ዓመት ከሁለት ወር ጊዜ አኳያ እንደበቂ ምክንያት የሚታይ አይደለም፤ በአመልካቾች ቸልተኝነት ጊዜው ያለፈ ስለመሆኑ ይግባኙን እንዲያቀርቡ ሊፈቀድ አይገባም በማለት የቀረበው የማስፈቀጃ አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡

የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካቾች የሠበር አቤቱታ ይዘትም አመልካቾች ከምንኖርበት ሻኪሶ ከተማ አስተዳደር የጸጥታ ችግር፣ መንገድ መዘጋት፣ ኔትወርክ መቋረጥ እንደነበር ማስረጃ አቅርበናል፡፡ በሽብር ኃይሎች የአመልካቾች ወኪል ታፍኖና ተደብድቦ ነበር፡፡ ውሳኔው የተሰጠበት ፍርድ ቤት ከአመልካቾች አድራሻ አንጻር ሩቅ ነው፤ ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች ስላጋጠመን ይግባኙን እንድናቀርብ ሊፈቀድ ይገባል የሚል ሲሆን የሠበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አመልካቾች በሚኖሩበት አካባቢ የጸጥታ ችግር መኖሩ ማስረጃ በቀረበበት ሁኔታ ይግባኙ ጊዜው ያለፈው በአመልካቾች ቸልተኝነት ነው መባሉ ተገቢነቱን ለማጣራት ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ አዟል፡፡ ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ይግባኙ አንድ ዓመት ከሁለት ወር ጊዜ ያለፈበት ነው፤ አመልቾች በቂ ምክያት ያላቀረቡ በመሆኑ ውሳኔው ሊጸና ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አመልካቾች ያቀረቡት ይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ ውድቅ መደረጉ ሕጋዊነቱን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 323(2) መሠረት ይግባኝ የሚቀርበው ውሳኔው በተሰጠ በ60 ቀናት ወስጥ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ የይግባኝ ማመልከቻው ጊዜ ያለፈበትና የማይመረመር ነው፡፡ አመልካቾች ይግባኝ ያቀረበቡትን ውሳኔ የሠጠው በአማራ ክልል የአዊ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሕዳር 11 ቀን 2012 ዓ/ም ነው፡፡ አመልካቾች ይግባኝ ግልባጭ እንዲሰጣቸው የጠየቁት አመት ከሁለት ወር ጊዜ በኋላ ጥር 19 ቀን 2013 ዓ/ም ነው፡፡ ይሕም 60 ቀናት ጊዜው ያለፈ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ በዚህም ምክንያት ይግባኝ ለሚቀበለው ፍርድ ቤት ጥር 20 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ ይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ክርክር ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ወጭና ጊዜ ቆጣቢ እንዲሁም ፍትሐዊ በሆነ ሁኔታ እንዲመራ ዓላማ አድርጎ የተቀረጸ ነው፡፡ አቤቱታዎች ሆኑ ክርክሮች ሲቀርቡ ሕጉ ሊያሳካው ከፈለገው ግብ ጋር ተመዛዝኖ መወሰን አለበት፡፡ በውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኝ በማቅረብ አቤቱታው እንዲመረመርለት ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው ቢሆንም መብቱ ለማስከበር ደግሞ ጥንቃቄ የታከለበት ትጋት እንዲኖረው ሕጉ ይጠበቅበታል፡፡

አመልካቾች የሚከራከሩት ጊዘው ያለፈው ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች የኮሮና ወረርሽኝ በሽታ መከሰት፣ በሚኖሩበት አካባቢ የጸጥታ ችግርና የትራንስፖርት ችግር ያጋጠማቸው መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 326(1) እንደተመለከተው ፍርድ ቤቱ የቀረበው ምክንያት በቂ ስለመሆኑ ካመነበት ይግባኙን እንዲያቀርቡ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ውሳኔ የተሰጠው ሕዳር 11 ቀን 2012 ዓ/ም ሲሆን በኢትዮጵያ የኮሮና በሽታ በወረሽኝ መልክ የታወጀው ይግባኝ ማቅረቢያ 60 ቀናት ካለፈበት ጊዜ በኋላ በመሆኑ የኮሮና ወረሽኝ በሽታ ይግባኙን በጊዜው ላለማቅረብ በቂ ምክንያት አይደለም፡፡ አመልካቾች በሚኖሩበት አካባቢ የጸጥታ ችግርና የትራንስፖርት ችግር በመኖሩ ነው ይግባኙን በጊዜው ያላቀረብነው የሚለውን ምክንያት በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት ችግሩ የሚያጋጥም መሆኑን ተቀብሏል፡፡ ነገር ግን አቤቱታውን ውድቅ ያደረገው አመልካቾች የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈባቸው ከአንድ ዓመት ከሁለት ወር ጊዜ መሆኑ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ የተፈጠረው የፀጥታ ችግር ለዚህን ያሕል ጊዜ ይግባኝ እንዳያቀርቡ የሚከለክል ስለመሆኑ አሳማኝ አይደለም በማለት ነው፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤት በአመልካቾች የቀረቡትን ምክንያቶች አመዛዝኖ ባለው ፍቅድ ሥልጣን አግባብ የወሰነው በመሆኑ በዚህ ችሎት ደረጃ የሚመረመር መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አላገኘንበትም፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 55100 የካቲት 25 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡

2. ግራቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- ❖ ውሳኔው ለሥር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡
- ❖ አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- ❖ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ.203747
መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. አንዳርጌ ከበደ } ጠበቃ ክንፈ ዋለ ቀረቡ

2. ትዕግስት ከበደ

ተጠሪ፡- ሀብታሙ ላቀው- አልቀረቡም

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች መጋቢት 01 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 142024 ጥር 21 ቀን 2012 ዓ.ም ተጠሪ አከራካሪውን ቤት ሕዳር 05 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል ገዝቶ የያዘ በመሆኑ ቤቱን ለቆ ሊያስረክብ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 251737 ጥር 28 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ወሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የቤት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች ከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ቀበሌ 07 ክልል ውስጥ በካርታ ቁጥር የካ/164566/03 የሚታወቅ ስፋቱ 150 ካ.ሜ የሆነ በአባታቸው ስም የተመዘገበ ቤት ያላቸው መሆኑን፤ ተጠሪ በዚሁ ይዞታ ውስጥ የሚገኙትን ሰርቪስ ቤቶች አላግባብ የያዘ እና ቤቱን እንዲለቅ ሲጠየቅ ከእናታችሁ ገዝቻለሁ በማለት ለመልቀቅ ፍቃደኛ አለመሆኑን፤ ሆኖም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪ ቤቱን የገዛ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ በቤቱ ማሕደር ላይም ሆነ በሰነዶች ማረጋገጫ ጽ/ቤት የሌለ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ ቤቱን ለቆ እንዲያስረክባቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ ደግሞ አከራካሪውን ቤት የአመልካቾች እናት ወ/ሮ ብርቱካን ጋሻውብዛ አመልካቾችን በመወከል እና በራሳቸውም ስም ከወ/ሮ ጽጌ ከበደ እና ወ/ሮ ህብስተመና ከበደ ጋር በመሆን ሕዳር 05 ቀን 1997 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል በብር 17,000 የሸጡለት መሆኑን፤ አመልካቾች በአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ሆነው 1ኛ አመልካች በቀን 15/06/1997 ዓ.ም፤ 2ኛ አመልካች በቀን 21/06/1997 ዓ.ም እንዲሁም አመልካቾች በጋራ በመሆን በቀን 13/11/1997 ዓ.ም ለወላጅ እናታቸው ውክልና ሰጥተዋል፤ ውክልናውም ቤቱን እንዲሸጡ እና እንዲለውጡ ስልጣን የሚሰጣቸው በመሆኑ በዚሁ ውክልና መሠረት ቤቱ ከተሸጠ በኋላ አላግባብ የቀረበው ክስ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ እና ከሚመለከተው አካል ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ አመልካቾች ለእናታቸው ወ/ሮ ብርቱካን ጋሻውብዛ በሰጡት ውክልና መሠረት እናታቸው ከወ/ሮ ጽጌ ከበደ እና ወ/ሮ ሕብስተመና ከበደ ጋር በመሆን አከራካሪውን ቤት ለተጠሪ የሸጡለት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ቀርቧል ምስክሮችም ይህንኑ አስረድተዋል፤ የሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ጽ/ቤት አመልካቾች በማረሚያ ቤት ውስጥ ሆነው ለእናታቸው ውክልና ሰጥተው በቀን 18/11/1997 በጽ/ቤቱ የተመዘገበ መሆኑን በማረጋገጥ ምላሽ ሰጥቷል፤ ውክልናው አመልካቾች በውርስ የሚያገኙትን ንብረት የመሸጥ ስልጣን የሚሰጥ መሆኑ ተረጋግጧል፤ ተጠሪ ቤቱን የገዛው አመልካቾች ለእናታቸው ውክልና ከመስጠታቸው በፊት ህዳር 5 ቀን 1997 ዓ.ም ቢሆንም አመልካቾች የጠየቁት ዳኝነት አላግባብ ተጠሪ የያዘውን ይዞታ ለቆ እንዲያስረክባቸው ነው፤ አመልካቾች ቤቱ እንዲሸጥ ውክልና ከመስጠታቸው በፊት ተጠሪ ቤቱን የገዛ ቢሆንም ውሉ የፈረሰ ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ ቤቱን አላግባብ ይዟል ማለት ስለማይቻል ተጠሪ ቤቱን ለአመልካቾች ሊያስረክብ አይገባም፤ አመልካቾች ሕዳር 5 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው ውል ሊፈርስ ይገባል የሚሉበት ምክንያት ካላቸው ክስ የማቅረብ መብታቸው ተጠብቋል በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ጸንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የአከራካሪውን ይዞታ ስፋት 150 ካ.ሜ ሆኖ ሳለ ተጠሪ 220 ካ.ሜ ይዞታ በምን አግባብ እንደገዛ አልተጣራም፤ ተጠሪ ገዛሁ በሚለው በ220 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ግብር ስለመክፈሉ ያቀረበው ማስረጃ የለም፤ የአመልካቾች እናት የቤቱ ባለቤት ስለመሆኗ አልተረጋገጠም፤ የሽያጭ ውሉ አመልካቾች ለእናታቸው ውክልና ከመስጣቸው በፊት መደረጉ በተረጋገጠበት ሁኔታ በሕግ አግባብ እንደተደረገ ውል ተቆጥሮ ተጠሪ ቤቱን ሊያስረክብ አይገባም በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአሁን አመልካች ለእናታቸው ሰጡ የተባለው ውክልና ከቤቱ ሽያጭ በኋላ የተደረገ ሆኖ ሳለ የጸና የቤት ሽያጭ ውል መኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካቾች የውል ይፍረስ ክስ ማቅረብ ነበረባቸው ተብሎ ክሳቸውን ውድቅ በማድረግ የመወሰኑን አግባብነት ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ጋር በማገናዘብ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የአመልካቾች እናት የሽያጭ ውሉን ለመዋዋል የማይችሉ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፤ ቤቱን የሸጡልኝ የአመልካቾች እናት በፍርድ እስካልተከለከሉ ድረስ ውል ለመዋዋል ይችላሉ፤ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን 220 ካ.ሜ ይዞታ ላይ የተሰራ ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤት የገዛሁት በሟች አቶ ከበደ ወልደኪዳን ስም ተመዝግቦ ከሚገኘው 457.43 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ተቀንሶ ነው፤ የሽያጭ ውሉ የተፈጸመው በአመልካቾች እውቅና እና ፍቃድ ስለመሆኑ ለእናታቸው የሰጡት ውክልና ያሳያል፤ የሽያጭ ውሉ ጸንቶ ባለበት ሁኔታ ተጠሪ ከአሥራ አምሥት ዓመት በፊት በግዥ የያዝኩትን ቤት ለአመልካቾች የማስረክብበት ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ ውሳኔው ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካቾች በማረሚያ ቤት ሆነው ለእናታቸው ወ/ሮ ብርቱካን ጋሻውበዛ ሰጥተውታል የተባለው ውክልና በቀን 18/11/1997 ዓ.ም በሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበ መሆኑ የተረጋጠ ፍርነገር ነው፡፡ ሆኖም ተጠሪ ቤቱን የገዛው አመልካቾች ለእናታቸው ውክልና ሰጥተውበታል ከተባለበት ከቀን 18/11/1997 ዓ.ም በፊት ሕዳር 5 ቀን 1997 ዓ.ም መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት መረጋገጡ በውክልናው ሕጋዊነት ላይ ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ቤቱን ሸጠዋል የተባሉት የአመልካቾች እናት ወ/ሮ ብርቱካን ጋሻውበዛ፤ ወ/ሮ ጽጌ ከበደ እና ወ/ሮ ሕብስተመና ከበደ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 40/2 መሠረት በክርክሩ ተከፋይ መሆን የሚገባቸው ናቸው፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 43226 በሰጠው ውሳኔ በሕግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ዳኞች ውሉ በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ሕጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት የለውም በማለት ለመወሰን እንደሚችሉ በመግለጽ በየትኛውም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩ ሲታይ አመልካቾች በውርስ የሚደርሳቸውን ድርሻ እንዲሸጡላቸው ለእናታቸው ውክልና ከመስጠታቸው በፊት ተጠሪ ቤቱን መግዛቱ እስከተረጋገጠ ድረስ የሽያጭ ውሉ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑ ተመርምሮ የውሉ ሕጋዊ ዉጤቱ ምን እንደሆነ በቅድሚያ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዚህ አግባብ በማየት በቅድሚያ በውሉ ሕጋዊ ውጤት ላይ ምላሽ መስጠት ሲገባው የሽያጭ ውሉ ጸንቶ ባለበት ሁኔታ ተጠሪ ቤቱን ለቆ ሊያስረክባቸው አይገባም፤ አመልካቾች ውሉ ሊፈርስ ይገባል የሚሉበት ምክንያት ካላቸው ክስ የማቅረብ መብታቸው ተጠብቋል በማለት የሰጠው ውሳኔ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 43336 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚጥስ እና አመልካቾችን ለተጨማሪ ክርክር የሚጋብዝ፤ ክርክሮች በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጪ እንዲቋጩ ለማድረግ ታስቦ የወጣውን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉን ዓይነተኛ ዓላማ ያላገናዘበ መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ስለሆነም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች ለእናታቸው ወ/ሮ ብርቱካን ጋሻውበዛ በቀን 18/11/1997 ዓ.ም የውክልና ሥልጣን ከመስጠታቸው በፊት ሕዳር 5 ቀን 1997 ዓ.ም ተደርጓል የተባለው የቤት ሽያጭ ውል ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን ቤቱን ለተጠሪ ሸጠዋል የተባሉትን የአመልካቾች እናት ወ/ሮ ብርቱካን ጋሻውበዛ፤ ወ/ሮ ጽጌ ከበደ እና ወ/ሮ ሕብስተመና ከበደ ወደ ክርክሩ በማስገባት አግባብነት ያለውን ትዕዛዝ በመስጠት ጉዳዩን አጣርቶ እና መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ ሥነ-ሥርዓታዊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 142024 በቀን 21/05/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 251737 ጥር 28 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሳኔ የዘጋውን መዝገብ እንደገና በማንቀሳቀስ ከላይ በፍርድ ሐተታው ላይ በተገለጸው መንገድ ጉዳዩን አጣርቶ ተገቢውን እንዲወስን በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

ማ/አ   የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ. 203654
ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. ቤተልሄም ጌቱ አለሙ
2. እንግዳ ወርቅ አይናለም
3. አዜብ ጌታሁን
4. ህይወት ጌታቸው ታደሰ
5. ሩሚያ ጁሀር ኑሬ
} አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የፌ/ጠ/ ዐቃቤ ህግ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መ.ቁ. 05450 የካቲት 01 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠውን ብይን፤ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መ.ቁ. 00159 የካቲት 26 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካቾች ላይ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- የሙስና ወንጀል አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31(1) እና (2) በመተላለፍ አመልካቾች የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽመዋል የሚል ነው፡፡ የአሁን አመልካቾች ክሱን በሚመለከት ያቀረቡት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መቃወሚያ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀጽ 78(2)፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማደራጀ አዋጅ ቁጥር 322/96 አንቀጽ 2 እና በአዋጅ ቁጥር 434/97 መሰረት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም፣ አመልካቾች እምነት አጉድለዋል የተባለበት የግል የጤና አገልግሎት ከሚሰጥ ድርጅት ጋር በተያያዘ እንጂ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የመንግስት የልማት ድርጅት ባለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ስር ክስ ሊቀርብ አይገባም በማለት ከክሱ በነፃ እንዲሰናበቱ ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀጽ 7(2) በክልል መንግስት ስር የሚወድቁ የሙስና ወንጀሎች በሚመለከት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው መቃወሚያ ውድቅ አድርጎታል፣ ሆኖም ግን የግል ተበዳይ ሐረር ጠቅላላ ሆስፒታል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በህክምና ባለሙያዎች በግል በራሳቸው ሀብት እና ንብረት የተቋቋመ የግል ኩባንያ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 2(4) አንቀጸ 5፣6 እና 7 መሰረት በህዝባዊ ድርጅት ውስጥ የሚካተት ኩባንያ አይደለም፣ በመሆኑም አመልካቾች የግል ተበዳይ ሐረር ሆስፒታል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሰራተኞች ሆነው ለተጠረጠሩበት የሙስና ወንጀል ክስ አዋጅ ቁጥር 881/2007 ተፈጻሚነት የለውም በማለት በነፃ እንዲሰናበቱ ብይን ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ይህን ብይን በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤትም በአዋጅ ቁጥር 2(4) ስር "ህዝባዊ ድርጅት" ለሚለው ከተሰጠው ትርጓሜ አግባብነት ያለው "ኩባንያ" የሚለው አገላለጽ አንቀጽ 2 (6) "በህዝባዊ ድርጅት የተቋቋሙ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ሲሆን የሽርክና ማህበር ያጠቃልላል" በማለት የቃሉን ትርጉም ተሰጥቶበታል በመሆኑም ከአዋጁ አጠቃላይ መንፈስ ህዝባዊ ድርጅት አግባብነት ያለው ኩባንያ እና የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኞ አገላለጾች በህጉ የተሰጣቸው ትርጉም አዋጅ ለትርፍ የተቋቋሙ የግል ተቋማት ላይ ተፈጻሚነት እንዳለው በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ በአዋጁ አይታይም በማለት የሰጠውን ብይን ሽሮ በአመልካቾች ላይ የቀረበው ክስ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ የሚመለከት ጉዳይ ስለሆነ የስር ፍርድ ቤት ጉዩን እንዲያየው በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ ብይን በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጸንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ከአዋጅ ቁጥር 881/2007 ይዘት እና አላማ ውጪ አዋጁ የግል ድርጅት ሰራተኞችም ላይ ተፈጻሚነት አለው በማለት የሰጠው ብይን አንቀጽ 2(4) ስር የተሰጠውን የህግ ትርጉም የሳተ መሆኑን እንዲሁም ለጭብጡ እና ለብይኑ ዝርዝር ምክንያት ያደረገውን የህግ ትንታኔ በምን ምክንያት ውድቅ እንዳደረገው ሳይገለጽ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ብይን መሻሩ ይህም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የአሁን አመልካቾች የሚሰሩበት ሆስፒታል ህዝባዊ ድርጅት ነው በሚል በአዋጅ ቁጥር 881/07 አንቀጽ 31 በሙስና ወንጀል ሊከሰሱ ይገበል ተብሎ የተወሰነበትን አግባብ ከዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ ፣ 4 እና ተያይዞ ካሉት ድንጋጌዎች መሰረተ መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የግል ተበዳይ የሆነው የሐረር ጠቅላላ ሆስፒታል ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የገንዘብ ምንጩ ከአባላት በተሰበሰበ በአክሲዮን ግዥ በተገኘ ገንዘብ ከሚሰጠው የህክምና አገልግሎ ባፈራው ገንዘብ፣ ንብረት እና ሀብቶች የሚስተዳደር የግል ዘርፍ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 32/2 ስር የሚወድቅ ሲሆን አመልካቾች በዚሁ ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኞች በመሆናቸው በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 32(2) መሰረተ ሊጠየቁ ይገባቸዋል፤ የአዋጁ ተፈጻሚነት በመንግስት ሰራተኞች ላይ ብቻ ተደርጎ መወሰዱ ከአዋጁ ይዘት እና አላማ ጋር የሚፃረር ነው፤ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነውም በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽማችኋል በሚል የሙስና አዋጅን ጠቅሶ ተጠሪ ክስ የመሰረተባቸው ሲሆን የሙስና ወንጀሉ ተፈፀመ የተባለውም አመልካቾች ሲሰሩበት የነበረው የግል ተበዳይ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡
ከማስቀረቢያ ነጥቡ አኳያ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው የግል ተበዳይ ድርጅት ህዝባዊ ድርጅት ሊባል የሚገባው ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው በመሆኑ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የግል ተበዳይ የሆነው የሐረር ጠቅላላ ሆስፒታል ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የገንዘብ ምንጩ ከአባላት በተሰበሰበ በአክሲዮን ግዥ በተገኘ ገንዘብ ከሚሰጠው የህክምና አገልግሎት ባፈራው ገንዘብ፣ ንብረት እና ሀብቶች የሚስተዳደር ነው፡፡
በአዋጅ ቁጥር 881/2007 አስቀድሞ የነበረውን የሙስና አዋጅ ያሻሻለበት ዋና አላማን በመግቢያው ሲያብራራ ፡- "--------- የሙስና ወንጀሎቹ ማካተት የነበረባቸውን ተመሳሳይ ተግባራት በተለይም ከህዝብ የተሰባሰበ ወይም ለህዝብ ተብሎ የተሰባሰበ ሀብት በሚያስተዳድሩ የግል ዘርፍ አካላት የሚፈፀሙ ተመሳሳይ ተግባራትን በአግባቡ ያላካተቱ በመሆናቸው እነዚህኑ ማካተት በማስፈለጉ፣----"
በሚል ዓላማውን ይዘረዝራል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2/4 ስርንሜ ስር፡- “ ህዝባዊ ድርጅት ማለት በማንኛውም አግባብ ከአባላት ወይም ከህዝብ የተሰበሰበ ወይም ለህዝባዊ አገልግሎት ታስቦ የተሰበሰበ ገንዘብ፣ ንብረት ወይም ሌላ ሃብትን የሚያስተዳድር አካልና አግባብ ያለው ኩባንያን የሚያካትት የግል ዘርፍ ሲሆን፣ የሚከተሉትን አያካትትም፡-

ሀ. የሀይማኖት ድርጅትን፣

ለ/ የፖለቲካ ድርጅትን/ፖርቲን/፣

ሐ/የዓለም አቀፍ ድርጅትን፣ እና

መ/ ዕድርንና ተመሳሳይ ባህላዊ ወይም ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ማህበርን፡፡ “

በሚል ይደነግጋል፡፡

እንዲሁም በአንቀጽ 2/6 ስር ፡- “ አግባብነት ያለው ኩባንያ ማለት በሕዝባዊ ድርጅት የተቋቋመ ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ ሲሆን እንደዚህ ዓይነት ኩባንያ ከሌሎች ጋር የሚቋቋመውን የሽርክና ማህበርን ያጠቃልላል፣” በሚል ይደነግጋል፡፡

ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አመልካቾች የሚሰሩበት የግል ተበዳይ የሆነው የሐረር ጠቅላላ ሆስፒታል ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የገንዘብ ምንጩ ከአባላት በተሰበበሰበ በአክሲዮን ነው፡፡ አክስዬን ማህበር ደግሞ ኩባንያ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው የቀድሞው የሙስና አዋጅ በአዲስ እንዲሻሻል የተፈለገበት ዓላማ የሃይማኖት ተቋማት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣የዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ዕድሮች እንዲሁም እነዚህን የመሳሰሉ የሃይማኖት እና የባህላዊ ማህበራት እስካልሆኑ ድረስ የሙስና ወንጀል በህዝባዊ ድርጅቶች እና በኩባንያዎች ውስጥ በሚፈፀመ ጊዜ በአዋጁ የማይሸፈን በመሆኑ በአዋጁ እንዲጠቃለል የተደረገ መሆኑን ነው፡፡

የግል ተበዳይ ኩባንያ ምንም እንኳን በግለሰቦች የተመሠረተ ቢሆንም ነገር ግን በአዋጁ ድንጋጌ መሠረት በኩባንያ ውስጥ የሙስና ወንጀል በተፈፀመ ጊዜ በሙስና አዋጅ ክስ የሚመሰረት መሆኑን የሚያስገነዝብ በመሆኑ በአመልካቾች ላይ የሙስና አዋጅን በመጥቀስ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽመዋል በሚል የቀረበውን ክስ የስር ፍ/ቤት ተገቢ ነው ሲል የደረሰበት መደምደሚያም ሆነ የበላይ ፍ/ቤት መቀበሉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ፈጽሟል ለማለት የማይቻል ስለሆነ ሊፀና የሚገባው ነው ብለን ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1) የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 00159 በ25/06/2012 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣የሀረሪ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/05450 በ1/6/2013ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣ ፣የሀረራ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 20950 ጥር 05 ቀን 2013 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 195/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2) የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረስ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሃሳብ ልዩነት

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 3 የተመለከተው ዳኛ በያዝነው ጉዳይ የግል ተበዳይ ሆኖ የቀረበው የሐረር ጠቅላላ ሆስፒታል ኃ/የተ/የግ/ማህበር በአዋጁ መሠረት ህዝባዊ ድርጅት በመሆኑ አዋጅ ቁጥር 881/2007 ን መሠረት በማድረግ በአመልካቾች ላይ ክሱ መቅረቡ አዋጁን መሠረት ያደረገ ነው በማለት በአብላጫ ድምፅ የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በማፅናት በተሰጠው ውሳኔ የማልስማማ በመሆኑ የልዩነት ሀሳቤን እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ ተሻሽሎ የወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 ወደ ኢትዮጵያ የህግ ማዕቀፍ የመጣው የቀደሙት የሙስና ህጎች በወንጀል ድርጊትነት መካተት የነበረባቸውን በተለይም ከህዝብ የተሰበሰበ ወይም ለህዝብ ተብሎ የተሰበሰበ ሀብት በሚያስተዳድሩ የግል ዘርፍ አካላት የሚፈፀሙ ህገወጥ ተግባራትን አካትተው ያልተቀረፁ በመሆናቸው እነዚህን ማካተት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ መሆኑ በአዋጁ መግቢያ ላይ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ህጉ ከላይ እንደተመለከተው በመግቢያው ላይ የግል ዘርፍ / private sector / የሚለውን ሀረግ የተጠቀመ ቢሆንም በህጉ የትርጉም ክፍል አንቀፅ 2/4/ እና 2/5/ እንዲሁም በዝርዝር የወንጀል ድንጋጌዎቹ ላይ በተደጋጋሚ የተጠቀመው ህዝባዊ ድርጅት /public organization/ የሚለውን ከማካተት አንፃር ጠበብ ብሎ የተቀረፀውን ሀረግ ነው፡፡ በህጉ አንቀፅ 2/4/ የተመለከተው ህዝባዊ ድርጅት ለሚለው ሀረግ የተሰጠው ትርጉም ሰፋ ብሎ የተመለከተ መሆኑን በማስመልከት በሥራ ባልደረቦቼ የተሰጠውን ገለፃ የምስማማበት ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ አንድ ድርጅት ህዝባዊ ድርጅት ለመባል በሁለት መስፈርቶች ማለትም በምንጭ መስፈርት እና /ወይም በግብ መስፈርት / The source-purpose test/ ሊሰፈር የሚገባ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እነዚህ መስፈርቶች በአንድነት ማሟላት አለባቸው ወይስ የለባቸውም በሚለው ነጥብ ላይ የዘርፉ ፀሀፍት የተለያየ አቋም የሚያንፀባርቁ ቢሆንም አንድ ድርጅት ህዝባዊ ድርጅት ነው ለማለት መስፈርቶቹ በአንድ ላይ / cumulatively / መሟላት አለባቸው ብዬ አላምንም፡፡

ስለዚህ የገንዘብ ምንጭ ህዝባዊ መሆኑ አልያም ለህዝባዊ አግልግሎት የተሰበሰበ ሀብት ድርጅቱ ማንቀሳቀሱ ድርጅቱን ህዝባዊ ድርጅት ለማለት በቂ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ እዚህ ጋር በህጉ አንቀፅ 2/4/ የገንዘቡን ምንጭ አስመልክቶ በማንኛውም አግባብ ከአባላት ወይም ከህዝቡ የተሰበሰበ ሀብት በማለት ህጉ ምንጩን አስመልክቶ ሰፋ ያለ ትርጉምን የተከተለ ቢሆንም ኩባንያን አስመልክቶ ግን የተለየ ትርጉምን የተከለ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ አግባብነት ያለውን ኩባንያን የሚያካትት መሆኑን በሚያመለክት መልኩ የተቀረፀ ሲሆን አግባብነት ያለው ኩባንያ ማለት ምን ማለት እንደሆን ደግሞ በአንቀፅ 2/6/ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ትርጉም መሠረት አግባብነት ያለው ኩባንያ ማለት … any Private limited company which is established through the contribution of shares…በማለት መመልከቱ ህጉ አግባብነት ያለው ኩባንያ ከሚለው ሀረግ ትርጉም አንፃር ጠበብ ያለ ትርጉም መከተሉን ያሳያል ፡፡ ይህ ትርጉም አክሲዮንን ለህዝብ በመሸጥ የተቋቋሙትን ኩባንያዎች(companes established by share subscription by the public at large) ብቻ የሚያጠቃልል በመሆኑ መስራቾች (Founders) ብቻ ተደራጅተው ያቋቋሟቸው ኩባንያዎች (አክሲዩን ለህዝቡ በመሸጥ ካፒታላቸውን በማሳደግ ህዝባዊ ድርጅትነትን ካልተጎናፀፉ በስተቀር) እንዲሁም ሁለት ግለሰቦች ገንዘብ ወይም ንብረት አዋጥተው ያቋቋሙት ኃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታም የቤተሰብ አባላት የሚያቋቁሙት ከህዝባዊነት ይልቅ ግለሰባዊነት የሚንፀባረቅበት ተቋም በመሆኑ የፀረ ሙስና ህጉ ተሻሽሎ የወጣው እንደዚህ አይነት ምንም አይነት ህዝባዊነት የማይታይባቸውን ድርጅቶች ለመጠበቅ በዚህ አግባብም ታላላቅ የሆኑ የሙሰና ወንጀሎችን ከመዋጋት ይልቅ ተቋሙ ጥቃቅን በሆኑ ህዝባዊ ድርጅት ባልሆኑ ድርጆቶች ጊዜውንና ገንዘቡን እንዲሁም የሰው ሀይሉን ለማባከን ነው ብዬ አላምንም፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ሀላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ ህዝባዊ ድርጅት ነው በሚል በጥቅል የሚወሰድ ትርጉም የአዋጁን ግብ መሠረት ያደረገ ነው ብዬ አላምንም፡፡ ከዚህ ይልቅ የድርጅት ህዝባዊ መሆን እንደ ጉዳዩ አግባብ / case by case / ሊታይና ሊመረመር ይገባል፡፡ መሠረታዊ መስፈርቱም ድርጅቱ አክሲዩንን ለህዝብ በመሸጥ የተቋቋመ ኩባንያ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

(companies established by share subscripition by the public at large) ነው ወይስ አይደለም የሚለው ሊሆን ይገባል ብዬ አምናለሁ፡፡ ይህ ትርጉምም ህጎችን ወይም በህጎች ውስጥ የሚገኙ ድንጋጌዎችን ሀረጎችን እና ቃላቶችን ከአላማቸው አንፃር አይቶ ትርጓሜ የመስጠት አስተሳሰብን የተከለ ዓላማዊነት (purposivism) ፅንሰ ሀሳብን የተከተለ ነው፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ የሐረር ጠቅላለ ሆስፒታል ኃ/የተ/የግ/ማህበር ህዝባዊ ድርጅት መሆን አለመሆን በዚህ አግባብ ተመርምሮ በሥር ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ እልባት ያልተሰጠው በመሆኑ በዚህ አግባብ ተጣርቶ እንዲወሰን ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊመለስለት ይገባ ነበር በማለት ከሥራ ባልደረቦቼ በሀሳብ ተለይቼያለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 203603
ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ብሩክ አስፋው ፡- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የፌደራል ጠቅላይ ዐ/ሕግ ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ብይን ተሰጥቷል፡፡

ብይን

ጉዳዩ አመልካች በኢትዮጵያ የፖሊስ ሰራዊት ላይ እንዳይፈፀም የተከለከለን ድርጊት በመፈፀሙ የወንጀል ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ ተብሎ በእስራት እንዲቀጣ ከተወሰነበት በኋላ የይግባኝ አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜው ስላለፈበት ይግባኙን ጊዜው ካለፈ በኋላ እንዲያቀርብ እንዲፈቀድለት ለከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ያቀረበ ቢሆንም የማቅረቢያ ጊዜው ያለፈውን ይግባኝ ለመቅረብ የሚያስችል በቂ ምክንያት አልቀረበም ተብሎ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪ በቁጥር 02010 የካቲት 16ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ ክሱ አመልካች በ1996ዓ/ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 324(1) እንዳይፈፀም የተከለከለውን ድንጋጌ በመተላለፍ ታሕሳስ 30ቀን 2012ዓ/ም ከምሽቱ 4:20 ሲሆን በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ልዩ ስፍራው ሸንበቆ ምግብ ቤት ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ፖሊሣዊ ሃላፊነቷ የሆነውን የወንጀል መከላከል ተግባር በመፈፀም ላይ የነበረችው ኮንስታብል ደመቀች ገልጋሎ በአመልካች ላይ ሳትደርስበት የለበሰችውን የደንብ ልብስ በመያዝ በቦክስ በመምታቱ በፖሊስ ሰራዊት ላይ የሚፈፀም የጥቃት ወንጀል ፈፅሟል የሚል ክስ አቅርቦበታል፡፡ አመልካች የቀረበበትን የወንጀል ክስ ድርጊት አልፈፀምኩም ሲል በመከራከሩ የተጠሪ ማስረጃ ተሰምቶ መከላከል እንዲጀምር ታዞ መከላከያ ማስረጃውን

ለማዳመጥ ተደጋጋሚ ቀጠሮ የተሰጠው ቢሆንም ወደ ችሎት መቅረብ በማቋረጡ የቀረበበትን ክስ የመከላከል መብቱን መጠቀም እንዳልፈለገ ተቆጥሮ በተጠቀሰበት ድንጋጌ ጥፋተኛ ተብሎ በአንድ ዓመት ከስምት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ጥቅምት 13ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት ተወስኖበታል፡፡

አመልካች በሌለበት የተወሰበት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ እንዲነሣለት ለስር ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረበ ቢሆንም የጥፋተኝነቱም ሆነ የቅጣት ውሣኔው የተወሰነው አመልካቹ በሌለበት ሣይሆን ወደ ፍርድ ቤት መቅረብ በመቋረጡ የመከላከል መብቱን መጠቀም እንዳልፈለገ ተቆጥሮ ነው ሲል ውድቅ ተደርጎበታል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ አመልካች ታህሣስ 30ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ በስር ፍርድ ቤት በተወሰነው ውሣኔ ቅሬታ ቢኖረውም ሕጉ በፈቀደው ጊዜ የይግባኝ አቤቱታውን አለማቅረቡን ጊዜው ያለፈበት ከአቅሙ በላይ በሆነው በኮረና ወርሽንና ከአንዱ ማረሚያ ቤት ወደ ሌላ ማረሚያ ቤት ሲዘዋወር እንዲሁም በፖሊስ ጣቢያ በመቆየቱ እንደሆነ በመዘርዘር ጊዜው ያለፈውን ይግባኝ ለማቅረብ እንዲፈቅድለት የፌደራሉን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጠይቋል፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ የይግባኝ አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈው ከአመልካቹ አቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለመሆኑ የሚያሣምን ምክንያት አልተገኘም ሲል ውድቅ አድርጎበታል፡፡

አመልካች የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲተረምለት ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አመልካች የካቲት 26ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው በስር ፍርድ ቤት በተወሰነበት ውሣኔ ቅር የተሰኘ ቢሆንም የይግባኝ መጠየቂያ ጊዜው ያለፈው ከውሣኔ በኋላ ወደ ማረሚያ ቤት ሣይወሰድ በፖሊስ ጣቢያ በመቆየቱ እንዲሁም ማረሚያ ቤት ከተወሰደ በኋም በማግለያ ቦታ በመቆየቱና እህቱ ታማ ፀበል ያስጠምቅ ስለነበር ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ መሆኑን ቶሎ ባለመስማቱ መሆኑን በመዘርዘር ያቀረበውን አቤቱታ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው ተብሎ እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የይግባኝ መጠየቂያ ጊዜው ያለፈው በበቂ ምክንያት መሆን ያለመሆኑ እንዲጣራ ተጠሪም የመልስ ክርክር እንዲያቀርብ ታዞ የመልስ ክርክሩ ባለመቅረቡ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፋፎ ክርክሩ ተጠናቋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን አመልካች ጊዜው ያለፈበትን የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ እንዲፈቀድለት ያቀረበውን አቤቱታ የመረመረው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአመልካቹን አቤቱታ ውድቅ በማድረጉ እንዲታረም በቀጥታ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ የመቅረቡ ሕጋዊነት በቅድሚያ መመርምር ያለበት መሆኑ ታምኖበታል፡፡

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀፅ 80 (3) ድንጋጌ መሰረት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን የመጨረሻ ውሳኔ ባገኙ ጉዳዮች ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተትን ማረም ነው፡፡ የመጨረሻ ውሣኔ ማለት በፍርድ ቤት ወይም በሌላ የመዳኘት ስልጣን በተሰጠው አካል………የተሰጠ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እና ለጉዳዩ እልባት [የመጨረሻ እልባት የሰጠ] ፍርድ፣ ብይን፣ትዕዛዝ፣ ውሳኔና ወይም የይግባኝ ሂደቱን የጨረሰ ፍርድ ፣ብይን፣ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ እንደሚጨምር የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(5) ይደነግጋል። በመሆኑም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሞበታል የተባለው ፍርድ፣ ውሣኔ ወይም ሌላ እልባት የሚያስገኘው ትዕዛዝ ወይም ብይን ለሰበር ሰሚ ችለቱ ከመቅረቡ በፊት በየደረጃው በሚገኙ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ወይም ችሎቶች እንዲታረም የይግባኝ የክርክር ሂደቶችን በመጠቀም እንደሚገባና ይህ የይግባኝ የክርክር ሂደት መጠናቀቁ ካልተረጋገጠ በስተቀር የመጨረሻ ውሳኔ ነው ተብሎ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊቀርብ እንደማይገባ ተደንግጓል።

በያዝነው መዝገብ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበው ጉዳይ የይግባኝ ጊዜ ካለፈ በኋላ አመልካቹ ይግባኙን ለማቅረብ ፈቃድ እንዲሰጠው የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 191(1) ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የቀረበ አቤቱታ መሆኑን የክርክሩ አመጣጥ ያስገነዝባል። ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም የአመልካችን አቤቱታ ከመረመረ በኋላ የይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈው በአመልካቹ ጥፋት ባልሆነ ምክንያት ስለመሆኑ አላስረዳም ሲል በወ/መ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 191(3) መሰረት ውድቅ አድርጎበታል። የይግባኝ ጊዜው ካለፈ በኋላ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ እንዲፈቀድለት የቀረበው የማስፈቀጃ አቤቱታ ይግባኝ ሰሚ ለሆነው ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበ ነው። ጊዜው ካለፈ በኋላ ይግባኙን ማቅረብ እንዲፈቀድለት የቀረበን አቤቱታ የመረመረው ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ወይም ውሣኔ ያልተስማማ ወገን ቀጥሎ ላለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ማቅብ የማይችል መሆኑን አልደነገገም።

በሌላ በኩል የተከሰሱ ሰዎች ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠባቸው ትዕዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የመጠየቅ መብታቸው ሊከበርላቸው እንደሚገባ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀፅ 20(5) ይደነግጋል። በዚህ መሰረት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበለትን የይግባኝ ማስፈቀጃ አቤቱታ መርምሮ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 191(3) መሰረት የሚሰጠው ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ተፈፅሟል የሚለው የፍሬ ነገር ወይም የማስረጃ ምዘና ስህተት እንዲታረምለት የይግባኝ አቤቱታውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ የማሳረም መብቱን ሊጠቀም ይገባል።

በመሆኑም አመልካች የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል የሚለውን ስህተት እንዲታረም የይግባኝ አቤቱታውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ የመጨረሻ ውሳኔ ማግኘት ሲገባው ይህን ሣይፈፅም የይግባኝ ሂደቱን ያልጨረሰና የመጨረሻ ውሳኔ ያላገኘ ጉዳይ ለሰበር ሰሚ ችሎት በማቅረቡ አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ብቁ አይደለም ተብሎ ተሰርዟል።

ትዕዛዝ

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሰ/መ/ቁ 203538

ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ ሳቢት አባ ዲንካ- ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጣሂር አባ ዲንካ- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች በቀን 26/06/2013 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የሲግሞ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 34088 በቀን 20/06/2013 ዓ.ም፣ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 54191 በቀን 25/03/2013 ዓ.ም፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 224595 በቀን 22/04/2013 ዓ.ም እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 334929 በቀን 20/05/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው። ክርክሩ የውረስ ይዞታ መሬትን የተመለከተ ሲሆን የጀመረው በወረዳ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ነው።

አመልካች በቀን 25/03/2012 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ እናቴ ወ/ሮ አቶሜ አባፎጊ በቀን 20/02/1991 ዓ.ም በሞት ተለይታለች፤ የሟች ወራሽ የሆነው ልጆች ከሳሽና ተከሳሽ ብቻ ነን፤ እናቻችን ትታው ያለፈችው በሁለት ቦታ የሚገኝ ይዞታ ሲሆን በ1ኛው ቦታ ስፋቱ 20 በ 80 የሆነ አዋሳኙ በክሱ የተገለፀው እና በግምት 2000.00 ብር የሚያወጣ ባህር ዛፍ፤ እንዲሁም 2ኛው ቦታ ስፋቱ 20 በ 30 የሆነ አዋሳኙ በክሱ የተገለፀው የሚገኝ ሲሆን ተከሳሽ የውርስ ድርሻየን ከህግ ውጪ ይዞ ስለከለከለኝ ድርሻየን ግማሹን እንዲያካፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት እናታችን ከሞተች 20 አመት ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል ካሉ በኋላ በፍሬ ነገር መልሳቸው ደግሞ 1ኛው ቦታ 20 በ 80 የሆነውና ባህርዛፍ እንዲሁም 2ኛው ቦታ 20 በ30 የሆነው ይዞታ የውርስ መሬት ሳይሆን የግል ይዞታዬ ነው፤ አባቴ በህይወት በነበረ ጊዜ የሰጠኝ ነው፤ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በይዞታው እየተጠቀምኩበት ስለሆነ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክርክሩንና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በ1ኛ ቦታ ያለው መሬት በሚመለከት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፤ በ2ኛ ቦታ ላይ ያለው መሬት በተመለከተ የግራ ቀኙ ምስክሮች በተመሳሳይ ቃል የመሬት ይዞታው የውርስ መሆኑን አረጋግጠዋል፤ ተከሳሽ ይህ መሬት ይዞታ አባቴ በህይወት በነበረ ግዜ በስጦታ የሰጠኝ ነው ከማለት ውጭ በሚያሳምን ሁኔታ ተቀባይነት ባለው መልኩ አባቱ መስጠቱን የሚያሳይ እንዲሁም የግሉ መሆኑን የሚያስረዳ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር፣ የግብር ደረሰኝ ወይም መሬቱ በስሙ መኖሩን እና መጠቀሙን የሚያሳይ ማስረጃ አልተገኘም፤ አከራካሪውን ይዞታ ሲጠቀሙበት የነበሩበት ስለሆነ ወራሾች ለመውረስ መብት ያላቸው በመሆኑ 2ተኛውን የመሬት ይዞታ እኩል እንዲካፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እንዲሁም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ቢያቀርቡም ቀባይነት አላገኙም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት ማመልከቻ የስር ወረዳ ፍ/ቤት ከአከራካሪው 2ኛ ቦታ 20 በ30 በእኩል እንድንካፈል ወስኖልኝ 1ኛው ቦታ 20 በ 80 የሆነውን ተጠሪ ያለአንዳች ምክንያት ከነድርሻዬ ጭምር ይዞ እያለ ተጠሪ በ3 አመት ይርጋ ክሱ ቀሪ ይሆናል ስላለ ብቻ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ፍ/ቤቱ በአግባቡ ሳያጣራ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው ምክንያቱም ይዞታውን እስከ 2011 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር አብረን ስንጠቀም ስለቆየን ከይርጋ ጋር አይገናኝም፤ ተጠሪ ታናሼ በመሆኑ ቤተሰቦቼ ለእኔ ትተው በመሞታቸው አብረን እስከ 2011 ዓ.ም ስንጠቀም ቆይተን በ2011 ዓ.ም ሁከት ፈጥሮብኝ ተጋጭተን ከዛ በኋላ መሬቱን ፈቅደን ወደን ለመከፋፈል አሰብን እንጂ የተጠሪ የግል ይዞታ አይደለም። አባቴ አከራካሪውን 20 በ 80 የሆነ ይዞታ በስጦታ ለተጠሪ አልሰጠም እንጂ ቢሰጥም ህጋዊ የስጦታ ፎርማሊቲ ያላሟላ እና በገጠር መሬት አዋጅ 133/98 አንቀጽ 23/4 መሰረት እና ሰበር በመ/ቁ 115399 በሰጠው ትርጉም መሰረት አግባብ ባለው አካል ያልተመዘገበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም። ተጠሪ አባቱ በህይወት እያለ በስጦታ መሰጠቱን እያመነ እና ምስክሮችም በስጦታ ከአባቱ እንደተላለፈ እየመሰከሩለት በ1ኛው ቦታ ድርሻውን ተካፍሎ በ2ኛው ቦታ 20 በ 80 የሆነውን ከ20 አመት በፊት ተላፎልኛል የሚለው ሚዛናዊነት የሌለው በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ተሽሮ ሁሉንም ቦታ በጋራ እንድንካፈል ይወሰንልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል።

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የክርክር መነሻ የሆነውና ተጠቅሶ የቀረበው 20 በ80 ሜትር ይዞታ በግራ ቀኙ መካከል ሳይካፈል የታለፈበት አግባብነት ለማጣራት በሚል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል።

ተጠሪ ባቀረቡት መልስ የስር ፍ/ቤቶች የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያደረጉበት መነሻ ተጠሪ ያቀረብኩትን የመጀመሪያ ደረጃ የይርጋ መቃወሚያ መሰረት በማድረግ ሲሆን መቃወሚያውም የውርስ ጥያቄው እናታችን ከሞተች 20 አመት ካለፈው በኋላ የቀረበ በመሆኑ እና አከራካሪውን ንብረት አመልካች በተጠሪ መያዙን ካወቀ ከ3 አመት በላይ ካለፈ በኋላ የቀረበ በመሆኑ ነው። አመልካች እናታችን በቀን 20/02/1991 ዓ.ም እንደሞተች በግልጽ ያስቀመጠው ሲሆን አቤቱታውን ያቀረበው ደግሞ በቀን 25/03/12 ዓ.ም ነው። በሌላ በኩል ተጠሪ ይዞታውን በእጄ አድርጌ ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ስገለገልበት 25 አመት ያለፈኝ መሆኑን ያቀረብኳቸው ምስክሮች በሚገባ ያስረዱ ከመሆኑም በተጨማሪ የአመልካች ምስክሮችም ይዞታውን አመልካች የውርስ ጥያቄ ከማቅረቡ በፊት ለረጅም ግዜ ስገለገልበት የነበርኩ መሆኑን መስክረዋል። አመልካች በአቤቱታው ይዞታውን እስከ 2011 ዓ.ም አብረን ስንጠቀም ነበር በሚል ያቀረበው ከእውነት የራቀ ሲሆን ተጠሪ ለብቻዬ ስገለገልበት የቆየ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መሆኑን በስር ፍ/ቤት በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ አቤቱታው እናታችን ከሞቱ 20 አመት በኋላ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1000 መሰረት የቀረበው የውርስ ጥያቄ በማንኛውም አስተያየት ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካች በመብቱ ተጠቅሞ የውርስ ጥያቄ እንዳያቀርብ በህግ ፊት ተቀባይነት ያለው ምክንያት የነበረው ስለመሆኑ ማስረዳትም አልቻለም፤ እንዲሁም ይርጋው ከመቆጠር መቋረጥ የሚያስችል ምክንያት የነበረ ስለመሆኑም በስር ፍ/ቤት የቀረበ መከራከሪያ የለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በአመልካች የቀረበው የውርስ ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሰጠው ውሳኔ ምንም አይነት የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ ውሳኔው እንዲጸና በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም በመልስ መልሳቸው አቤቱታቸውን በማጠናከር አቅርበዋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የተፈጸመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀው ከውርስ ሃብት ጋር በተያያዘ ወራሽ ነኝ የሚል ወገን መብቱንና የውርስ ንብረቶቹ በሌላ ወራሽ መያዛቸውን ካወቀ ከሶስት ዓመት በኃላ የሚያቀርበው የወራሽነት ክስ ተቀባይነት እንደማይኖረው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000(1) ስር ተመልክቷል፡፡ ይህን የይርጋ ድንጋጌ አስመልክቶ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 26422 እና 20295 እንዲሁም በሌሎች በርካታ መዛግብት አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ በሌላም በኩል በመጀመሪያው ፍርድ ቤት ያልተነሳውን ክርክና ያልቀረበውን አዲስ ነገር ይግባኝ ሰሚው (የበላይ) ፍርድ ቤት ለመቀበል አይችልም፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በስር ፍርድ ቤት እናታቸው ወ/ሮ አቶሜ አባፎጊ በቀን 20/02/1991 ዓ.ም መሞታቸውን ገልፀው ለወራሾች ሊተላለፍ የሚገባውን ሁለት በታ ላይ ያለ ይዞታና ባህር ዛፍ ድርሻቸውን ተጠሪ እንዲያካፍላቸው የጠየቁት በቀን 25/03/2012 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው በግልፅ ክሱ በይርጋ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ክርክሩ በወራሾች መካከል በመሆኑና ክሱ የቀረበው አውራሽ ከሞቱ ከ 20 ዓመት በኃላ በመሆኑ ይርጋ መቆጠር የሚቋረጥበት ምክንያት ስለመኖሩ ክርክርና ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ ክሱ ከፍሲል በተጠቀሰው የህግ አግባብ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡

አመልካች በውርስ ይዞታው እስከ 2011 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር አብረን ስንጠቀም ቆይተናል በማለት በዚህ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቢገልፁም ይህን ክርክራቸውን በስር ፍርድ ቤት ማቅረባቸውን መዝገቡ አያሳይም። በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳው ክርክር በዚህ ፍርድ ቤት የሚቀርብበትና ተቀባይነት የሚያገኝነት የህግ አግባብ አግባብ የለም።

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት በ1ኛው ቦታ ያለውን መሬት በሚመለከት ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው ብሎ 2ተኛውን የመሬት ይዞታ እኩል እንዲካፈሉ በማለት ውሳኔ መስጠቱ አመልካችን የጠቀመ ነው ከሚባል በቀር ከአመልካች አንጻር ውሳኔው የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም። ተከታዩንም ወስነናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የሲግሞ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 34088 በቀን 20/06/2013 ዓ.ም፣ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 54191 በቀን 25/03/2013 ዓ.ም፣ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 224595 በቀን 22/04/2013 ዓ.ም እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 334929 በቀን 20/05/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል።
2. እግድ ካለ ተነስቷል።
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

ማ/አ የማይነበብ የአምሰት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

??/? /?? ? 203381
?? 30/3/2014 ?/?

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፊይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - 1. አቶ ጌታቸው ዳንደና 2. ወ/ሮ ቅዲስት ቢያዝን

ከጠበቃ- ካሌብ አለባቸው ጋር ቀርበዋል

ተጠሪ - አቶ አልዓዛር ዳዊት

ከጠበቃ ደሳለኝ ደምሴ ጋር ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካቾች የካቲት 25 ቀን 2013 ዓ/ም በተፃፈ አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 758936 የካቲት 17 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 48597 መጋቢት 2 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ማብራሪያ ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ቅሬታቸውን በማቅረባቸው ነው፡፡ ቅሬታቸውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካቾች የሚቃወሙባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልን ይገባል የሚሉትን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤቶች ሟች ከተናዘዘችው ኑዛዜ ውጪ የውርስ ንብረት ለተጠሪ እንዲሰጥ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ መጀመሪያ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ እርማት በሚል አዲስ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልን የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ሟች ወ/ሮ ዓለም ፀሀይ እያሱ በ29/6/1992 ዓ/ም ኑዛዜ አድርጋለች፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከሳሽና ተከሳሾች ካርታ በጋራ ለማውጣት ስንስማማ አብላጫ ድርሻዬን ለመልቀቅ አልተስማማሁም፡፡ በመሆኑም በኑዛዜው መሰረት ክፍፍል እንዲደረግልኝ ሲል ጠይቋል፡፡ ተከሳሾችም ሟች ለከሳሽና ተከሳሾች ኑዛዜ አድርጋለች፡፡ ይሁንና ከሳሽና ተከሳሾች በ7/7/1997 ዓ/ም ባደረግነው የውል ስምምነት ለከሳሽ የአብላጫ ድርሻ የተደረገለት ቢሆንም ሁላችንም እኩል እንድንካፈል የተስማማን በመሆኑ እኩል እንድንካፈል በሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 48597 ግንቦት 9 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ሟች ወ/ሮ አለም ፀሀይ ኑዛዜ ያደረገች መሆኑ አልተካደም፡፡ በ7/7/1997 ዓ/ም በከሳሽና ተከሳሾች መካከል ተደረገ የሚባለው ውል ቤቱን በስማቸው በሶስቱም ስም ለማስመዝገብ የተስማሙና በውሉ ላይ "የቤቱ አብላጫ የኔ ቢሆንም..." የሚል ቃል ሲታይ ድርሻውን ትቷል የሚል ሀሳብ የሚያመለክት ባለመሆኑ ከሳሽና ተከሳሾች በኑዛዜው መሰረት ይካፈሉ ሲል የክፍፍሉን ዓይነት ዘርዝሮ ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚሁ መዝገብ መጋቢት 2 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት ከአፈጻጸም ችሎት ማብራሪያ ተጠይቄያለሁ በሚል የማብራሪያ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተከሳሾች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚሁ መዝገብ መጋቢት 2 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው የማብራሪያ ትእዛዝ ላይ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው በመ/ቁጥር 758936 የካቲት 17 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ስህተት የተፈጸመበት ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኛቸውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካቾችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርበዋል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 48597 ግንቦት 9 ቀን 2009 ዓ/ም በተሰጠው ውሳኔ "በተደረገው ኑዛዜ መሰረት ንብረቶቹ ላይ ለውጥ የተደረገበት ቢሆንም አሁን ባለበት ሁኔታ ተለይቶ እና ተለክቶ ለአመልካቾች ተከፍሎ ይሰጥ" የሚል ሲሆን ውሳኔውም በተጠሪ አመልካችነት እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ፀንቶ ባለበት በተጠቀሰው መዝገብ ላይ በመጋቢት 2 ቀን 2012 ዓ/ም በተሰጠው የማብራሪያ ትእዛዝ ለአመልካቾች ከተሰጡ ቤቶች ውጪ ያሉ በቤት ቁጥር 068 ሥር የሚጠቃለሉ ናቸው በሚል የተወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ሚያዝያ 12 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካቾችም ግንቦት 4 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ሟች ወ/ሮ ዓለም ፀሀይ እያሱ በ29/6/1992 ዓ/ም ባደረገችው ኑዛዜ መሰረት የውርስ ንብረቱ ክፍፍል ይደረግልን ሲል ጠይቆ የአሁን አመልካቾችም መልስ ሰጥተውበት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 48597 ግንቦት 9 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የሟች የውርስ ንብረቶች ሟች በ29/6/1992 ዓ/ም ባደረገችው ኑዛዜ መሰረት እንዲፈጸም ይሄውም 1. በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 08 ቀበሌ25 የቤት ቁጥር 068 ከሆነው ቤት ጋር ተጠቃሎ የሚገኘውን እና አሁን ደግሞ በእነ አላዛር ዳዊት ስም በተዘጋጀው በቤት ካርታ ውስጥ የሚገኘውን በኑዛዜ አገላለጽ በወቅቱ የእቃ መሸጫ ሱቅ ተብሎ የተለየውን ቤት ከኑዛዜ በኋላ በዚህ ቤት ላይ ለውጥ የተደረገበትም ቢሆንም አሁን ባለበት ሁኔታ ተለክቶ ለወ/ሮ ቅድስት ቢያዝን ተከፍሎ እንዲሰጥ፡፡ 2. በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 08 ቀበሌ 25 የቤት ቁጥር 068 ከሆነው ቤት ጋር ተጠቃሎ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሚገኘውን እና አሁን ደግሞ በእነ አላዛር ዳዊት ስም በተዘጋጀው በቤት ካርታ ውስጥ ተጠቃሎ የሚገኘውን በኑዛዜ አገላለጽ በወቅቱ አቶ ጌታቸው ዳንደና ምግብ ቤት አድርጎ ይነግድበት የነበረውን ምግብ ቤት ተብሎ የተለየውን ቤት ከኑዛዜው በኋላ በዚህ ምግብ ቤት በነበረው ቤት ላይ የተደረገ ለውጥ ቢኖርም አሁን ባለበት ሁኔታ ተለይቶ እና ተለክቶ ለአቶ ጌታቸው ዳንደና ተከፍሎ እንዲሰጥ፡፡ 3. ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ ለወ/ሮ ቅድስት ቢያዝን እና ለአቶ ጌታቸው ዳንደና የተወሰነላቸው ሱቅና ምግብ ቤት ለተጠሪዎች ከተሰጠ በኋላ የሚቀረውን በአ/አበባ ከተማ ወረዳ 8 ቀበሌ 25 የቤት ቁጥር 068 የሆነው ቤት እና በአሁኑ ሰዓት ደግሞ በእነ አላዛር ዳዊት ስም በተዘጋጀው ካርታ የሚታወቀው ዋና መኖሪያ ቤት ከነ ከፍት ይዞታዎቹ ከሌሎቹ ወራሾች በአብላጫነት ተከፍሎ ለአቶ አላዛር ዳዊት እንዲሰጥ ሲል ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በግልጽ እንደሚያመለክተው ለአሁን 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች የውርስ ንብረት ክፍፍሉ ለወ/ሮ ቅድስት ቢያዝን የእቃ መሸጫ ሱቅ የነበረው ከኑዛዜ በኋላ በዚህ ቤት ላይ ለውጥ የተደረገበትም ቢሆንም አሁን ባለበት ሁኔታ እንዲሰጣት የሚልና ለአቶ ጌታቸው ዳንደና ምግብ ቤት የነበረው ከኑዛዜው በኋላ በዚህ ምግብ ቤት ላይ የተደረገ ለውጥ ቢኖርም አሁን ባለበት ሁኔታ እንዲሰጠው የሚል ነው፡፡ በመሆኑም የፍርድ አፈጻጸም ችሎቱ ለአሁን አመልካቾች እንዲሰጣቸው የተባሉት ቤቶች ላይ ከኑዛዜ በኋላም በነዚህ ቤቶች ላይ የተደረገ ለውጥ ቢኖር አሁን ባለበት ሁኔታ የተወሰነላቸው በመሆኑ ከዚሁ ውሳኔ አንጻር አይቶ ማስፈጸም ሲቻል ማብራሪያ በሚል ምክንያት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቤቶቹን ኑዛዜውን መሰረት በማድረግ በካሬ ሜትር ለይቶ የሰጠው አዲስ ውሳኔ ከሥነ ሥረዓት ህጉ ውጪ የራሱን ውሳኔ በመለወጥ የተሰጠ ውሳኔ የሚሆን ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 373 (2) እንደ ፍርድ እንዲያስፈጽም ትእዛዝ የተላለፈለት ፍርድ ቤት የተላለፈለትን ጽሁፎች በአንድ መዝገብ ውስጥ ይዞ ስለ ፍርዱ ትክክለኛነት ወይም በግልባጮቹ ላይ ስለ ሰፈረው ነገር ሌላ መግለጫና ማብራሪያ ሳይጠይቅ በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ማስፈጸም አለበት፡፡ ስለሆነም የፍርዱን ወይም የትእዛዙን ወይም የግልባጩን ትክክለኛነት የሚያጠራጥር ልዩና በቂ ምክንያት ያጋጠመው እንደሆነ ይህንኑ መዝግቦ ማረጋገጫ የሚሆን ማስረጃ እንዲላክለት ለመጠየቅ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 48597 ግንቦት 9 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው፣ በኑዛዜው መሰረት ውሳኔ አልተሰጠኝም የሚል ወገን ወይም ውሳኔው ግልጽ ያልሆነና የማይፈጸም ነው የሚል ወገን ካለ ቅሬታውን በይግባኝ ለሚያየው ፍ/ቤት አቅርቦ ማሳረም እንጂ በማብራሪያ መክንያት መጀመሪያ ከተሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ መስጠት የሥነ ሥረዓት ህጉ የማይፈቅድና ህጋዊ መሰረትም የሌለው ነው፡፡ በሌላ በኩል በዚህ ጉዳይ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አከራክሮ በመ/ቁጥር 48597 ግንቦት 9 ቀን 2009 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የአሁን አመልካቾችና የአሁን ተጠሪ ቅሬታ አቅርበውበት እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይም ነው፡፡ የአሁን ተጠሪም በዚሁ ማብራሪያ ተብሎ ውሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ የማብራሪያ ትእዛዝ ሳይሰጥበት በፊት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦበት እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ውሳኔ ያገኘ ሲሆን ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ እንደገና በማብራሪያ ምክንያት አዲስ ውሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 758936 የካቲት 17 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 48597 መጋቢት 2 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ማብራሪያ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት መጋቢት 17 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ኮ/ቀ/ም/ችሎት የመ/ቁጥር 76038 ላይ የተሰጠው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

ማ/አ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በዳንኤል ፍቃዱ (ጠበቃና የህግ አማካሪ)

ያልታተሙ የሰበር ውሳኔዎች በአንድ ተሰብስበው የተዘጋጁ

ቅፅ _ 4